# ድርሳነ ፡ ማሕየዊ ፡፡

## ወመልክአ ፡ ማሕየዊ ፡፡

## ግዕዝና ፡ አማርኛ ፡፡

# ድርሳነ፡
## ማሕየዊ።
## ወመልክአ፡
## ማሕየዊ ።

በግዕዝና፡በአማርኛ

# መግለጫ ።

እግዚአብሔር ፡ ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ የሚሠራው ፡ በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ ነውና ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ የደህንነቱ ፡ የጊዜ ፡ መለኪያ ፡ ሰዓቱን ፡ ባመለከተ ፡ ጊዜ ፡ ተቀዳሚ ፡ ተከታይ ፡ የሌለው ፡ አንድ ፡ ልጁን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰማየ ፡ ሰማያት ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ልኮ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ ተወለደ ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ነቢያት ፡ አቤቱ ፡ የማዳንህ ፡ ጊዜው ፡ ረዘመብን ፡ ኃይልህን ፡ ገልጸህ ፡ ልዑል ፡ ክንድህን ፡ ከላይ ፡ ከአርያም ፡ ሰደህ ፡ ከዲያብሎስ ፡ ቍራኝነት ፡ ከሲኦል ፡ ጥገኝነት ፡ ከገሃነመ ፡ እሳት ባርነት ፡ ነፃ ፡ አውጣን ፡ እያሉ ፡ የሚጸልዩት ፡ ከትንቢት ጋር ፡ የተባበረ ፡ ጸሎታቸው ፡ ተቀባይነት ፡ ያለው መሆኑ ፡ ተረጋገጠ ። ሰውና ፡ መላእክትም ፡ በመተባበር ፡ ስለተፈጸመው ፡ ተስፋና ፡ ስለተገኘው ፡ ነፃነት ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ አቀረቡ ። ኃይለኛ ፡ የሆነውን ፡ የልቡናን ፡ ዓለማዊ ፡ ስሜት ፡ ለመቆጣጠር ሰብአዊ ፡ ኃይል ፡ ባይኖርም ፡ በጸሎትና ፡ በእምነት ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጩኸቷን ፡ የምታሰማ ፡ ሰውነት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መልስ ፡ አይነፈጋትምና ።

ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ በቤተ ልሔም ፡ ተወልዶ ፡ በግዕዘ ፡ ሕፃናት ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ እያለ አድጎ ፡ ከናዝሬት ፡ ወደገሊላ ፡ እየተመላለሰ ፡ ልዩ ልዩ ፡ ተአምራትን ፡ በማድረግና ፡ የወንጌልን ፡ መንግሥት ፡ እያስተማረ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ተልእኮውን

አከናውኖ ፣ ወደሰማይ ፣ ካረገ ፣ በኋላ ፣ ለሐዋርያት ፣ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፣ ልኮላቸው ፣ አራቱ ፣ ወንጌላውያን ፣ ቅዱስ ፣ ወንጌልን ፤ ከዚያም ፣ ቅዱስ ፣ ወንጌልን ፣ መሠረት ፣ በማድረግ ፣ ብፁዓን ፣ ሐዋርያት ፣ ሐዋርያዊ ፣ ሥራቸውንና ፣ ወንጌላዊ ፣ መልእክቶቻቸውን ፡ ሲጽፉ ፣ ከመዋዕለ ፣ ስብከቱ ፣ እስከ ፡ ዕለተ ሞቱ ፣ ከጌታ ፣ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፣ ያልተለዩ ፣ ከቅዱሳት ፣ አንስት ፣ መካከል ፣ ኤልሳቤጥ ፣ ቤርዜዳንና ፣ ሜልቴዳን ፣ የተባሉ ፣ ደግሞ ፣ ይህን ፣ የቅዱስ ወንጌል ፣ አካል ፣ የሆነ ፣ ድርሳነ ፣ ማኅየዊ ፣ የተባለ መጽሐፍ ፣ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የ ሠ ራ ው ን ትሩፋት ፤ ያደረገውን ፣ ተአምራትና ፡ ለሰው ፡ ልጅ ሲል ፡ የተቀበለውን ፣ ፀዋትወ ፡ መ ከ ራ ፡ በወንጌላውያን ፡ ትብብር ፡ ጽፈው ፡ በየጊዜው ፡ የ ተ ነ ሡ ፣ ሊቃውንት ፡ በጸሎቱ ፡ ኃ ይ ለ ፣ ቃ ል ፡ ድ ው ይ ፡ እየፈወሱበት ፡ ጉባጣ ፡ እያቀኑበት ፡ ዕውር ፡ እያበሩበት ፡ ከትውልድ ፡ ወደትውልድ ፡ እየተላለፈ ፣ መጥቶ ፣ እነሱ ፣ የተጠቀሙትን ፣ ጥቅም ፡ ልንጠቀምበት ፡ እነሆ ፡ አሁኑ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፣ ደ ር ሷ ል ።

ይልቁንም ፡ እግዚአብሔር ፡ አዳምን ፡ በአርአያውና በአምሳሉ ፡ ከፈጠረ ፡ በኋላ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ብቻውን ይሆን ፡ ዘንድ ፡ አይገባውም ፡ ብሎ ፡ ሔዋንን ፡ ረዳት ፡ አድርጎ ፡ ፈጠረለት።


Ω

## የሰኞ ፡ ድርሳን ፡ ማሕየዊ ።

## አንደኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ልዩ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ ስም ፤ ልዩ ፡ በሆነ ፡
በወልድ ፡ ስም ፤ ልዩ ፡ በሆነ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ስም ፡ የጌትነቱ ፡ ምስጋና ፡ በሰማይ ፡ በምድር ፡
የመላ ፡ ፍጹም ፡ አሸናፊ ፡ በሚሆን ፡ በአንድ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ አምናለሁ ። እያመንሁም ፡ ለዘ
ላለም ፡ በሦስትነት ፡ ጸንቶ ፡ ለሚኖር ፡ ለአብ ፡ ለወ
ልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እሰግዳለሁ ። ዘወትር ፡ ባን
ድነቱ ፡ ጸንቶ ፡ ለሚኖር ፡ ለአብ ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ
ቅዱስ ፡ እሰግዳለሁ ። ያለሱ ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ ለሌለ ፡
ለአብ ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እሰግዳለሁ ።

፪ ፤ ክፉ ፡ ነገር ፡ ከማሰብ ፡ ከመስማት ፡ ከመናገር ፡ ንጽ
ሕት ፡ ለምትሆን ፡ ለዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ መመኪያ ፡ ለሆ
ነች ፡ በድንጋሌ ፡ ኅሊና ፡ በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፡ ለጸናች ፡
አምላክን ፡ ለወለደች ፡ ለእመቤታችን ፡ እሰግዳለሁ ።
በመከራው ፡ ጊዜ ፡ ከጐኑ ፡ በፈሰሰ ፡ ደምና ፡ ውሃ ፡ ለከበረ
ለጌታችን ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መስቀል እሰግዳለሁ ።

፫ ፤ ልዩ ፤ ሦስት ፡ ሆይ ! ሦስት ፡ አራት ፡ ከሚሆን
ከኃጢአቴ ፡ ፍዳ ፡ አድነኝ ። ልዩ ፡ ሦስት ፡ ሆይ ! ሰባ
ቱን ፡ አንድ ፡ እያልህ ፡ እስከ ፡ ፸ ፡ ድረስ ፡ የሠራሁትን
በደሌን ፡ ይቅር ፡ በለኝ ። ልዩ ፡ ሦስት ፡ ሆይ ! በአምስት
መቶ ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ ያይደለ ፡ በብዙ ፡ ሺህ ፡ የሚቆ
ጠር ፡ የበደሌን ፡ ዕዳ ፡ አጥፋልኝ ። የሰውን ፡ ሁሉ ፡
በደል ፡ ይቅር ፡ የምትል ፡ አንተ ፡ ነህና ፡ በዕውነት ።

፩ ፤ የጌታችን ፡ የፈጣሪያችን ፡ የመድኃኒታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሞቱንና ፡ የመከራውን ፡ ነገር ፡ የሚናገር ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ። ዓለምን ፡ ሁሉ ፡ የሚያድን ዓለምን ፡ ሁሉ ፡ የሚወድ ፡ ለዓለም ፡ ሁሉ ፡ ቤዛ ፡ የሆን ፡ ዓለምን ፡ ሁሉ ፡ የሚጠብቅ ፡ ዓለምን ፡ ሁሉ ፡ የሚታደግ ። ጌታችን ፡ የመከራውን ፡ ነገር ፡ ያስተማራቸው ፡ ኤልሳቤጥና ፡ መልቴዳ ፡ በርዜዳ ፡ የሚባሉ ፡ ሦስቱ ፡ ደናግልና ፡ ዐራቱ ፡ ወንጌላውያን ፡ የጻፉት ፡ በዕለተ ፡ ሰኑይ ፡ የሚነበብ ፡ የሚጸለይ ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ።

፪ ፤ የዚህም ፡ መጽሐፍ ፡ ስሙ ፡ ድርሳን ፡ ማሕየዊ ይባላል ። በመጋቢት ፡ ፳፯ ፡ ቀንና ፡ እንዲሁም ፡ በየወሩ የሚያነበው ፡ የሚደግመው ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ። በነፍሱም ፡ በሥጋውም ፡ ይከበራል ። በመንግሥት ፤ ሰማያትም ፡ ዕድል ፡ ፈንታው ፡ ከፈያታዊ ፡ ዘየማን ጋራ ፡ ይሆናል ። በየሳምንቱም ፡ ዐርብ ፡ ዐርብ ፡ ቀን ፡ የሚደግመው ፡ በነፍሱም ፡ በሥጋው ፡ ይከበራል ፡ በመንግሥት ፡ ሰማያትም ፡ ዕድል ፡ ፈንታው ። ጌታችንን ፡ ከገነዙ ፡ ከኒቆዲሞስና ፡ ከዮሴፍ ፡ ጋራ ፡ ይሆናል ።

፫ ፤ በየሳምንቱ ፡ ዐርብ ፡ ቀን ፡ በጸሎትና ፡ በጾም ፡ በልቅሶና ፡ በኀዘን ፡ እስከ ፡ ፲፪ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ የመከራውን መታሰቢያ ፡ እናደርግ ፡ ዘንድ ፡ ሐዋርያት ፡ አዘዋልና ። ያም ፡ ባይሆን ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ። በየቀኑም በ፯ቱ ፡ ጊዜያት ፡ የሚደግመው ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ በነፍሱም ፡ በሥጋውም ፡ ፈጽሞ ፡ ይከብራል ። በመንግሥት

ስማያትም ፡ ዕድል ፡ ፈንታው ፡ እስከ ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ በየቀኑ ፡ የጌታውን ፡ መከራ ፡ እያሰበ ፡ ካለ ቀስ ፡ ከጌታ ፡ ባለሟል ፡ ከዮሐንስ ፡ ጋራ ፡ ይሆናል ።

፯ ፤ አቤቱ ፡ ጌታችን ፡ ሆይ ፤ ተቀዳሚ ፡ ተከታይ ፡ ስለሌለው ፡ ልጅህ ፡ ስለ ፡ ወዳጅህ ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ዐማኑኤል ፡ ብለህ ፡ ይቅርታህን ፡ ከኛ ፡ አታርቅ ፡ ቃል ፡ ኪዳንህንም ፡ አታፍርስ ። በውነት ፡ ለዘላለሙ ፨

፰ ፤ በአብ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ህልው ፡ ሆኖ ፡ የሚኖር ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። ፡ርሱም ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ህልዋን ፡ ሆነው ፡ የሚኖሩ ። ልቡ ናው ፡ አብ ፡ ያንደበቱም ፡ ትንፋሽ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚሆን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እሱም ፡ የአብ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቃላቸው ፡ የሚሆን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በልዕልና ፡ ሳለ ፡ በመሠረት ፡ ያለውን ፡ የሚያይ ።

፱ ፤ በውነት ፡ ከሰማይ ፡ በቸርነቱ ፡ ወርዶ ፡ ክብርት ድንግል ፡ ከምትሆን ፡ ከመቤታችን ፡ ከሥጋዋ ፡ ሥጋ ፤ ከነፍሷ ፡ ነፍስ ፡ ነስቶ ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ካምስት ፡ ቀን ፡ በማኅፀኗ ፡ ተወስኖ ፤ ልጅነትን ፡ ሰጥቶ ፡ በሥጋው ፡ ወገኖቹ ፡ ያደርገን ፡ ዘንድ ፡ በሰው ፡ ሥጋ ፡ ተወለደ ።

፲ ፤ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ የልደቱ ፡ ነገር ፡ እንደዚህ ፡ ነው ። እናቱ ፡ እመቤታችን ለዮሴፍ ፡ በታጨች ፡ ጊዜ ፡ ሳይገናኙ ፡ በግብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፀንሳ ፡ ተገኘች ። በድንጋሌ ፡

ሥጋ ፡ በድንጋሌ ፡ ነፍስ ፡ ጸንታ ፡ ያለች ። የዚህ ፡ ዓለም ፡ ሀልዮ ፡ የሌለባት ፡ ከፉ ፡ ከመናገር ፡ ከመስማት ፡ ከመዳሰስ ፡ ድንግል ፡ ናትና ። ዕጮኛዋ ፡ ዮሴፍ ፡ ግን ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ነበረና ፡ ሊገልጣት ፡ ሊያጣላት ፡ አልወደደም ። ሥውር ፡ ሊተዋት ፡ ሊያኖራት ፡ ወደደ ፡ እንጂ ።

፲፩ ፡ ይህንም ፡ ሲያስብ ፡ እነሆ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ለዮሴፍ ፡ በሕልም ፡ ተገልጾ ፡ ተነጋገረው ። የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ዮሴፍ ፡ ሆይ ፡ ዕጮኛህ ፡ ማርያምን ፡ መቀበል ፡ አትፍራ ። ከሷ ፡ የሚወለደው ፡ በግብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነውና ። እነሆ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ትወልዳ ለች ፡ ስሙንም ፡ ኢየሱስ ፡ (መድኃኒት) ትለዋለች ። እሱ ፡ ወገኖቹን ፡ ከኃጢአታቸው ፡ ፍዳ ፡ ያድናቸዋልና ።

፲፪ ፡ ይህም ፡ ሁሉ ፡ የተደረገው ፡ ነቢይ ፡ ከእግዚ አብሔር ፡ አግኝቶ ፡ እነሆ ፡ ድንግል ፡ ትፀንሳለች ፡ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ትወልዳለች ፡ ስሙንም ፡ ዐማኑኤል ይሉታል ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ነገር ፡ ይደርስ ፡ ይፈ ጸም ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ዐማኑኤልም ፡ ማለት ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ የሆነ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፲፫ ፡ ዮሴፍም ፡ ከዕንቅልፉ ፡ ነቅቶ ፡ የእግዚአብ ሔር ፡ መልአክ ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረገ ። ዮሴፍም ፡ ለድንግልናዋ ፡ ሰገደ ። ለንጽሕናዋ ፡ ለቅድስናዋም ፡ ተገዛ ። ዕጮኛው ፡ የምትሆን ፡ ማርያምንም ፡ ወሰዳት ። በዙር ፡ ተብሎ ፡ የተጠራ ፡ ልጅዋን ፡ እስክትወልድ ፡ ድረስ ፡ አላወቃትም ።

፲፩ ፤ በወለደችውም ፡ ጊዜ ፡ አውራ ፡ ጣቷን ፡ አሠረችው ። በጨርቅም ፡ ጠቅላ ፡ የበለስ ፡ ቅጠል ፡ አለበሰችው ። በበረትም ፡ ውስጥ ፡ አስተኛችው ። በሱ ችግር ፡ እኛ ፡ እንከብር ፡ ዘንድ ፡ ስለኛ ፡ ተቸገረልና ። ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ በሥጋ ፡ ቢበርደው ፡ የሚሞቅ ፡ ያፉቸውን ፡ ትንፋሽ ፡ እየተነፈሱ ፡ ላምና አህያ ፡ አሟሟቁት ። የሲህን ፡ እንስሳ ፡ እስትንፋስ የፈለገ ፡ አምላክ ፡ በላያችን ፡ እፍ ፡ ብሎ ፡ ልጅነትን ሰጠን ። በመለኮታዊ ፡ ትንፋሹም ፡ አከበረን ።

፲፪ ፤ በማሕፀኗ ፡ ሳትፀንሰው ፡ በፊት ፡ መልአክ ፡ ስሙ ፡ ኢየሱስ ፡ ይባላል ፡ ብሎ ፡ እንደነገራት ፡ በተገዘረም ፡ ጊዜ ፡ ዘመዶቿ ፡ ስሙን ፡ ኢየሱስ ፡ ብለው ፡ አወጡለት ። የሚነጹበትም ፡ ወራት ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሙሴ ፡ ሕግ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያቆሙት ፡ ዘንድ ፡ ጌታችን ፡ ሕፃኑን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወሰዱት ። እሱ ፡ የደኅንነትና ፡ የፍቅር ፡ መሥዋዕት ፡ ሲሆን ፡ እሱ ፡ ከኃጢአት ፡ የተለየ ፡ ንጹሕ ፡ ኀዳጌ ፡ በቀል ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ታላቅ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ሲሆን ፤ ከመዓርገ ፡ መላእክት ፡ በላይ ፡ ሲሆን ፤ ስለ ፡ ድካማችን ፡ መከራን ፡ መቀበል ፡ ታግሠ ፡ እሱ ፡ መሥዋዕት ፡ የሚቀርብለት ፡ አምላክ ፡ ሲሆን ፤ ስለሱ ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረቡለት ።

፲፫ ፤ በአራት ፡ እንደተጻፈ ፡ ሕግን ፡ ይፈጽሙለት ፡ ዘንድ ወደቤተ ፡ መቅደስ ፡ ይዘውት ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ ስምዖን

በከንዱ ፡ ተቀብሎ ፡ ከጭኑ ፡ ላይ ፡ አስቀመጠው ፡፡
(ሉቃ ፡ ፪ ፡ ፳፯) ፡፡ እግዚአብሔርንም ፡ አመሰገነው ፡፡
(ሉቃ ፡ ፪ ፡ ፴፬ ፡፡) እናቱ ፡ እመቤታችንንም ፡ ይህ ፡
ብላቴና ፡ ከእስራኤል ፡ ወገን ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡
ለመውደቃቸውም ፡ ለመነሣታቸውም ፡ መፈራረጃ ፡
ሊሆን ፡ የተሾመ ፡ ነው ፡፡ በሚከራከሩ ፡ ሰዎች ፡
ምልክት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡፡ አንችን ፡ ግን ፡ እንደ ፡
ጦር ፡ ልቡናሽን ፡ የሚከፋፍል ፡ ኀዘን ፡ ያገኝሻል ፡፡
(ሉቃ ፡ ፲፱ ፡ ፳፰ ፡ ፳፯ ፡፡) የብዙ ፡ ሰዎች ፡ የልቡና
ቸውን ፡ ሐሳብ ፡ ይገልጽ ፡ ዘንድ ፡፡

፲፯ ፤ የሞቱንም ፡ ነገር ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ ጽኑ ፡ ኀዘን
አዘነች ፡፡ መራር ፡ የሆነ ፡ ልቅሶንም ፡ አለቀሰች ፡፡ ጌታችን
ኢየሱስም ፡ በተወለደ ፡ በሁለት ፡ ዓመቱ ፡ ከናቱ ፡ ከመ
ቤታችን ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ደጋው ፡ ተራሮች ፡ ወደ ፡ ግብጽም
አውራጃ ፡ ብሔረ ፡ አግዓዚም ፡ (ኢትዮጵያ ፡) ወደምት
ባል ፡ አገር ፡ ተሰደደ ፡፡ ዮሴፍም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መል
አክ ፡ እንደ ፡ ነገረው ፡ ብቻውን ፡ ተከተላት ፡፡ በጥምና ፡ በረ
ኃብ ፡ ተሰደደ ፡ ጊዜው ፡ ሳይደርስ ፡ ሄሮድስ ፡ እንዳይድገ
ለው ፡፡ በወንጌል ፡ የታዘዘ ፡ ሥርዓት ፡ ሁሉ ፡ እንዳይቀ
ርብን ፡፡ ዳግመኛም ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስና ፡ ከጥምቀት ፡
የሚገኝ ፡ ልደት ፡ እንዳይቀርብን ፡፡ ኃጢአትን ፡ ለማ
ስተሥረይ ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ መቀበል ፡ እንዳይቀ
ርብን ፡፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትም ፡ ለማግኘት ፡፡ ጌታችንም
ሄሮድስ ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ በየተራራው ፡ በየዋሻው ፡
በየፍርኩታው ፡ በየዕንጨቱ ፡ ግንድ ፡ ውስጥ ፡ ተሸሸገ ፡፡

፲፰ ፤ ነገር ግን ፥ በጌታችን ፥ በኢየሱስ ፥ ስደት ፥ ሞት ፥ ከኛ ፥ ራቀ ። በጌታችን ፥ በኢየሱስም ፥ መስ ደድ ፥ ሞት ፥ ከኛ ፥ ተለይቶ ፥ ተሰደደ ። ሄሮድስም ከሞተ ፥ በኋላ ፥ ሦስት ፥ ዓመት ፥ ከስድስት ፥ ወር ፥ ( መንፈቅ ፥ ) ጌታችን ፥ ኢየሱስ ፥ ክርስቶስ ፥ ወዳገሩ ወደ ፥ ናዝሬት ፥ ተመለሰ ። ጥቂት ፥ በጥቂት ፥ እያለ ፥ አደገ ። ማደጉም ፥ በልብስ ፥ ማጌጥና ፥ በክብር ፥ አይደ ለም ። እንደ ፥ ድሆች ፥ ልጆች ፥ ለዘመዶቹ ፥ እየታዘዘ ፥ በታላቅ ፥ ተግሣጽ ፥ አደገ ፥ እንጂ ። በመጨረሻውም በዐርብ ፥ ቀን ፥ ግን ፥ ደዌያችንን ፥ ተቀበለ ፤ መከ ራችንንም ፥ ተሸከመ ። ከራድዮን ፥ የሚባል ፥ ወፍ ፥ ሰውን ፥ ለማዳን ፥ የሰውን ፥ ደዌ ፥ እንዲቀበል ፥ እንዲሁ ፥ ተቀበለ ፥ አቤቱ ፥ ጌታችን፥ ሆይ ፤ እኔን ፥ አገልጋይህን፥ ከኃጢአት ፥ ሞት ፥ አድነኝ፥ አሜን ።

## ሁለተኛ ፥ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ይሁዳም ፥ አማቹ ፥ በርባንን ፥ ለማዳን ፥ የዋ ጋው ፥ ተጨማሪ ፥ አድርጎ ፥ ጌታችን ፥ ኢየሱስን ፥ ለሠላሳ ፥ ብር ፥ ሸጠው ። ወንጌላውያንም ፥ እንዲህ አሉ ። የአስቆሮቱ ፥ ሰው ፥ ይሁዳ ፥ ወደ ፥ ካህናቱ ፥ አለቆች ፥ ሄዶ ፥ እነሆ ፥ ኢየሱስን ፥ አሲዛችኋለሁ ፥ ምን ፥ ትሰጡኛላችሁ ፥ አላቸው ። ደስ ፥ ብሏቸ ውም ፥ ሠላሳ ፥ ብር ፥ ሊሰጡት ፥ ተነጋገሩት ።

፪ ፤ ከዚያ ፥ ቀን ፥ ጀምሮ ፥ የሚያሲዝበትን ፥ ጊዜና ቦታ ፥ ይፈልግ ፥ ጀመረ ። ይሁዳም ፥ ምንም ፥ የደንጊያ ፥

ምስስ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ቆሞ በሰው ፡ አንደበት ፡ እየተ
ናገረ ፡ ቢገሥጸው ። ምንም ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ በላዩ ፡
ስጣ ፡ ቢጠጣበት ። ምንም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡
ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ከናንተ ፡ አንዱ ፡ እንዲያሲዘኝ ፡
እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ ሲነግራቸው ፡ ቢሰማ ።
የሚያሲዝበትን ፡ ምክር ፡ አልተወም ።

፫ ፤ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ብዙ ፡
አዘነው ፡ ኢየንዳንዳቸው ፡ መምህር ፡ እኔ ፡ ነኝን ፡ እኔ ፡
ነኝን ፡ አሉት ። ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ መለሰ ። የሚ
ያሲዘኝ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ ወጭት ፡ አግብቶ
የሚጠልቀው ፡ ነው ፡ አላቸው ። የሰው ፡ ልጅ ፡ ግን ፡
እንደ ፡ ተጻፈለት ፡ ይሄዳል ። ነገር ፡ ግን ፡ የሰው ፡
ልጅን ፡ ለሚያሲዘው ፡ ለዚህ ፡ ሰው ፡ ወዮለት ፡
ባይወለድ ፡ በተሻለው ፡ ነበር ።

፬ ፤ ዳግመኛም ፡ ባጠገቡ ፡ የተቀመጠ ፡ ደቀ ፡
መዝሙሩ ፡ ዮሐንስ ፡ አቤቱ ፡ ማነው ፡ የሚያሲዝህ
ብሎ ፡ በጠየቀው ፡ ጊዜ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡
የሚያሲዘኝ ፡ እኔ ፡ እንጀራ ፡ በወጥ ፡ ጠቅሼ ፡ የምሰ
ጠው ፡ ነው ፡ አላቸው ። ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ለአስቆ
ሮቱ ፡ ሰው ፡ ለይሁዳ ፡ እንጀራውን ፡ በወጥ ፡ ጠቅሶ
ሰጥቶ ፡ የምታደርገውን ፡ ፈጥነህ ፡ አድርግ ፡ አለው ።

፭ ፤ ይሁዳም ፡ እንጀራውን ፡ ተቀብሎ ፡ በሌሊት ፡
ወጥቶ ፡ ወደ ፡ አይሁድ ፡ ሄዶ ፡ እነሆ ፡ ኢየሱስን ፡
አሲዛችኋለሁና ፡ የምትሰጡኝን ፡ ስጡኝ ፡ አላቸው ።
ሠላሳ ፡ ብር ፡ ሰጡት ። እሱም ፡ ለሚስቱ ፡ ሰጣት ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ማን ፡ በመሸጠ ፡ ከአራትና ፡ ከዕፀ ፡ በለስ ፡ እርግማን ፡ ተወጃጀን ፡፡

## ሦስተኛ ፡ ምዕራፍ ፡፡

፮ ፤ ጌቶቼ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፤ አደራ ፡ እላችኋለሁ ፡፡ እመቤቴ ፡ ማርያም ፡ እማልድሻለሁ ፡፡ በነፍሱና ፡ በሥጋው ፡ በተቀበላቸው ፡ መከራዎች ፡ ሁሉ ፡፡ በመቸንከሩም ፡፡ የሾህ ፡ አክሊልን ፡ ተቀዳጅቶ ፡ በመሰቀሉ ፡፡ በሞቱም ፡ ወደ ፡ ሲኦልም ፡ በመውረዱ ፡፡ በጦር ፡ በመወጋቱ ፡፡

በመቀበሩ ፡፡ ኃጢአቴን ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ ትሉኝ ፡ ዘንድ ፡፡ ከኃጢአቴም ፡ ሁሉ ፡ ፍዳ ፡ ታድኑኝ ፡ ዘንድ ፡ ለዘላለሙ ፡ እማፀናለሁ ፡ አሜን ፡፡

## ዐራተኛ ፡ ምዕራፍ ፡፡

፩ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ከአልዓዛር ፡ ቤት ፡ ወጥቶ ፡ እንዳስለመደ ፡ ይጸልይ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ሄደ ፡፡ በሱ ፡ ምክንያት ፡ አይሁድ ፡ የአልዓዛርን ፡ ቤት ፡ እንዳያጠፉ ፡፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ተከተሉት ፡፡

፪ ፤ ከዚያም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ እንዳትገቡ ፡ ከዚያ ፡ ሄጄ ፡ ጸሎት ፡ እስካደርግ ፡ ድረስ ፡ ከዚህ ፡ ተቀምጣችሁ ፡ ጸሎት ፡ አድርጉ ፡ አላቸው ፡፡ ያዕቆብና ፡ ጴጥሮስን ፡ ዮሐንስንም ፡ ይዞ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ ጌቴሴማን ፡ ወደሚባል ፡ የተክል ፡

ቦታ ፡ ገባ ። ሰውነቱም ፡ በፊታቸው ፡ በነፍስ ፡ መከራ ፡ ታመመች ። እሊህም ፡ መታወክና ፡ መቶ ከዝ ፡ ማዘን ፡ ናቸው ። በሰውነቱ ፡ ታውኢልና ።

፫ ፤ ዛሬ ፡ ግን ፡ ሰውነቴ ፡ ታወከችብኝ ፡ አለ ። ምን ፡ እላለሁ ፡ አባቴ ፡ ሰውነቴን ፡ ከዚች ፡ ሰዓት አድናት ፡ እላለሁ ። (እንጂ) ነገር ፡ ግን ፡ ስለዚህ ነገር ፡ መጥቼ ፡ ከዚህች ፡ ሰዓት ፡ ደርሻለሁ ። እንዲ ዚህ ፡ እያለ ፡ ያዝን ፡ ይቶከዝ ፡ ጀመር ። ሰውነቴም ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ ኀዘን ፡ አዘነች ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ተጋ ታችሁ ፡ ከዚህ ፡ ተቀመጡ ፡ አትተኙም ፡ አላቸው ።

፬ ፤ በሰውነቱ ፡ ፈጽሞ ፡ እንደ ፡ አዘነ ፡ እንደ ፡ ታወከ ፡ እንደዚሁም ፡ ለኛ ፡ ለወገኖቹ ፡ ተድላ ፡ ደስታውን ፡ ሰጠን ። የድንጋይ ፡ ውርወራ ፡ ያኽል ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ርቆ ፡ በጉልበቱ ፡ ተንበርክኮ ፊቱን ፡ ምድር ፡ አስነክቶ ፡ ሰገደ ።

፭ ፤ ስለዚህ ፡ እሱ ፡ በሥጋ ፡ ሲሰግድ ፡ መለኮት ፡ ከሥጋ ፡ አልተለየም ። መለኮትም ፡ ሲሰግድ ፡ ሥጋ ፡ ከመለኮት ፡ አልተለየም ።

፮ ፤ የሚቻልስ ፡ ቢሆን ፡ ይህች ፡ ሰዓት ፡ ከሱ ፡ ታልፍ ፡ ዘንድ ፡ ዳግመኛ ፡ ጸሎት ፡ አደረገ ። አባቴ ሆይ ፡ ሁሉ ፡ ይቻልሃልና ፡ ይህች ፡ ጽዋዕ ፡ (ሞት) ከኔ ፡ ትለፍ ፡ አለ ። ከኔ ፡ ትለፍ ፡ ማለቱ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ አይደለም ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ ሞት ፡ ትለፍ ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ። ነገር ፡ ግን ፡

የኔ ፡ ፈቃድ ፡ ያይደለ ፡ ያንተ ፡ ፈቃድ ፡ ይሁን ። ያንተ ፡ ፈቃድ ፡ ይሁን ፡ ማለቱም ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ይሞት ፡ ዘንድ ፡ አባቱ ፡ ልኮታልና ። የኔ ፡ ፈቃድ አይሁን ፡ ማለቱም ፡ ያለመሞቱን ፡ አይደለም ። መሞት ፡ ፈቃዱ ፡ ነውና ። ስለዚህም ፡ ነገር ፡ የልጁና ያባቱ ፡ ፈቃድ ፡ አንድ ፡ እንደሆነ ፡ ታወቀ ።

፺ ፤ የሚያጽናናው ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ከሰማይ ፡ ታየው ። አቤቱ ፡ ድል ፡ ማድረግ ፡ ከሀሊነት ፡ ላንተ ፡ ይገባል ፡ እያለ ። ሞትንና ፡ ሲኦልን ፡ ዲያብሎስንም ፡ ድል ፡ አድርገሃልና ። ድል ፡ አድርገህም ፡ የአዳምን ፡ ልጆች ፡ ከዲያብሎስ ፡ ቍራኝነት ፡ ለይተሃቸዋልና ።

፺፩ ፤ እሱ ፡ ግን ፡ ፈጽሞ ፡ መላልሶ ፡ ጸለየ ። ከሱ ፡ የራቀ ፡ ሰይጣንን ፡ በጥበቡ ፡ ያቀርበው ፡ ዘንድ ። እሱ ፡ ግን ፡ መላልሶ ፡ ጸለየ ፡ በቸርነቱ ፡ የሞት ፍርሃትን ፡ ከኛ ፡ ያርቅ ፡ ዘንድ ።

## አምስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሄደ ፡ ተኝተውም ፡ አገኛቸውና ፡ ጴጥሮስን አንድ ፡ ሰዓት ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ መትጋትና ፡ መታገስ ፡ ተሳናችሁን ። ወደ ፡ ፈተና ፡ እንዳትገቡ ፡ ተግታችሁ ጸልዩ ። ነፍስ ፡ ጽኑዕ ፤ ሥጋ ፡ ደካማ ፡ ነውና ።

፰ ፤ ዳግመኛም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ሄዶ ፡ ጸለየ ። አባቴ ፡ ሆይ ፡ የሚቻልስ ፡ ቢሆን ፡ ይህ ፡ (ጽዋዕ ፡) እንዳልጠጣው ፡ ከኔ ፡ ይለፍ ፡ አለ ። ነገር ፡ ግን ፡ ፈቃድህ ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ምድርም ፡ ሰገደ ።

፱ ፤ ዳግመኛም ፡ ወደ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ መጣ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ ሁሉ ፡ ተኝተው ፡ አገኛቸው ። ዐይኖቻቸውም ፡ ፈጽመው ፡ በእንቅልፍ ፡ ተይዘዋልና ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ እንደ ፡ ተኙ ፡ ትቷቸው ፡ ሄዶ ፡ በታላቅ ፡ ጩኸት ፡ እያለቀሰ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ መላልሶ ፡ ጸለየ ። ስለሚያምኑበት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ አይደለም ። እሱ ፡ ግን ፡ በወዳጁ ፡ በአልዓዛር ፡ ሞት ፡ ካለቀሰ ፡ በኋላ ፡ ቀድሞም ፡ ስለ ፡ ጠላቶቹ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ አለቀሰ ። ርኅሩኅ ፡ ነውና ።

፲ ፤ ሀገሪቱንም ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ አለቀሰላት ፤ ርኅራኄ ፡ የባሕርዩ ፡ ነውና ። ብታውቂስ ፡ ደኅንነትሽ ፡ ዛሬ ፡ ነበር ፡ አላት ። እንግዲህስ ፡ ዕውቀትሽ ፡ ካይኖችሽ ፡ ተሰወረ ። (ተለየ ፡) ጠላቶችሽ ፡ በላይሽ ፡ ተሰብስበው ፡ የሚከቡሽ ፡ ቀን ፡ ይመጣል ። ከየሀገሩም ፡ ተሰብስበው ፡ ከልጆችሽ ፡ ጋራ ፡ ያጠፉሻል ። ድንጊያ ፡ በድንጊያ ፡ ላይ ፡ ሳይተዉ ፡ (ሳያስቀሩ ፡) የይቅርታሽን ፡ ወራት ፡ አላወቅሽምና ።

፩ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ እንደሚፈራ ፡ ሰው ፡ ነገር ፡ በማብዛት ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ጸሎቱን ፡ አለወጠም ። በብዙ ፡ ስግደቱም ፡ ጊዜ ፡ ወዙ ፡ ላቡ ፡ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ ጠብታ ፡ ሆነ ። ኋላ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ደም ፡ በዝቶ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ወረደ ። ከኛም የኃጢአትን ፡ ወዝ ፡ አጠፋ ። በመስገዱም ፡ የመላእክት አለቆች ፡ እያደነቁ ፡ ሰገዱለት ። የሚሰግዱለት ፡ እሱ ፡ ሰግዶልና ።

፪ ፤ እኛም ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ አካላዊ ፡ ለሆነ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከሥጋው ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ስግደትን ፡ እንሰግዳለን ። ለቃል ፡ እንሰግዳለን ። ለሥጋ ፡ አንሰግድም ፡ ሳንል ። ለቃል ፡ የሰገደ ፡ እነሆ ፡ ለሥጋ ፡ መስገዱ ፡ ነውና ። ለሥጋም ፡ የሰገደ ፡ ለእግዚብሔር ፡ ቃል ፡ መስገዱ ፡ ነውና ።

፫ ፤ ዳግመኛም ፡ እንደዚሁ ፡ አባቶቻችን ፡ ሐዋርያት ፡ ለከበረ ፡ ሥጋ ፡ በሰገዱ ፡ ጊዜ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቃልም ፡ሰገዱ ። ከብዙ ፡ ዕንባና ፡ ከጽኑ ፡ ልቅሶ ጋራ ፡ የሆነ ፡ ጸሎቱም ፡ ስግደቱም ፡ በጌቴሴማኒና ፡ በደብረ ፡ ዘይት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። በዮርዳኖስና ፡ በቆሮንቶስ ፡ በቂሳርያ ፡ ተራራና ፡ በደብረ ፡ ታቦርም ስለኛ ፡ ጸለየ ፡ እንጂ ። ይኸውም ፡ በምሴተ ፡ ኀሙስ ብቻ ፡ አይደለም ። ሰው ፡ በሆነበት ፡ ወራት ፡ ሁሉ ፡ ጧትም ፡ ማታም ፡ ስለኛ ፡ ጸለየ ፡ እንጂ ።

## ስድስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ጌቶቼ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አደራ ፡ እላችኋለሁ እመቤቴ ፡ ማርያም ፡ እማልድሻለሁ ። በነፍሱና ፡ በሥጋው ፡ በተቀበላቸው ፡ መከራዎች ፡ ሁሉ ፡ በመቸንከሩም ። የሾህ ፡ አክሊል ፡ ተቀዳጅቶ ፡ በመስቀሉ ። በመሞቱም ፡ ወደ ፡ ሲኦልም ፡ በመውረዱ ። በጦር ፡ በመዋጋቱ ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በመቀበሩ ። ኃጢአቴን ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ ትሉ ፡ ዘንድ ። ከኃጢአቴም ፡ ሁሉ ፡ ፍዳ ፡ ታድኑኝ ፡ ዘንድ ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

## ሰባተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱም ፡ ጸሎቱን ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ተመልሶ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተኙም ፡ ዕረፉም ፡ አላቸው ። እነሆ ፡ በክፉ ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ያሲዙት ፡ ዘንድ ፡ ጊዜው ፡ ደርሷልና ። እነሆ ፡ የሚያሲዘኝ ፡ (ይሁዳ ።) ቀርቧልና ፡ ከዚህ ፡ ተነሱ ፡ እንሂድ ።

፪ ፤ ይህን ፡ ሲነግራቸው ፡ ከዓሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ አንዱ ፡ ያስቆሮቱ ፡ ሰው ፡ ይሁዳ ደረሰ ። ያንንም ፡ ቦታ ፡ ያውቀው ፡ ነበር ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ቈይታ ፡ ያደርግበት ፡ ነበርና ።

፫ ፤ ይሁዳም ፡ ከፈሪሳውያንና ፡ ከካህናት ፡ አለቆች ፡ ሎላልቶቻቸውንና ፡ የወታደሮችን ፡

ጭፍራ ፡ ተቀብሎ ፡፡ በችቦ ፡ መብራትና ፡ በፋና ፡ ጦርና ፡ ሾተል ፡ ጐመድ ፡ ይዘው ፡ ሄዱ ፡፡ በበዓል ፡ ፈጥነው ፡ ይዘው ፡ ይገድሉት ፡ ዘንድ ፡ ልቡናቸው በቅናት ፡ ተቃጥሏልና ፡፡ ኋላ ፡ ግን ፡ ሕዝቡ ፡ እንዳ ይታወኩ ፡ የምንገድለው ፡ በበዓል ፡ አይደለም ፡ አሉ ፡፡ የሚያሲዘው ፡ ይሁዳም ፡ የምስመው ፡ እሱ ነውና ፡ እሱን ፡ ያዙት ፡ ብሎ ፡ ምልክት ፡ ሰጣቸው ፡፡

፬ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ የሚመጣበትን ፡ ሁሉ ፡ ዐውቆ ፡ እነሱ ፡ ወዳሉበት ፡ ቦታ ፡ ወጣላቸውና ማንን ፡ ትፈልጋላችሁ ፡ አላቸው ፡፡ የናዝሬቱን ፡ ሰው ኢየሱስን ፡ ነው ፡ አሉት ፡፡ እሱም ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አላ ቸው ፡፡ የሚያሲዘው ፡ ይሁዳም ፡ ከሳቸው ፡ ጋራ ፡ ቁሞ ፡ ነበረ ፡፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ባላቸው ፡ ጊዜ ፡ ወደኋላ ፡ ተመልሰው ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ወደቁ ፡፡ ከሚያስደነግጥ ፡ ከቃሉ ፡ ንግግርና ፡ ከሚያስፈራ ፡ የፊቱ ፡ ብርሃን ፡ የተነሣ ፡ ሊይዙት ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ የአይሁድን ፡ ድካም ፡ በቃሉ ፡ ብቻ ፡ ሲያሳውቅ ፡ እንዴት ፡ በም ንስ ፡ አምሳል ፡ ደከመ ፡ ይባላል ፡፡

፭ ፡ ዳግመኛም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ማን ፡ ትፈ ልጋላችሁ ፡ አላቸው ፡፡ የናዝሬቱን ፡ ሰው ፡ ኢየሱስን ነው ፡ አሉት ፡፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አላችሁ ፡ የለምን ፡፡ የም ትፈልጉትስ ፡ እኔን ፡ ከሆነ ፡ እሊህን ፡ ተዉዋቸው ፡ ይሂዱ ፡ አላቸው ፡፡ ከሰጠኸኝ ፡ አንዱ ፡ ስንኳ ፡

አልጠፋም ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ይደርስ ፡ ዘንድ ፡ ይፈጸም ፡

፪ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ይሁዳን ፡ አይሁድንም ፡ እንዲያዩትና ፡ እንዲያውቁት ፡ አደረጋቸው ፡፡ ይሁዳም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ መምህር ፡ ቸር ፡ ውለሃል ? ብሎ ፡ በተንኰል ፡ ሳመው ፡፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ይሁዳን ፡ ወዳጄ ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ በመሳም ፡ አሲዘህ ፡ ልታስገድለው ፡ መጣህን ፡ አለው ፡፡ ጠላቱ ፡ ሲሆን ፡ ጠላቴ ፡ አላለውም ፤ ወዳጄ ፡ አለው ፡ እንጂ ፡፡ ነዳጊ ፡ በቀል ፡ ልቡናው ፡ ትሑት ፡ ጠላቱን ፡ ወዳጅ ፡ ነውና ፡፡ ይሁዳ ፡ ግን ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ አንገቱን ፡ በቀሚሱ ፡ ያዘው ፡፡

፫ ፤ ይሁዳም ፡ አይሁድን ፡ እነሆ ፡ አሲዣችኋለሁ ፡ አጥብቃችሁ ፡ ዓሥራችሁ ፡ ይዛችሁ ፡ ውሰዱት ፡፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ቢያመልጣችሁ ፡ ዕዳ ፡ የለብኝም ፡ አላቸው ፡፡

## ስምንተኛ ፡ ምዕራፍ ፡፡

፩ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስንም ፡ የሺሕ ፡ አለቃና ፡ጭፍሮች ፡ የአይሁድም ፡ ሎሌት ፡ ሆነው ፡ በስንስለት ፡ አጥብቀው ፡ ዓሠሩት ፡፡ አይሁድ ፡ ክፋታቸውን ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ይፈጽሙ ፡ ዘንድ ፡ ወዶ ፡ አስናብታችዋልና ፡፡ ከያዙትም ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ምንም ፡ አልተጣላም ፡፡

፱ ፤ ጴጥሮስም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ይዘው ፡ እንዳሠሩት ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ የማልኮስን ፡ አንገት ፡ ሊቈርጥ ፡ ሾተሉን ፡ መዘዘ ። አንገቱን ፡ አልመታ ውም ። ጌታችን ፡ ባወቀ ፡ የማትሰማ ፡ ቀኝ ፡ ጆሮውን ፡ ቈረጠው ፡ እንጂ ። ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ጴጥሮስን ፡ ሾተልህን ፡ ወደ ፡ አፎቱ ፡ መልስ ፡ አለው ። በሾተል ፡ የመታ ፡ በሾተል ፡ ይሞታልና ። እኔ ፡ ግን ፡ አባቴ ፡ የሰጠኝን ፡ ጽዋዐ ፡ ሞት ፡ ሳልጠጣ አልተውም ፡ ካሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገደ ፡ እሥራኤል ፡ የሚበዙ ፡ ነገደ ፡ መላእክትን ፡ ይልክልኝ ፡ ዘንድ ፡ አባቴን ፡ መጠየቅ ፡ የማይቻለኝ ፡ ይመስልሃልን ። ነገር ፡ ግን ፡ መጽሐፍ ፡ የተናገረው ፡ እንደምን ፡ ይደርሳል ። (ይፈጸማል ።) እንደዚህ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ አለውና ። ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ የማል ኮስን ፡ ጆሮ ፡ አዳነለት ።

፲ ፤ በዚያችም ፡ ሰዓት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ሕዝ ቡን ፡ እንደ ፡ ሌባ ፡ ሾተል ፡ ጐመድ ፡ ይዛችሁ ፡ ልትፈልጉኝ ፡ (ልትይዙኝ ፡) መጣችሁ ? ፡ አላቸው ። ዘወትርም ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ እያ ስተማርሁ ፡ ስኖር ፡ አልያዛችሁኝም ። እጃችሁን ፡ እንኳ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ አልዘረጋችሁም ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ጊዜ ፡ ሰዓታችሁ ፡ ነው ። የጨለማው ፡ አለቃ ዲያብሎስም ፡ የሰለጠነበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ይህም ፡

ሁሉ ፡ የተደረገው ፡ ነቢያት ፡ የተናገሩት ፡ ይደርስ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡፡

፬ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ትተ ውት ፡ ሸሹ ፡፡ በፍታ ፡ ( ነጠላ ፡ ) የለበሰ ፡ አንድ ፡ ጐልማሳ ፡ ተከተለው ፡፡ እሱም ፡ ጐልማሶች ፡ ቢይዙት ልብሱን ፡ ጥሎ ፡ እራቁቱን ፡ ሸሸ ፡፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ሁላችሁም ፡ በዚች ፡ ሌሊት ፡ ትክዱኛላ ችሁ ፡ ብቻዬንም ፡ ትታችሁኝ ፡ ትበተናላችሁ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ነገራቸው ፡፡

፭ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ብቻዬን ፡ አይደለሁም ፡ አባቴ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ነውና ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ከያዙ ትም ፡ በኋላ ፡ ኃጢአት ፡ ያልሠራ ፡ ባንደበቱም ፡ ሐሰት ፡ ያልተናገረ ፡ እሱን ፡ ዐሥረው ፡ ሠላሳ ፡ ጊዜ ፡ በጡጫ ፡ መቱት ፡፡

፮ ፡ ጸሐፍት ፡ ፈሪሳውያን ፡ አይሁድ ፡ ሰዱቃ ውያንም ፡ የስሕተት ፡ ምክንያት ፡ በመፈለግ ፡ በተፈታተኑት ፡ ፈተና ፡ ሁሉ ፡፡ ዓሥረውም ፡ ባመ ጧት ፡ ሴት ፡ ነገር ፡ በሴትና ፡ በወንድም ፡ ነገር ፡፡ ግብርን ፡ በመስጠትና ፡ ግብርን ፡ በመጠየቅ ፡፡ በትን ሣኤ ፡ ሙታንም ፡ ነገር ፡ በነገሩ ፡ ያስቱት ፡ ዘንድ ፡ በጠየቁት ፡ ጊዜ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ አንደበት ፡ ሐሰት ፡ አልተገኘበትም ፡፡ ያንደበቱን ፡ መከናወን ፡ የነገሩንም ፡ መወደድ ፡ አደነቁ ፡ እንጂ ፡፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ትምህርቱን ፡ ለመስማት ፡ ይሽቀዳደሙ ፡ ነበርና ፡፡

፳ ፤ ጌታችን ፡ **ኢየሱስንም** ፡ አፉን ፡ በመቱት ፡ ጊዜ
ከንፈሮቹ ፡ ጥርሶቹም ፡ ታመሙ ፡፡ ከጌታችንም ፡ **ከኢየ
ሱስ** ፡ አፍ ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ ፈሰሰ ፡፡ አሕዛብን ፡ በሚያጠ
ፋበት ፡ ስለቱ ፡ ( ሥልጣን ) በሁለት ፡ ፊት ፡ የሆን
የተሳለ ፡ ሰይፍ ፡ ከአንደበቱ ፡ የሚወጣ ፡ ሲሆን ፤
(ንው ፡) ሑሩ ፡ የሚልበት ፡ ሥልጣን ፡ ገንዘቡ ፡
ሲሆን ፡፡ ዳግመኛ ፡ አይሁድ ፡ ጌታችን ፡ **ኢየሱስን**
ፊቱን ፡ ሃያ ፡ ጊዜ ፡ በጡጫ ፡ መቱት ፡፡ ይኸውም ፡
**እግዚአብሔር ፡ አብን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡** በመ
ልክ ፡ የሚመስል ፡ በባሕርይ ፡ የሚተካከል ፡ ነው ፡፡
፳ ፤ በጌትነቱ ፡ ክብር ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ በተ
ገለጸ ፡ ጊዜ ፡ ተለውጦ ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ ያበራ ፡
መልኩ ፡ ፊቱ ፡ ነው ፡፡ እሱ ፡ የማይጠልቅ ፡ ፀሐይ ፡
የማይጠፋ ፡ ፋና ፡ ነውና ፡፡ በወዳጆቹም ፡ ላይ ፡
ዘወትር ፡ የሚያበራ ፡ ፀሐይ ፡ ነውና ፡፡ ስንፎች ፡
አይሁድም ፡ ከምድር ፡ ነገሥታት ፡ ይልቅ ፡ የሚያ
ስፈራ ፡ ፊቱን ፡ ሲመቱት ፡ **የጌታችን ፡ የኢየሱስ**
የፊቱ ፡ ግርማ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡
የኋሊት ፡ የጣላቸው ፡ መሆኑን ፡ አላሰቡትም ፡፡

## ዘጠነኛ ፡ ምዕራፍ ፡፡

**፩ ፤ ጌቶቼ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አደራ ፡
አላችኋለሁ ፡፡ እመቤቴ ፡ ማርያም ፡ አንችንም ፡
እማልድሻለሁ ፡፡ በነፍሱና ፡ በሥጋው ፡ በተቀበ**

ላቸው ፡ መከራዎች ፡ ሁሉ ። በመቸንከሩም ።
የእሾኽ ፡ አክሊል ፡ ተቀዳጅቶ ፡ በመሰቀሉ ።

፱ ፤ በሞቱም ፡ ወደ ፡ ሲኦልም ፡ በመውረዱ ። በጦር ፡ በመወጋቱ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በመቀበሩ ኃጢአቴን ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ ትሉኝ ፡ ዘንድ ። ከኃጢአትም ፡ ፍዳ ፡ ሁሉ ፡ ታድኑኝ ፡ ዘንድ ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

## የሰኞ ፡ ተአምር ።

፩ ፤ በንዋም ፡ ጊዜ ፡ ያደረገው ፡ ተአምር ፡ ይህ ፡ ነው ። ያን ፡ ጊዜ ፡ መልአክ ፡ መጣ ፡ የብርሃን ፡ መክፈቻዎች በእጁ ፡ ተይዘው ፡ ነበር ። ዐይኖቹንም ፡ መግለጥ ፡ ጀመረ ። እነሆ ፡ ሰማያት ፡ ተከፍተው ፡ በዚያ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ አዩ ።

፪ ፤ ከዚያም ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ የብርሃን ፡ መላእክት ፡ ወርደው ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ አገለገሉት ። በፊቱ ፡ ሲሰግዱ ፡ ሚካኤልና ፡ ገብርኤልን አዩዋቸው ። ጌታችን ፡ ሆይ ፡ ዓለም ፡ ፈጽማ ፡ ጠፍታለችና ፡ ሰዶምና ፡ ገሞራን ፡ እንደ ፡ አቃጠልናት ፡ እናቃጥላት ፡ እናጠፋት ፡ ዘንድ ፡ ለምን ፡ አታዝዘንም ፡ አሉት ።
፫ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ ታገሡ ፡ አላቸው ። መልክተኞቹ ፡ ሚካኤልና ፡ ገብርኤል ፡ አትቈጡ ። አዳም ፡ በኃጢአቱ ፡ ስለወዛው ፡ ወዝ ፡ ፋንታ ። እኔ ፡ የሕይወት ፡ ወዝ ፡ ካልወዛሁ ፡

የሞት ፡ ወገዝ ፡ ከሱ ፡ አይጠፋምና ። መልክተኞቼ ፡ **ሚካኤልና ፡ ገብርኤል ፡** አትቸኩሉ ። ቸርነቴ ፡ ዓለ ምን ፡ ሁሉ ፡ ይገዛልና ፡ አላቸው ።

፯ ፤ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ያሉ ፡ ጭፍሮችንና ፡ አለቆችንም ሁሉ ፡ ወደ ፡ ሰማያት ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ አዘዛቸው ። ይቅርታውና ፡ ቸርነቱ ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ይኑር ፡ ለዘለዓ ለሙ ፡ አሜን ።

## የሰኞ ፡ አርኬ ።

**፩ ፤ ባለመለወጥ ፡ በከበረ ፡ አብ ፡ ስም ፡ አምኜ ፡** የሕማምህን ፡ መሃላ ፡ በማመን ፡ የሕማምህን ፡ ድርሳን ፡ አነብ ፡ ዘንድ ፡ ለሕማምና ፡ ለመሰቀል ፡ ሰው ፡ የሆንህ ፡ **ክርስቶስ ፡** በእሳትና ፡ በነፋስ ፡ አምሳል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ላክልኝ ። መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነገርህን ፡ ሁሉ ፡ ያሳስባልና ።

፪ ፤ በተወሰነ፡ ወር ፡ ከብቸኛ ፡ እናትህ ፡ እንደሚ ያበራ ፡ ዕንቍ ፡ ልደት ፡ የተወለድህ ። ልብህ ፡ የዋህ ፡ የሆነ ፡ የኢሳይያስ ፡ ሕፃን ፡ ወልድ ፡ ደስ ፡ ከሚያሰኝ ፡ ፊትህ ፡ ጋራ ፡ የአባትህን ፡ ፊት ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ በሦስቱ ፡ ንጽሕና ፡ አንጻኝ ።

፫ ፤ ዘመንንና ፡ አዝማንን ፡ የዘመንንም ፡ እኩሌታ በታመነ ፡ ስደትህ ፡ የፈጸምህ ። እንደበት ፡ የሚያ መሰግንህ ፡ ምድረ ፡ ግብፅን ፡ በኪደት ፡ እግርህ ፡

የቀደስከ ፡ ክርስቶስ ። የብዙ ፡ ሽንጋላ ፡ ሰይጣን ፡
ከበኋላህ ፡ እንደ ፡ ሄደ ። ባንተ ፡ ቃል ፡ ከኋላዬ ፡
ሰይጣን ፡ ይሂድ ።

፩ ፤ የሌቦች ፡ አለቃ ፡ ስግብግብ ፡ ሆዱንም ፡ የሚ
ወድ ፡ ይሁዳ ፡ በርባንን ፡ የጥቂት ፡ ዋጋው ፡ መጨ
መሪያ ፡ አድርጎ ። ለጥቂት ፡ ዋጋ ፡ የሸጠኽ ።
መላእክት ፡ ከሎጥ ፡ ጋራ ፡ እንዳደሩ ፡ በመጠበቅ ፡
የሠለጠነ ፡ ኪሩባዊ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ይደር ።
፪ ፤ ትጸልይ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡
የሄድህ ። ገዳይ ፡ የሆነ ፡ የሞት ፡ ጽዋንም ፡ በጸሎ
ትህ ፡ ታሳልፍ ፡ ዘንድ ። ቃልህን ፡ እያሳሰብህ ፡
መሐላህንም ፡ እያሰብህ ። የኤሊ ፡ የልጆቹን ፡
ምግባር ፡ እሠራለሁና ። ከሀሊ ፡ ቃልህ ፡ ይፍ
ታኝ ፡ ይፍታኝ ።
፫ ፤ የጸለይህ ፡ የከበረ ፡ የፊትህ ፡ ወዝ ፡ እንደ ፡
ዝናም ፡ ሲወርድ ። በምድር ፡ ላይ ፡ የሰገድህ ።
የባሪያ ፡ ማልኮስ ፡ የተቆረጠ ፡ ጆሮውን ፡ ያዳንህ ፡
ክርስቶስ ። በራስህ ፡ ዋጋ ፡ ብር ፡ ማደሪያ ፡ ግዛልኝ ።
ባባትህ ፡ ቤት ፡ ብዙ ፡ ማደሪያ ፡ አለና ።
፬ ፤ አቤቱ ፡ በውሃና ፡ በደም ፡ አምሳል ፡ ወዝን ፡
እያንጸፈጸፍህ ፡ ክፉ ፡ ጠላትን ፡ ለማቅረብ ፡ በሰገድህ
ጊዜ ። የሚያመሰግን ፡ የሰማይ ፡ መልአክ ፡ መጣ ፡
ባማረ ፡ በምስጋና ፡ ቃልም ፡ ገናንነትና ፡ ኃይል ፡
ላንተ ፡ ይገባል ፡ አለ ።

፰ ፡ አይሁድ ፡ ይይዙህ ፡ ዘንድ ፡ ጸሐፍትም ፡ ይገድሉህ ፡ ዘንድ ። ከበትሮችና ፡ ከሰይፎች ፡ ጋራ ፡ ከብዙ ጦርም ፡ ጋራ ፡ በችቦና ፡ በፋኖስ ፡ መብራት ፡ የመጡብህ ። ፈጣሪዬ ፡ የዳግም ፡ ሞት ፡ መከራን ፡ አታሳየኝ በይቅርታህ ፡ ማረፊያም ፡ አስቀምጠኝ ።

፱ ፡ አቤቱ ፡ ይሰቅሉህ ፡ ዘንድ ፡ በአደባባይም ፡ ይገድሉህ ፡ ዘንድ ፡ ወደው ። አይሁድን ፡ ማንን ፡ ትፈልጋላችሁ ፡ ባልሃቸው ፡ ጊዜ ። ወደ ፡ ኋላ ፡ ወደቁ ፡ እንቅጥቅጥም ፡ ያዛቸው ። በጸና ፡ መዓትህ ፡ ግን ፡ አላጠፋኻቸውም ።

፲ ፡ ያንተ ፡ ፈቃድ ፡ ከሰማይ ፡ ጠራችህ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ሳለ ፡ በወጥ ፡ ውስጥ ፡ የጠለቀ ፡ ይሁዳ ፡ መሪ ፡ ለሆናቸው ፡ ምልክታቸውን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ። እንዴት ፡ አደርክ ፡ ብሎ ፡ የሳመህ ። አቤቱ ፡ ቀኖናዬን ፡ አታክብድ የንጸሁም ፡ አድርገኝ ። ንስሐዬ ፡ ንስሐ ፡ አይደለምና ።

፲፩ ፡ ብዙ ፡ ላሞች ፡ የከበቡህ ፡ በኃጢአት ፡ የደለቡ ፡ ፍሪዳዎችም ፡ የያዙህ ፡ ከምሴተ ፡ ኀሙስ ፡ ዠምሮ እስከ ፡ ዐርብ ፡ ማታ ፡ ( ሠርክ ) የተፈረደብህ ። ዓለምን ፡ የምታድን ፡ ኢየሱስ ፡ የአባ ፡ አሞንና ፡ የአባ ጳውሊ ፡ ነፍስ ፡ ወዳረገችበት ፡ ነፍሴን ፡ አሳርጋት ።

፲፪ ፡ አይሁድ ፡ ሰዓሬ ፡ ሰንበት ፡ ነህ ፡ ብለው ፡ ገለጠው ፡ በሰኤል ፡ ገመድና ፡ በጽኑዕ ፡ ሰንሰለት ፡ የኋሊት ፡ ፈጽመው ፡ ያሠሩህ ፡ ነፍሳትን ፡ የሚ

ቃሙ ፡ በሰማይ ፡ አሉና ፡ አቤቱ ፡ ከሊህ ፡ እጅ ፡ እኔን ፡ አድነኝ ፡፡

፲፫ ፤ አድነኝ ፤ በጎ ፡ የሚናገር ፡ አንደበትህን ፡ አይሁድ ፡ የመቱህ ፡ ፊትህም ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ በታቦር ፡ የታየ ፡፡ በመልክህ ፡ መልአክ ፡ የተባልህ ፡ ክርስቶስ ፡ ፊትህን ፡ አሳየኝ ፡፡ ቃልህንም ፡ አሰማኝ ፡፡ ሰውነቴ ፡ ፈጽማ ፡ አንተን ፡ ወደደች ፡፡ ዓለምን ፡ የምታድን ፡ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤ ኃጢአቴን ፡ አስተርሥይልኝ ፡፡ በደሌንም ፡ አጥፋልኝ ፡ ጠላቴንም ፡ ሁሉ ፡ አስወግድልኝ ፡ አሜን ፡፡

## የማክሰኞ ፡ ድርሳን ፡ ማሕየዊ ፡፡

## አንደኛ ፡ ምዕራፍ ፡፡

፩ ፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ በዕውነት ፡ በማመን ፡ ዓለምን ፡ ሁሉ ፡ የሚያድን ፡ የጌታችን ፡ የመድኃኒታችን ፡ የሞቱንና ፡ የመከራውን ፡ ነገር ፡ የሚናገር ፡ በዕለተ ፡ ሠሉስ ፡ የሚጸለይ ፡ የሚነበብ ፡ ድርሳን ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡

፪ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስንም ፡ አይሁድ ፡ አስቀድሞ ፡ ወደ ፡ ሐና ፡ ወሰዱት ፡፡ በዚያች ፡ ወራት ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ተሹሞ ፡ ለነበረ ፡ ለቀያፋ ፡ አማቱ ፡ ነበርና ፡፡ ቀያፋ ፡ ፈሪሳውያንንና ፡ የካህናት ፡ አለቆችን ፡ የመከራቸው ፡ ነበረ ፡፡

፫ ፤ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ለመምከር ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ እነሆ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡

ብዙ ፡ ታምራት ፡ ያደርጋል ፡ ምን ፡ እናድርግ ፡ ተባባሉ ። እንዲሁም ፡ ብንተወው ፡ ሁሉ ፡ ያምንበታል ። የሮሜ ፡ ሰዎች ፡ መጥተው ፡ እኛንም ፡ ወገኖቻችንንም ፡ አገራችንንም ፡ ይወስዳሉ ።

፩ ፤ ቀያፋም ፡ እናንተስ ፡ የምትመክሩትን ፡ አታውቁም ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሕዝብ ፡ ከሚጠፉ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ብንገድል ፡ ይሻላል ፡ አላቸው ። ይኸንም ፡ ያለው ፡ ከልቡ ፡ አይደለም ።
ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ይሞት ፡ ዘንድ ፡ ስላለው ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ፡ እንጂ ። ስለ ፡ ሕዝቡም ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። የተበተኑ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ልጆች ፡ ባንድነት ፡ ሊሰበስባቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፭ ፤ ከዚያች ፡ ቀን ፡ ዠምረው ፡ እስከሚሞትባት ፡ ዐርብ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ይገድሉት ፡ ዘንድ ፡ ተማከሩ ። ሲወስዱትም ፡ ከተክሉ ፡ ቦታ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሐና ፡ ቤት ፡ ድረስ ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ወደቀ ። አይሁድ ፡ ግን ፡ በመውደቁ ፡ አዝነው ፡ ከሚያነሡት ፡ ይልቅ ፡ ከፊትና ፡ ከኋላው ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ጊዜ ፡ በእግራቸው ፡ ረገጡት ። የተሳለ ፡ ጦርን ፡ መርገጥ ፡ እንዲብስባቸው ፡ አላወቁምና ።

፮ ፤ አይሁድም ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ያንገቱን ፡ ሥር ፡ ይሙት ፡ ብለው ፡ በታላቅ ፡ ዓመታት ፡ መቱት ። እያንዳንዱም ፡ ለሞት ፡ የሚበቃ ፡ ዐሥራ ፡

ዘጠኝ ፡ ጊዜ ፡ ደበደቡት ። ሁል ፡ ጊዜ ፡ ለመግደል ይፈልጉት ፡ ነበርና ።

፷ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስንም ፡ ዐሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ ጊዜም ፡ ደብድበውት ፡ እንዳልሞተ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ። ክንዶቹን ፡ ስልሳ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ መቱት ፡ ሥጋዎቹን ፡ በሚቆራርጥ ፡ በጽኑዕ ፡ እስራትና ፡ በጽኑዕ ፡ መመታት ፡ ክንዶቹ ፡ ፈጽመው ፡ ታመሙ ።

፷፩ ፤ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ደረቱንም ፡ ከተራበ ፡ ከተጣጋ ፡ ሆዱ ፡ ጋራ ፡ ፳፭ ፡ ጊዜ ፡ መቱት ። መራ ቡም ፡ ዕውነት ፡ ነው ። ሰይጣን ፡ ስንኳ ፡ የጾሙን ፡ ወራት ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ፈጽሞ ፡ እንደ ፡ ተራበ ፡ ዐውቆ ፡ ወደርሱ ፡ ቀረበ ። ሲፈታተነው ፡ የእግዚአብ ሔር፡ ልጅስ ከሆንክ፡ እሊህ፡ ደንጎች፡ እንጀራ፡ ይሁኑ ብለህ፡ እዘዝ ፡ እኔም፡ አንተም፡ ተርበናልና፡ አለው ።

፷፪ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ ሰው ፡ የሚ ድን ፡ በእንጀራ ፡ እንዳይደለ ፡ ተጽፏል ። ከእግዚአ ብሔር ፡ እንደበት ፡ በሚወጣው ፡ ቃል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በማለት ፡ ሰይጣንን ፡ ድል ፡ ነሣው ።

፷፫ ፤ መላእክትም ፡ ሊያገለግሉት ፡ መጡ ። ልዩ ፡ የሚሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ የማይቸነፍ ፡ አቸናፊ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ አመሰገኑት ።

፷፬ ፤ ዳግመኛም ፡ ጌታችን ፡ በጐዳና ፡ ሲሄድ ፡ በተራበ ፡ ጊዜ ፡ የበለስን ፡ ፍሬ ፡ ፈለገ ። ከቅጠል ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ ፍሬ ፡ ስለአላገኘባት ፡ ዘለዓለም ፡ ባንቺ ፡

ላይ ፡ ፍሬ ፡ አይገኝብሽ ፡ ብሎ ፡ ረገማት ። ፈጥናም ፡ ደረቀች ። ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ እንደምን ፡ ፈጥና ደረቀች ፡ ብለው ፡ አደነቁ ።

፲፪ ፤ ሰው ፡ በሆነበት ፡ ወራት ፡ ሁሉ ፡ ስለኛ ፡ ተራበ ። እኛን ፡ ከነፍስና ፡ ከሥጋ ፡ ረኃብ ፡ ያድነን ዘንድ ። እርሱ ፡ ባምስት ፡ እንጀራ ፡ በሁለት ፡ ዓሣ ፡ አምስት ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፤ ባንድ ፡ ዓሣና ፡ በሰባት ፡ እንጀራ ፡ ላራት ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ ያጠገበ ፡ ሲሆን ፤ ስለኛ ፡ ተራበ ።

፲፫ ፤ ወደ ፡ ጥንተ ፡ ነገራችን ፡ እንመለስ ። ከተራበ ፡ ሆዱ ፡ ጋራ ፡ ደረቱን ፡ በመቱት ፡ ጊዜ ፡ የታመሙትን ፡ ሰዎች ፡ በትእዛዙ ፡ ያዳናቸው ፡ የጌታችን ፡ የኢሱስ ፡ ልቡ ፡ በሰውነቱ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚቀልጥ ፡ ሰም ፡ ቀለጠ ።

## ሁለተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ዳግም ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ መጥቶ ፡ ማለደው ። ጌታዬ ፡ ሆይ ፤ ራራልኝ ፡ ልጄ ፡ በጭንቅ ፡ ታሞ ከቤተ ፡ ሕሙማን ፡ ተኝቷልና ፡ አለው ።

፪ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ እኔ ፡ መጥቼ ፡ አድነ ዋለሁ ፡ አለው ።

፫ ፤ ይኸውም ፡ ሹም ፡ መልሶ ፡ ከቤቴ ፡ ልትገባ ፡ አይ ገባህም ። በቃልህ ፡ ይዳን ፡ ብለህ ፡ እዘዝ ፡ ልጄም ፡ ይድ ናል ፡ እንጂ ፡ አለው ። እኔም ፡ እንጂ ፡ ገዥ ፡ ነኝ ፤ የም

ገዛቸው፥፡ጭፍሮች ፡ አሉኝ ። ከዚህ ፡ ያለው ፡ ሂድ ፡ ብለው ፡ ይሄዳል ፤ ሌላውንም ፡ ና ፡ ብለው ፡ ይመጣል ሎሌዬንም ፡ ይህን ፡ አድርግ ፡ ብለው፡ያደርጋል፡ አለው

፩ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ አደነቀ ፡ ለሚከተሉትም ፡ ሰዎች ፡ አላቸው ። በእስራኤል ፡ ውስጥ ፡ እንደዚህ ፡ የ ሚያምን ፡ እን ዳላገኘሁ ፡ እውነት ፡ እላችኋለሁ ። ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በኔ ፡ ስም ፡ አምነው ፡ ከምሥራቅና ፡ ከምዕራብ ፡ ይመጣሉ ። ከአብርሃም ፡ ከይስሐቅና ፡ ከያዕቆብ ፡ ጋራ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ይቀመጣሉ ።

፲፪ ፤ የመንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ ልቅሶ ፡ ጥርስ ፡ ማፋጨት ፡ ወዳለበት ፡ ጨለማ ፡ ያወጧቸዋል ። በቃሉ ፡ ትእዛዝ ፡ ልጁን ፡ አድኖ ይህነን ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ ሂድ ፡ እንደ ፡ ሃይማኖትህ ይሁንልህ ፡ አለው ።

፲፫ ፤ ይኸውም ፡ ሹም ፡ ወደቤቱ ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ልጁን ፡ ድኖ ፡ አገኘው ። አይሁድ ፡ ግን፡ደረቱን፡ከሆዱ ጋራ ፡ በትእዛዝ ፡ የሚያድን ፡ እሱን ፡ ልቡን፡ መቱት።

## ሦስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ዳግመኛም ፡ የከነዓን ፡ ሴት ፡ እየጮኸች ፡ መጣች ። ጌታዬ ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ እዘንልኝ ፡ ልጄን ከፉ ፡ ጋኔን ፡ ይዞ ፡ አእምሮዋን ፡ ያሳጣታልና ፡ አለ ችው ።

፱ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ለልጆች ፡ የቀረበ ውን ፡ እንጀራ ፡ አንሥቶ ፡ ለውሾች ፡ መስጠት ፡ አገባብ ፡ አይደለም ፡ አላት ።

፲ ፤ ይህችም ፡ ሴት ፡ መልሳ ፡ አዎን ፡ ጌታዬ ፡ ውሾችም ፡ እንጂ ፡ ከልጆች ፡ ከጌቶቻቸው ፡ ገበታ የሚጥሉትን ፡ ፍርፋሪ ፡ ይበላሉ ፡ አለችው ። በል ቡም ፡ ትእዛዝ ፡ ከልጅዋ ፡ ጋኔኑ ፡ አወጣ ።

፲፩ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ስለ ፡ ዕምነትሽ ፡ ያ ፡ ጋኔን ፡ ከልጅሽ ፡ ወጣ ፡ ሂጂ ፡ አላት ። ወደ ፡ ቤቷም በተመለሰች ፡ ጊዜ ፡ ጋኔኑ ፡ ከሷ ፡ ወጥቶ ፡ ልጅቱ ፡ ድና ፡ ልብሷን ፡ ለብሳ ፡ ከአልጋ ፡ ላይ ፡ ተቀምጣ ፡ አገኘቻት ። አይሁድ ፡ ግን ፡ ደረቱን ፡ ከሆዱ ፡ ጋራ ልቡንም ፡ መቱት ።

፲፪ ፤ በልቡናውም ፡ ትእዛዝ ፡ ለምጽ ፡ የያዛቸው ፡ ዐሥሩን ፡ ሰዎች ፡ አዳናቸው ። ቸር ፡ ጌታችን ፡ ኢየ ሱስ ፡ ከበጎ ፡ ሣጥን ፡ ልቡናው ፡ በጎ ፡ ነገርን ፡ ያወጣ ታልና ። እንደዚህ ፡ የሚራራ ፡ ልብ ፡ ግን ፡ መከራ ፡ ተቀበለ ። እንደ ፡ ሠም ፡ ቀለጠ ። በመረገጥና ፡ በመ መታት ፡ የውስጥ ፡ሕዋሳቱ ፡ ሁሉ ፡ ታመሙ ።

፲፫ ፤ ስለዚህም ፡ ነገር ። ተአምርም ፡ መታመምም ፡ የሱ፡ናቸው ፡ የትሕትናና ፡ የመለኮት ፡ ቃሎችም ፡ ለአ ንድ ፡ ለክርስቶስ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። አንድ ፡ ክርስቶስን ወደ ፡ ሁለት ፡ አናናፍ ፡ አንለየው ። ሁለት ፡ አካል

ሁለት ፡ አምሳል ፡ ለማለት ፡፡ ሁለት ፡ ፈቃድ ፡ ሁለት ፡ ክፍል ፡ ሁለት ፡ ሥራ ፡ በማለት ፡ እንለየው ፡፡

፩ ፤ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ የመለኮትም ፡ የትስብእ ትም ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡፡ በአህያዋና ፡ በውርንጫዋ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ በትሕትና ፡ የታ ዩትን ፡፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስን ፡ ጭኖች ፡ ሰማኒያ ፡ ጊዜ የመቱት ፡ አሉ ፡፡ የተቀመጠውም ፡ እንደ ፡ አርበኞች በሠረገላና ፡ በፈረስ ፡ አይደለም ፡፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ሰውን ፡ ማጥፋት ፡ አይወድምና ፡፡

፲ ፤ ዮሐንስና ፡ ያዕቆብን ፡ የሰውነታችሁን ፡ መጠን አታውቁምን ፡ እንዳላቸው ፡፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሰውን ፡ ሊያድን ፡ እንጂ ፡ ሊያጠፋ ፡ አልመጣምና ፡፡ ዮሐን ስና ፡ ያዕቆብ ፡ አቤቱ ፡ ኤልያስ ፡ ከሰማይ ፡ እሳት ፡ አውርዶ ፡ እንዳጠፋው ፡ አንተም ፡ የሰማርያን ፡ ሰዎች እሳት ፡ ከሰማይ ፡ አውርደህ ፡ አጥፋቸው ፡ ባሉት ፡ ጊዜ ፡ አላጠፋቸውም ፡፡

፻ ፤ በአህያዋና ፡ በውርንጫዋ ፡ በላይ ፡ በመቀመጡ ፍቅርና ፡ ትሕትናን ፡ እንዳመጣ ፡፡ ወራቱም ፡ የፍቅር ወራት ፡ እንደሆነ ፡ ተገለጠ ፡ (ተረዳ) ከጠላቶቹም ፡ ከአ ይሁድ ፡ እጅ ፡ እንዲያመልጥ ፡ በነሱም ፡ እጅ ፡ እን ዲሞት ፡ ተረዳ ፡፡ ዮርዳኖስ ፡ የፈራቸው ፡ የጌታችን የኢየሱስን ፡ እግሮች ፡ አርባ ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ የመ ቷቸውም ፡ አሉ ፡፡

፲ ፡ ዮርዳኖስም ፡ የጌታችን ፡ እግሮች ፡ ከዳርቻው ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ አርባ ፡ ክንድ ፡ ያህል ፡ ወደ ፡ ኋላው ተመልሶ ፡ ሸሸ ። እሳታውያን ፡ ከሚሆኑ ፡ እግሮቹ ፡ የተነሣ ፡ ዮርዳኖስ ፡ በእሳት ፡ እንዳፈሉት ፡ የፈላ ፡ ሆን ። ኃያላን ፡ በሚሆኑ ፡ እግሮች ፡ ከላይ ፡ ነቁ ፡ አንድ ፡ የነበረ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ከታች ፡ ከሁለት ፡ ተከ ፈለ ። በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ እግሮች ፡ ሥር ፡ አንበ ሪዎችና ፡ ዓሦች ፡ ሰገዱለት ።

፲፩ ፡ ጠላት ፡ ዲያብሎስ ፡ ጽፎ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ያና ረውን ፡ የአዳምና ፡ የሔዋን ፡ የዕዳቸውን ፡ ደብዳቤ በእግሮቹ ፡ አጠፋላቸው ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ በዮ ሐንስ ፡ እጅ ፡ በዮርዳኖስ ፡ የተጠመቀ ፡ በዚህ ፡ ምክ ንያት ፡ ነውና ።

፲ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ወንዝ ፡ ያጠ ምቀው ፡ ዘንድ ፡ ከገሊላ ፡ ወደ ፡ ዮሐንስ ፡ ሄደ ፡ ብሎ ወንጌል ፡ እንደ ፡ ተናገረ ። ዮሐንስም ፡ እኔ ፡ ካንተ እጠመቅ ፡ ዘንድ ፡ እወዳለሁ ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ ወደኔ ትመጣለህን ፡ ብሎ ፡ አይሆንም ፡ አለው ።

፲፫ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ አንድ ፡ ጊዜስ ፡ ተው ፡ ይህ ፡ ለኛ ፡ ተድላ ፡ ነውና ፡ አለው ፡ ዕውነትም ፡ ነገር ፡ (ትንቢተ ፡ ነቢያትን) እንፈጽም ዘንድ ፡ ይገባናል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ተወው ፤ ዮሐን ስም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ክቡር ፡ ምስጉን ፡ የም ትሆን ፡ ብርሃንን ፡ የምትገልጽ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ እያለ ፡ አጠመቀው ።

የማይዳሰስ ፡ ራሱን ፡ ዳሰሰው ፡ ውሆችም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ፈሱ ። በመጠመቁም ፡ ክብር ፡ ስላጣን ፡ ፈንታ በክብር ፡ ላይ ፡ ክብርን ፡ አገኘን ።

፲፩ ፡ ከተጠመቀም ፡ በኋላ ፡ ያን ፡ ጊዜውን ፡ ከውሃው ፡ ወጣ ። እነሆ ፡ ሰማያት ፡ ተከፈቱለት ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ እንደ ፡ ርግብ ፡ ወርዶ ከራሱ ፡ ላይ ፡ ሲቀመጥ ፡ አየ ። እነሆ ፡ የመረጥሁት ደስ ፡ የምሰኝበት ፡ የምወደው ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ከሰማይ ፡ መጣ ። ይህ ፡ ልጄ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሁለት ፡ አይባልም ። አንዱ የማርያም ፡ ልጅ ፡ ሁለተኛው ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ ሊባል ፡ አይገባውምና ።

፲፪ ፡ በጎል ፡ የተወለደው ፡ ሌላ ፡ መላእክት ፡ የሰገዱለት ፡ ሌላ ፡ አይደለም ። የተጠመቀው ፡ ሌላ ፡ አይደለም ፡ አንዱ ፡ ልጄ ፡ ነው ፡ እንጂ ። እግሮቹንና ሕዋሳቶቹን ፡ ሁሉ ፡ የደበደቡት ፡ ጠላቶቹ ፡ ግን ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ መሆን ፡ አለባቸው ።

፲፫ ፡ አይሁድም ፡ እሱን ፡ በመደብደብ ፡ ከደከሙ ፡ በኋላ ፡ በገመድና ፡ በራሱ ፡ ጠጉር ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ አምስት ፡ ጊዜ ፡ ጐተቱት ። ጽሕሙንም ፡ ይዘው ፡ ከወደቀበት ፡ መነሣት ፡ እስኪሳነው ፡ ድረስ ሃያ ፡ ስምንት ፡ ጊዜ ፡ ጐተቱት ።

፲፬ ፡ ከምድርም ፡ አንስተው ፡ ጽሕሙንም ፡ ይዘው በራሱ ፡ ጠጉር ፡ በጐተቱት ፡ ጊዜ ፡ የራሱን ፡ ጠጉር

ሦስት ፡ መቶ ፡ አምስት ፡ ጊዜ ፡ ነጨት ። ደግሞም ፡ ጽሕሙን ፡ ሃያ ፡ ስምንት ፡ ጊዜ ፡ ነጨት ፡ በዚህ ፡ መከራው ፡ ሁሉ ፡ ተቆጥቶ ፡ አልተናገረም ። በሚ ሸልተው ፡ ፊት ፡ የማይናገር ፡ በግ ፡ ነውና ። ይኸ ውም ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ በግ ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር አስቀድሞ ፡ የታወቀ ፡ የተዘጋጀ ፡ ነው ።

፲፰ ፤ በኋላ ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ ስለኛ ፡ ተገለጸ ። ይኸ ውም ፡ የዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአት ፡ የሚያስተሠርይ መሥዋዕት ፡ ነው ። እንዲህም ፡ እየደበደቡ ፡ እየጐ ተቱ ፡ ወስደው ፡ ከሐና ፡ ፊት ፡ አቆሙት ። ዮሐን ስና ፡ ጴጥሮስም ፡ ተከትለውት ፡ ነበር ። ያም ፡ ዮሐ ንስ ፡ በሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ዘንድ ፡ የተላመደ ፡ ነውና ፡ ከጌታችን ፡ ከኢየሱስ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ቦታ ፡ ገባ ። ጴጥሮስ ፡ ግን ፡ ተከልክሎ ፡ ከውጭ ፡ ቀረ ይኸውም ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ዮሐንስ ፡ ለበረኛዪቱ ተናግሮ ፡ ጴጥሮስን ፡ አስገባው ።

፲፱ ፤ በረኛዪቱም ፡ ሴት ፡ ጴጥሮስን ፡ አንተም ፡ ደግሞ ፡ የዚያ ፡ ሰው ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ወገን ፡ ነህ ፡ አለችው ፡ እሱም ፡ አይደለሁም ፡ አላት ። የአይሁድ ፡ ሎሌሎችና ፡ ጭፍሮችም ፡ በዚያች ፡ ሌሊት ብዙ ፡ ብርድ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ እሳት ፡ አንድደው ፡ እየ ጫሩ ፡ ቁመው ፡ ይሞቁ ፡ ነበር ፡ ጴጥሮስም ፡ ከነሱ ጋራ ፡ እሳት ፡ ይሞቅ ፡ ነበር ።

፳ ፤ የካህናቱም ፡ አለቃ ፡ ሐና ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ስለ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱና ፡ ስለ ፡ ትምህርቱ ፡ ጠየቀው ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እኔ ፡ በዚህ ፡ ዓለም በግልጥ ፡ ተናገርኩ ። አይሁድ ፡ ዘወትር ፡ በሚሰበ ሰቡበት ፡ በቤተ ፡ መቅደስና ፡ በምኵራብ ፡ እያስ ተማርኩ ፡ በግልጥ ፡ ተናገርኩ ። በስውር ፡ የተናገር ኩት ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ የለም ፡ እኔን ፡ ለምን ፡ ትጠይ ቀኛለህ ፡ ነገሬን ፡ የሰሙትን ፡ እሊያን ፡ ጠይቃቸው እኔ ፡ የተናርገኩትን ፡ እነሱ ፡ ያውቁታልና ።

፳፩ ፤ ይህንንም ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ ቆሞ ፡ የነበረው ፡ ከሎላልቱ ፡ አንዱ ፡ ለካህናቱ ፡ አለቃ ፡ እንደዚህ ፡ ብለህ ፡ ትመልስለታለህን ፡ ብሎ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ በጥፊ ፡ መታው ።

፳፪ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ ክፉ ፡ ተና ግሬ ፡ እንደሆን ፡ ስለ ፡ ክፋቴ ፡ መስክርብኝ ። በጎ ፡ ተናግሬ ፡ እንደሆን ፡ ግን ፡ በዳኛ ፡ ፊት ፡ ለምን ፡ ትመታኛለህ ፡ አለው ። ይህንም ፡ የተናገረ ፡ በሥ ጋዊ ፡ አንደበቱ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። ከሥጋ ፡ ጋራ የተዋሐደ ፡ ቃል ፡ ለምን ፡ ትመታኛለህ ፡ አለ ፡ እንጂ ።

፳፫ ፤ በጥፊ ፡ ስለ ፡ መመታቱም ፡ ባሕር ፡ ተንቀጠ ቀጠች ፡ ፈሳሽም ፡ ውሃ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ሸሸ ። ሕያው ፡ ባሕርይ ፡ የሚሆን ፡ የአምላክን ፡ ልጅ ፡ የፊቱን ፡ መመ ታት ፡ አይታለችና ።

## ዐራተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ሐናም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ እንደ ፡ ታሰረ ወደ ፡ ካህናቱ ፡ አለቃ ፡ ወደ ፡ ቀያፋ ፡ ሰደደው ። ጴጥሮስም ፡ እስከ ፡ ካህናቱ ፡ አለቃ ፡ ቦታ ፡ ድረስ ፡ ከሩቅ ፡ ተከተለው ። የነገሩንም ፡ መጨረሻ ፡ ያይ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ። ካህናቱና ፡ የካህናቱ ፡ አለቆች ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ይገድሉት ፡ ዘንድ ፡ የሐሰት ፡ ምስክር ፡ ይፈልጉ ፡ ጀመር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አላገኙም ።

፪ ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ የሐሰት ፡ ምስክሮች መጡ ፡ ደክመውም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አላገኙበትም ። ደግሞም ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ መጥተው ፡ ይህማ ፡ ይህን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አፍርሼ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ እሠራዋለሁ ፡ ያለው ፡ ነው ፡ አሉ ፡ ማርቆስም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ጸሐፊዎ ችና ፡ ካህናቱ ፡ የካህናቱም ፡ አለቆች ፡ ወደ ፡ ተሰበ ሰቡበት ፡ ወደ ፡ ካህናት ፡ አለቃ ፡ ቦታ ፡ ወሰዱት ብሎ ፡ ተናግሯል ። ጴጥሮስም ፡ እስከ ፡ ካህናቱ ፡ አለቃ ፡ ቦታ ፡ ድረስ ፡ ርቆ ፡ ተከተለው ። ጴጥሮስም ከሎሌዎቻቸው ፡ ጋራ ፡ በብርሃን ፡ በኩል ፡ ተቀ ምጦ ፡ እሳት ፡ ይሞቅ ፡ ነበር ።

፫ ፤ የካህናት ፡ አለቆችና ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ጌታ ችን ፡ ኢየሱስን ፡ ይገድሉት ፡ ዘንድ ፡ የሐሰት ፡ ምስክርን ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ አላገኙም ።

በሐሰትም ፡ የሚመሰክሩበት ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።
ምስክርነታቸውም ፡ አልተስማማም ። ሌሎች ፡ የሐ
ሰት ፡ ምስክሮች ፡ ተነሥተው ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡
ተናገሩ ፡ ይህ ፡ እጅ ፡ የሠራውን ፡ መቅደስ ፡ አፍ
ርሼ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ሌላ ፡ በእጅ ፡ ያልተሠራ ፡
እሠራለሁ ፡ ሲል ፡ እኛ ፡ ሰማነው ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ።
ከዚህም ፡ ጋራ ፡ ምስክርነታቸው ፡ አልተስማማም ።

፴ ፤ የካህናቱም ፡ አለቃ ፡ ከአደባባይ ፡ መካከል ፡
ተነሥቶ ፡ እሊህ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ሲያሳጡህ ፡ አንድ
ስንኳ ፡ አትመልስምን ፡ ብሎ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን
ጠየቀው ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ ዝም ፡ አለ ፡
ምንም ፡ አልመለሰም ።

፴፩ ፤ ደግሞም ፡ የካህናቱ ፡ አለቃ ፡ የቡሩክ ፡ ልጅ
ክርስቶስ ፡ አንተ ፡ ነህን ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ፡ ዕው
ነትም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ክርስቶስ ፡ አንተ
እንደሆንክ ፡ ትነግረኝ ፡ ዘንድ ፡ በሕያው ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ አማጽኝሃለሁ ፡ አለው ።

፴፪ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እኔ ፡ ክርስቶስ
እንደሆንኩ ፡ አንተ ፡ ትላለህ ፡ አለው ። እነሆ ፡
የሰው ፡ ልጅን ፡ በሰማይ ፡ ደመና ፡ ተቀምጦ ፡
ኀይል ፡ ባለው ፡ ሥልጣን ፡ ሲመጣ ፡ ታዩታላችሁ ።
የካህናቱም ፡ አለቃ ፡ ልብሱን ፡ ቀደደና ፡ እንዲህ ፡
አለ ። እነሆ ፡ ስድቡን ፡ ሰማችሁ ፡ ለምን ፡ ምስክር
ትፈልጋላችሁ ። እንግዲህ ፡ ምን ፡ ትላላችሁ ፡ አላ
ቸው ። ሁሉም ፡ ሞት ፡ ይገባዋል ፡ ብለው ፡ ፈረዱበት

አይሁድም ፡ ከሰው ፡ ልጅ ፡ ይልቅ ፡ ደም ፡ ግባቱ ፡ በሚያምር ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ምራቅ ያበዛላቸው ፡ ዘንድ ፡ ባፋቸው ፡ ውሃ ፡ እየጨመሩ ፡ ምራቃቸውን ፡ ሰባ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ተፉበት ፡፡ ፊቴን አይቶ ፡ የሚድን ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ በተናገረ ፡ በጌታ ችን ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ተፉበት ፡፡

፲፮ ፤ እሱ ፡ ግን ፡ ምራቃቸውን ፡ ተጸይፎ ፡ ፊቱን ፡ አልመለሰም ፡፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ የሚያጸይፍ ፡ ምራቅን ፡ በፊቱ ፡ ላይ ፡ በመቀበሉ ፡ በኃጢአት ፡ የጠ ቋቈረና ፡ የኃጢአት ፡ ቅባት ፡ የተቀባ ፡ ፊታችንን ደስ ፡ በሚያሰኝ ፡ ቅባቱ ፡ ብሩህ ፡ ያድርገው ፡፡

፲፯ ፤ ራሱንም ፡ በበትር ፡ መቱት ፡ ጉንጮቹንም ፡ መቶ ፡ ሃያ ፡ ጊዜ ፡ በጥፊ ፡ መቱት ፡፡ በጥፊና ፡ በበትር ከመመታቱ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ራሱም ፡ ጉንጮ ቹም ፡ ቈሰሉ ፡፡ በራሱም ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ቍስሎች ፡ ታላላቆች ፡ ሰባ ፡ ሁለት ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡፡ ዐይኖ ቹም ፡ አፍንጮቹም ፡ የደም ፡ ምንጭ ፡ ሆኑ ፡፡

፲፰ ፤ የያዙትም ፡ ሰዎች ፡ በጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይዘብቱበት ፡ ዘመር ፡፡ ፊቱን ፡ በጨርቅ ቀዳድ ፡ ሸፍነው ፡ እየደበደቡ ፡ ክርስቶስ ፡ የመታህ ማነው ፡ ተናገር ፡ ይሉት ፡ ነበር ፡፡ ሌላም ፡ ብዙ ፡ ብዙ ፡ ስድብ ፡ ይሰድቡት ፡ ነበር ፡፡

## አምስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፡ ጴጥሮስም ፡ ከውጭ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ አንዲት ፡ ብላቴና ፡ መጥታ ፡ አንተም ፡ ከገሊላው ሰው ፡ ከኢየሱስ ፡ ጋራ ፡ ነበርክ ፡ አለችው ። ይኽን የምትይውን ፡ ሰው ፡ እኔ ፡ አላውቀውም ፡ ብሎ ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ ካደ ።

፪ ፡ ወደ ፡ ደጅ ፡ ወጥቶ ፡ ሳለ ፡ ሌላይቱ ፡ ብላቴና ፡ አገኛችው ፡ ከዚያም ፡ ለቆሙ ፡ ሰዎች ፡ ይህም ፡ ከናዝሬቱ ሰው ፡ ከኢየሱስ ጋራ ፡ ነበር ፡ ብላ ፡ ነገረቻቸው ። ይኽን ፡ ሰው ፡ አላውቀውም ፡ ብሎ ፡ እየማለ ፡ ካደ ።

፫ ፡ ጥቂት ፡ ቆይቶም ፡ ሳሉ ፡ ከዚያ ፡ የቆሙ ፡ ሰዎች መጥተው ፡ ጴጥሮስን ፡ አንተም ፡ ዕውነት ፡ የእሱ ፡ ወገን ፡ ነህ ፡ በነገርህም ፡ ትታወቃለህ ፡ አሉት ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ይኽን ፡ ሰው ፡ አላውቀውም ፡ ብሎ ፡ እራሱን ፡ እየረገመ ፡ ማለ ። ሁለተኛም ፡ ዶሮ ፡ ጮኸ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ተመልሶ ፡ ጴጥሮስን ፡ አየው ። ጴጥሮስም ፡ ዶሮ ፡ ሳይጮህ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ትክደኛለህ ፡ ብሎ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ አስቦ ፡ ሂዶ ፡ ያለቅስ ፡ ጀመር ።

፬ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ የጴጥሮስን ፡ የመጸጸቱን ፡ ልቅሶ ፡ ተቀብሎ ፡ ሠላሳውን ፡ አንድ ፡ እያለ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ይቅር ፡ አለው ። የመንግሥተ ሰማያትንም ፡ መክፈቻዎች ፡ ሰጠው ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ቸር ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ነውና ።

## ስድስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ጌቶቼ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፤ አደራ ፡ እላችኋለሁ ። እመቤቴ ፡ ማርያም ፡ አንች ንም ፡ እማፀናለሁ ፡ እማልዳለሁ ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በነፍሱና ፡ በሥጋው ፡ በተቀበ ላቸው ፡ መከራዎች ፡ ሁሉ ።

፪ ፤ ሁለተኛም ፡ በመቸንከሩም ። የእሾህ ፡ አክሊል ተቀዳጅቶ ፡ በመስቀሉ ። በሞቱም ፡ ወደ ፡ ሲኦልም በመውረዱ ። በጦር ፡ በመወጋቱ ፡ በመቀበሩ ። ኃጢ አቴን ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ ትሉኝ ፡ ዘንድ ። ከኃጢአትም ሁሉ ፡ ፍዳ ፡ ታድኑኝ ፡ ዘንድ ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

## የማክሰኞ ፡ ተአምር ።

፩ ፤ ወንጌል ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያደረገው ፡ ተአምር ፡ ይህ ፡ ነው ።

፪ ፤ በቅፍርናሆም ፡ ልጁ ፡ የታመመበት ፡ የንጉሥ ወገን ፡ የሚሆን ፡ አንድ ፡ ሹም ፡ ነበር ፡ እርሱም ጌታ ችን ፡ ኢየሱስ ፡ ከይሁዳ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ እንደመጣ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ልጁ ፡ ለሞት ፡ ቀርቦ ፡ ነበርና ፡ ያድንለት ዘንድ ፡ እንዲወርድ ፡ ወደርሱ ፡ ሄዶ ፡ ለመነው ።

፫ ፤ ጌታችንም ፡ ኢየሱስ ፡ ተአምርና ፡ ምልክት ካላየህ ፡ አታምንምን ፡ አለው ።

፬ ፤ ያም ፡ የንጉሥ ፡ ባሪያ ፡ ልጄ ፡ ሳይሞት ፡ ፈጥነህ ፡ ውረድልኝ ፡ አለው ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ልጅህ ፡ ድኖልሃል ፡ ሂድ ፡ አለው ።

፳ ፡ የም ፡ ሰው ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ በነገረው ቃል ፡ አምና ፡ ሄደ ፡ ሲወርድም ፡ ብላቴኖች ፡ ተቀ ብለው ፡ ልጅህስ ፡ ድኗል ፡ አሉት ። አይሁድ ፡ ግን አዳኝ ፡ ክርስቶስን ፡ ደረቱን ፡ ልቡን ፡ ከሆዱ ፡ ጋራ ፡ መቱት ።

## የማክሰኞ ፡ አርኬ ።

፩ ፡ የመሴፋ ፡ ሰው ፡ ከሚሆን ፡ ከሳሙኤል ፡ ዘመን ጀምሮ ፡ የናቁህ ፡ አይሁድ ፡ በራስህ ፡ ጠጉርና በገመድ ፡ እየሳቡ ፡ ከሐና ፡ ወደቀያፋ ፡ የወሰዱህ ፡ አልፋ ፡ ሆይ ። ለዘለፋ ፡ መጥቶ ፡ ለተስፋ ፡ ለዘለፋ መጥቶ ፡ ለተስፋ ፡ በቆመ ፡ ጊዜ ፡ መስቀልህ ፡ ተስፋ ይሁነኝ ፡ እንጂ ፡ ዘለፋ ፡ አይሁንብኝ ።

፪ ፡ ከንድ ፡ ከወሰናቸው ፡ ከሁለቱ ፡ ክንዶችህ ፡ ጋራ ፡ የተዋረደች ፡ የሆነች ፡ የአንገትህን ፡ ሥር ፡ በመምታትና ፡ በማሠር ፡ መከራ ፡ ያጸኑብህ ። ፍጹም ኃጢአትም ፡ ብሠራ ፡ በየቀኑ ፡ ሁሉ ፡ ቸርነትህ ፡ ይከተለኝ ።

፫ ፡ ሆ ድ ህ ፡ ቸርነትን ፡ የተመላው ፡ ደረትህም ፡ ሰውን ፡ የሚያጸና ፡ ነው ፡ በከበረ ፡ ደምህና ፡ በፊትህ ወዝ ፡ መከራ ፡ እስኪያጸኑብህ ፡ ውሳጣዊ ፡ የሚሆን ፡

ንዋየ ፡ ውስጥህን ፡ የመቱህ ። ከተሠወረ ፡ ኃጢአቴ አንጻኝ ፡ ለኔ ፡ ለባሪያህም ፡ ከልዩ ፡ ነገር ፡ ራራልኝ።

፬ ፤ እንደ ፡ በደለኛ ፡ አይሁድ ፡ በመቱህ ፡ ጊዜ ያለቀጣ ፡ የጭኖች ፡ ብትርን ፡ የታገሥህ ፡ የሸፍቶ ችን ፡ መስቀል ፡ የተሸከምህ ፡ ከበደል ፡ የተራቆትህ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤ አቤቱ ፡ የቀይ ፡ እባብ ፡ ሠራዊ ቶች ፡ እንዳይመጡብኝ ፡ በኃይልህ ፡ እግራውቸን ፡ እንደ ፡ እባብ ፡ እግር ፡ አድርግ ።

፭ ፤ ድብደባን ፡ ካበዙብህ ፡ በኋላ ፡ አይሁድ ፡ በተክል ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ ሠላሳ ፡ ስድስት ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ እግሮችህን ፡ የመቱህ ። በቀኝና ፡ በግራ ፡ ዐረፍትን ፡ ሠርተህ ፡ በእሳታዊ ፡ ባሕር ፡ መካከል ፡ ጐዳናን ፡ ስጠኝ ።

፮ ፤ በሥጋው ፡ ጥቁር ፡ ከሆነ ፡ ከብዝት ፡ እራስህ ጠጉር ፡ ጋራ ፡ ግሩም ፡ የሆነ ፡ የፊትህን ፡ ጽሕም ፡ የነጩህ ። በተቀበልከው ፡ መከራ ፡ የበሽተኞች ፡ ሕይወት ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤ በጣፈጠ ፡ በጐንህ ፡ ደም ነፍሴን ፡ አሳድር ፡ ነፍሴ ፡ በደም ፡ ታድራለችና ።

፯ ፤ ግፍን ፡ የማይፈሩ ፡ አይሁድ ፡ ረግጠው ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ በጐዳና ፡ መካከል ፡ የጣሉህ ። ሊቀ ፡ ካህናትን ፡ በውጭ ፡ በጎ ፡ በተናገርከው ፡ ጊዜ ፡ በነ ገርህ ፡ እንዴት ፡ ተቈጣ ፡ ማልኮስስ ፡ ፊት ህን እንዴት ፡ ጸፋ ።

፰ ፤ በፈንታው ፡ ወደ ፡ ተሾመ ፡ ወደ ፡ አማቹ ፡ ቀያፋ ፡ በሐና ፡ ትእዛዝ ፡ ዳግመኛ ፡ የወሰዱህ ፡

መለኮትህ ፡ በሥጋ ፡ ለምን ፡ ታመመ ፡ መለኮት
ህስ ፡ በመቃብር ፡ ውስጥ ፡ ለምን ፡ ተኛ ። ዓለም ፡
አንተን ፡ ምንም ፡ በከንቱ ፡ ባልወርስ ።

፱ ፤ ከጠጉርህ ፡ እጅግ ፡ የበዙ ፡ ጠላቶችህ ፡
በግፍ ፡ በሕይወትህ ፡ የሞት ፡ ፍርድን ፡ የፈረዱብህ
በሰው ፡ መከራ ፡ የተፈተንህ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤ ክረም
ትን ፡ ባገባህ ፡ ጊዜ ፡ በጋንም ፡ በጊዜው ፡ ባመጣ
ኸው ፡ ጊዜ ፡ በምሕረትህ ፡ ጠብቀኝ ።

፲ ፤ ፊትህን ፡ ለመመታት ፡ የሰጠህ ፡ ከኀፍረት ፡
ምራቅም ፡ ፊትህን ፡ ያልመለስህ ፡ ተማሪዎች ፡ በመ
ከራህ ፡ ጊዜ ፡ ጥለውህ ፡ የሸሹ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤
በጭቃ ፡ የተሠራ ፡ ቤትን ፡ ሌቦች ፡ እንዳይቆፍ
ሩት ፡ በመስቀልህ ፡ ጠብቀው ።

፲፩ ፤ ጠላቶች ፡ በጣታቸው ፡ ዐይንህን ፡ የሸፈኑህ
በብትር ፡ መትተው ፡ ያቆሰሉህ ፡ ዳግመኛም ፡ በግ
ዞት ፡ ቤት ፡ እጅና ፡ እግርህን ፡ የታሠርህ ፡ ቸር ፡ ፈጣ
ሪዬ ፡ በለመለመች ፡ አገርና ፡ ባማረች ፡ ምድር ፡ ነፍ
ሴን ፡ አሳርፋት ። ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡
ኀጢአቴን ፡ አስተሥርይልኝ ፡ አሜን

## የረቡዕ ፡ ድርሳን ፡ ማሕየዊ ።

## አንደኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ
በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ በዕውነት ፡ አምነን ፤
ለዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ቤዛ ፡ የሚሆን ፡ ዓለሙን ፡ ሁሉ

የሚያድን ፡ የመድኃኔ ፡ ዓለምን ፡ የሞቱንና ፡ የመከራውን ፡ ነገር ፡ የሚናገር ፡ በዕለተ ፡ ረቡዕ ፡ የሚነበብ ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ።

፩ ፤ በነጋም ፡ ጊዜ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ይገድሉት ፡ ዘንድ ፡ የካህናቱ ፡ አለቆች ፡ ጻሐፊዎችና ፡ መምራን ፡ ተማከሩ ። ከሥር ፡ ቤት ፡ አውጥተው ፡ በጽኑ ፡ ገመድና ፡ ሰንሰለት ፡ አስረው ፡ ወደሚፈረድበት ፡ አደባባይ ፡ ወሰዱት ። ከቀያፋ ፡ ቤት ፡ እስከ ፡ ፍርድ ፡ አደባባይ ፡ ድረስ ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ በተንጠፈ ፡ ድንጊያ ፡ ለይ ፡ ጐተቱት ።

፪ ፤ ያለርኅራኄ ፡ መቱት ። ብዙ ፡ በደበደቡትም ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞ ፡ ከምድር ፡ ላይም ፡ ወደቀ ። ዳግመኛም ፡ እየደበደቡ ፡ ከፊታቸው ፡ አቆሙት ። እሱ ፡ ግን ፡ መቆም ፡ የማይቻለው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ወደቀ ። እየደበደቡም ፡ በውነት ፡ ክርስቶስ ፡ አንተ ፡ እንደ ፡ ሆንክ ፡ ግልጸህ ፡ ንገረን ፡ አሉት ።

፫ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ አላምን ፡ አላችሁ ፡ እንጂ ፡ እኔስ ፡ ነገርኋችሁ ። ብጠይቃችሁም ፡ አትመልሱልኝም ፡ ወይም ፡ አትተውኝም ። ነገር ፡ ግን ፡ እላችኋለሁ ፡ እንግዲህ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ቀኝ ፡ ተቀምጦ ፡ ታዩታላችሁ ።

፬ ፤ ሁሉም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ አንተ ፡ ነህን ፡ አሉት ። ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ እኔ ፡ እንደሆንኩ ፡ እናንተ ፡ ትላላችሁ ፡ አላቸው ። ስለሱም ፡ ምስክር ፡ ለምን ፡ ትፈልጋላችሁ ፡ እነሆ ፡ እኛ ፡ ባንደበቱ ፡

ሲናገር ፡ ሰማነው ፡ አሉ ። ሁሉም ፡ በአንድነት ፡
ተነሥተው ፡ እየዶበዶቡ ፡ ወደ ፡ ጲላጦስ ፡ ወሰዱት ።
፳ ፤ ጲላጦስም ፡ ወደ ፡ እነሱ ፡ ወጥቶ ፡ ይሄን ፡ ሰው
ወደኔ ፡ ያመጣችሁበት ፡ ነገሩስ ፡ በይሉስ ፡ ምን
ድር ፡ ነው ፡ አላቸው ። አይሁድም ፡ መልሰው ፡
ክፉ ፡ አድራጊስ ፡ ባይሆን ፡ ወዳንተ ፡ ባላመጣነ
ውም ፡ ነበር ፡ አሉት ። ጲላጦስም ፡ እናንተ ፡ እንደ
ሕጋችሁ ፡ ፈርዳችሁ ፡ ቅጡት ፡ አላቸው ። አይሁድም
ማንንም ፡ ልንገድል ፡ እኛ ፡ አይገባንም ፡ አሉ ። በማ
ናቸው ፡ ሞት ፡ ይሞት ፡ ዘንድ ፡ ሰላለው ፡ ለነሱ
ሲያመለክታቸው ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ የተናገረው
ነገር ፡ ይደርስ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ነው ። የሚሞ
ተውም ፡ ተሰቅሎ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በድንጊያ ፡ ተወ
ግሮ ፡ አይደለምና ። ያን ፡ ጊዜውን ፡ አይሁድ ፡ በጌ
ታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ላይ ፡ በሌባና ፡ በወንበዴ ፡
ፍርድ ፡ ፈረዱበት ።
፳፩ ፤ ያስያዘውም ፡ ይሁዳ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ እንደ
ተፈረደበት ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ተጸጸቶ ፡ ከሕዝቡ ፡ መም
ህራኖችና ፡ ከካህናቱ ፡ አለቆች ፡ የተቀበለውን ፡
ሠላሳ ፡ ብር ፡ መልሶ ፡ ሰጣቸው ። ይህን ፡ ዕውነተኛ
ሰው ፡ ያስገደልኩ ፡ ንጹሕ ፡ ደሙን ፡ ያፈሰስኩ ፡ እኔ
በድያለሁ ፡ አላበጀሁም ፡ ብሎ ፡ መለሰ ። እኛ ፡ ካንተ
አንተ ፡ ከኛ ፡ ምን ፡ አለህ ፡ ለራስህ ፡ ዕወቅ ፡ አሉት ።
ይህንንም ፡ ብር ፡ በአዳራሹ ፡ በትና ፡ ወደ ፡ ታላቅ ፡
ዕንጨት ፡ ሂዶ ፡ በዕንጨቱ ፡ ላይ ፡ ገመድ ፡ አስሮ ፡

ተሰቀለ ። ነገር ፡ ግን ፡ ያለንስሐ ፡ ተሰቅሎ ፡ እንዳ
ይሞት ፡ ብሎ ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ በቸርነቱ ፡ ዕን
ጨቱን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ አዘነበለው ።

፰ ፤ ይሁዳም ፡ ተሰቅሎ ፡ ባለመሞቱ ፡ ተበሳጭቶ
ወደ ፡ ሌላ ፡ ዕንጨት ፡ ሂዶ ፡ ተሰቀለ ፡ ጌታችን ፡ ኢየ
ሱስም ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ በቸርነቱ ፡ ብዛት ፡ ተሰቅሎ
እንዳይሞት ፡ ዕንጨቱን ፡ አዘነበለለት ። ዕንጨቱ
ንም ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ እንዲናገር ፡ አደረገው ። ዕን
ጨቱም ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ተናግሮ ፡ እንደ ፡ ወንድ
ምህ ፡ እንደ ፡ ጴጥሮስ ፡ ስለኃጢአትህ ፡ ንስሐ ፡ ገብ
ተህ ፡ አልቅስ ፡ አለው ። ጴጥሮስን ፡ ይቅር ፡ እንዳለው
ያንተንም ፡ ኃጢአትህን ፡ ይቅር ፡ ይልሃልና ።

፱ ፤ እምቢ ፡ ብሎ ፡ በብዙ ፡ ጻዕርና ፡ መከራ ፡
ሳይሞት ፡ በሦስተኛው ፡ ዕንጨት ፡ ተሰቅሎ ፡ ዋለ ።
በሠርክም ፡ ጊዜ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ፈቃድ
ዕንጨቱ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ጣለው ። በመከራም ፡
ዐርባ ፡ ቀን ፡ ተቀምጦ ፡ ንስሐ ፡ ሳይገባ ፡ በክፉ
ሞት ፡ ሞተ ። ወደ ፡ ምድር ፡ ወድቆ ፡ ጐኑ ፡
ተቀዶ ፡ አንጀቱ ፡ ወጥቷልና ።

፲ ፤ የካህናቱም ፡ አለቆች ፡ ብሩን ፡ ተቀብለው
ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ልናስገባው ፡ አይገባም ፡
የደም ፡ ዋጋ ፡ ነውና ፡ አሉ ። ተማክረውም ፡ በጌ
ታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ዕውቀት ፡ ለመጻተኛ ፡ መቃ
ብር ፡ ይሁን ፡ ብለው ፡ የአንጠረኛውን ፡ ቦታ ፡ ገዙ
በት ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ለድኆችና ፡ ለእንግዶች

በሕይወታቸውም ፡ በሞታቸውም ፡ አለኝታቸው ፡ ነውና ። ይኸውም ፡ ቦታ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የደም ፡ ቦታ ፡ ሲባል ፡ ኖረ ።

፲፩ ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የተስማሙበት ፡ ክቡር የሆነ ፡ የጌታን ፡ ዋጋ ፡ ፴ ፡ ብር ፡ ተቀበሉ ፡ ብሎ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ የተናገረው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ተፈጸመ ። ለአንጥረኛ ፡ ቦታ ፡ ስጡት ፡ በማለት ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘኝ ፡ እናገራለሁ ፡ ያለውም ፡ ደረሰ ።

፲፪ ፤ አይሁድም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ጲላጦስ ወዳለበት ፡ ቦታ ፡ ወሰዱት ። ሲገባም ፡ አይተው ፡ ከዚያ ፡ ቦታ ፡ ቁመው ፡ የነበሩ ፡ ጦሮች ፡ ሰገዱለት አይሁድ ፡ ግን ፡ ጦሮች ፡ ስለ ፡ ሰገዱለት ፡ ተቆጡ ። ወደ ፡ ጲላጦስም ፡ ዘንድ ፡ ገብተው ፡ በከንቱ ፡ ሐሜታቸው ፡ አሙት ።

፲፫ ፤ ጲላጦስም ፡ የመስገዳቸውን ፡ ነገር ፡ ይረዳ ፡ ዘንድ ፡ ስድስቱ ፡ ጦሮች ፡ ወዳሉበት ፡ ቦታ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ውሰዱት ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ። ጦሮችም በኃይል ፡ እየሳብዋቸው ፡ ሳሉ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ሰገዱለት ። አይሁድም ፡ ይህን ፡ ተአምራት ፡ አይተው ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ መድኃኒተኛ ፡ ሰው ፡ አላየንም ፡ ብለው ፡ ጮኹ ።

፲፬ ፤ ከዚያም ፡ ጲላጦስ ፡ ጦሮች ፡ ወዳሉበት ፡ ቦታ ፡ ወጣ ። በጲላጦስም ፡ ፊት ፡ ለጌታችን ፡ ለኢየሱስ ፡ እሊህ ፡ ጦሮች ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ሰገዱለት ፡ ለጌታ ፡ እንዳይሰግዱለት ፡ ኃይለኞች ፡ ሰዎች ፡ በገ

መድ ፡ ሲሰቧቸው ፡ ከማፈራቸው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ እንደ ፡ አስማተኞች ፡ እንደ ፡ ኢያኔስ ፡ እንደ ፡ ኢያንበሬስ ፡ አስማተኛ ፡ ነው ፡ አሉት ። ከማፈራቸው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ከጲላጦስ ፡ ፊት ፡ ወሰደው ፡ አቁመው ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ አጣሉት ፡ አካሰሱት ።

፲፰ ፤ ለቄሣርም ፡ ግብር ፡ እንዳይሰጡ ፡ ሕዝቡን ሲያስከዳቸውና ፡ ሲከለክላቸው ፡ አገኘነው ፡ እያሉ ። እሱም ፡ የእሥራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ነኝ ፡ ይላል ። የእግዚአብሔርን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አድርጉ ፡ የቄሣርን ፡ ለቄሣር ፡ ስጡ ፡ ካላቸው ፡ በኋላ ፡ ሐሰተኞች ሆነዋልና ። እሱም ፡ ስለ ፡ ትሕትናው ፡ ግብሩን ፡ ከሰጣቸው ፡ በኋላ ፡ ጲላጦስ ፡ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ አንተ ፡ ነህን ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ።

፲፱ ፤ ጌታችንም ፡ መልሶ ፡ እኔ ፡ ንጉሥ ፡ እንደሆንኩ ፡ አንተ ፡ ትላለህ ፡ አለው ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ሰንበትን ፡ የማያከብር ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወገን ፡ ያይደለ ነው ፡ እያሉ ፡ ያጣሉትም ፡ ያካሰሱትም ፡ አሉ ። በሰንበት ፡ ድዉያንን ፡ አዳነ ፤ የዕውራንንም ፡ ዐይን አበራ ፡ የሞቱትንም ፡ ሰዎች ፡ በሰንበት ፡ አስነሣ ። በሥራው ፡ ሁሉ ፡ ሰንበትን ፡ ሻረ ፡ ነው ። እንዲህ ሲያጣሉት ፡ ሲያካስሱት ፡ እሱ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ አልመለሳቸውም ።

፳ ፤ ዳግመኛም ፡ ጲላጦስ ፡ እሊህ ፡ ይህን ፡ ያህል ሲያጣሉህ ፡ ሲያካስሱህ ፡ አትሰማቸውምን ፡ አለው ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ሹሙ ፡ ፈጽሞ ፡ እስኪያደን ቀው ፡ ድረስ ፡ አንዲት ፡ ቃል ፡ ስንኳ ፡ አልመለ ሰም ። በሰንበት ፡ ተአምራት ፡ የሚያደርግ ፡ ጌታ ችን ፡ ግን ፡ አባቱ ፡ በሰንበት ፡ ተአምራት ፡ እንዲያ ደርግ ፡ እሱም ፡ በሰንበት ፡ የታመሙትን ፡ በዕው ነት ፡ አዳናቸው ። የዕውሮቹንም ፡ ዐይን ፡ በሰንበት አበራ ፡ የሞቱትንም ፡ በሰንበት ፡ አስነሣቸው ።

## ሁለተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ባዳራሹም ፡ ውስጥ ፡ እጁ ፡ የደረቀች ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አገኘ ። አይሁድ ፡ ግን ፡ ያጣሉት ፡ ያካስሱት ዘንድ ፡ በሰንበት ፡ ያድነው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብለው ይጠባበቁት ፡ ነበር ።

፪ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ይህን ፡ እጁ ፡ የደረቀ ችውን ፡ ሰው ፡ ተነሥተህ ፡ በመካከላቸው ፡ ቁም አለው ። በሰንበት ፡ በጎ ፡ ማድረግ ፡ አይገባምን ፡ ወይስ ፡ ክፉ ፡ ማድረግ ፡ ሰውን ፡ ማዳንን ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ መግደል ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። ዝም ፡ አሉ ።

፫ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ በዓይኑ ፡ አይቶ እጅህን ፡ ዘርጋ ፡ አለው ። እጁንም ፡ ዘረጋ ፡ ድና ፡ እንደ ፡ ሁለተኛይቱ ፡ ሆነችለት ። ፈሪሳውያንም ፡ ከዚህ ፡ ወጥተው ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ይገድ ሉት ፡ ዘንድ ፡ ከሄሮድስ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ተማከሩ ።

፬ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ወደብ ፡ ሄደ ። ያደረገውንም

ተአምራቱን ፡ ሰምተው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተከተሉት ። የታመሙትንም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ አዳናቸው ። ነገር ግን ፡ እንዳትገልጹ ፡ ብሎ ፡ አስጠነቀቃቸው ። አይሁድ ፡ ግን ፡ ሰንበት ፡ ሻሪ ፡ ነው ፡ አሉት ።

## ሦስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፡ ከወደፊቱ ፡ ሆዱ ፡ ያበጠ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ጸሐፍት ፡ ፈሪሳውያንን ፡ በሰንበት ፡ ሰው ፡ ማዳን ፡ ይገባልን ፡ ወይስ አይገባም ፡ አላቸው ። እነሱ ፡ ግን ፡ ዝም ፡ አሉ ።

፪ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ይህን ፡ ሆዱ ፡ ያበጠውን ፡ ሰው ፡ ይዞ ፡ በሰንበት ፡ አድኖ ፡ ሰደደው። አይሁድ ፡ ግን ፡ ሰንበት ፡ ሻሪ ፡ አደረጉት ። ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ጋኔን ፡ ይዞ ፡ የሚጥላት ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ነበረች ። እሷም ፡ ጐባጣ ፡ ነበረች ፡ ፈጽሞም ፡ መቆም አትችልም ።

፫ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ባያት ፡ ጊዜ ፡ አንቺ ፡ ሴት ፡ ከደዌሽ ፡ ድነሻል ፡ ብሎ ፡ በእጁ ፡ዳሰሳት። ድናም ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ ሄደች ፡ እግዚአብሔርንም አመሰገነች ፡ አይሁድ ፡ ግን ፡ እሱን ፡ ሰንበት ፡ ሻሪ ፡ ነው ፡ አሉት ።

## ዐራተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ ከዚያ ሲያልፍ ፡ ዕዉር ፡ ሆኖ ፡ የተወለደ ፡ ሰው ፡ አገኘ ። ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ መምህር ፡ ሆይ ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ ዕውር ፡ ሆኖ ፡ የተወለደ ፡ ብራሱ ፡ ኃጢአት ፡ ነውን ወይስ ፡ በዘመዶቹ ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ።

፪ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሥራ በሱ ፡ ላይ ፡ ይገለጽ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ዘመዶቹም ፡ እሱም ፡ አልበደሉም ፡ አላቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ብርሃን ፡ ሳለ ፡ ያባቴን ፡ ሥራ ፡ እሠራ ፡ ዘንድ ለኔ ፡ ይገባኛል ፡ አላቸው ። አንድ ፡ ሰው ፡ ስንኳ ፡ ሥራ ፡ ሊሠራበት ፡ የማይቻለው ፡ ሌሊት ፡ ይመጣልና ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሳለሁ ፡ የዓለም ፡ ብርሃን ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

፫ ፤ ይህንም ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ በምራቁ ፡ አፈር ፡ ለውሶ ፡ ዐይኑን ፡ ቀብቶ ፡ ሂደህ ፡ በፈሳሽ ፡ ውሃ ፡ ታጠብ ፡ አለው ። ሂዶም ፡ ታጠበ ፡ እያየም ፡ ተመለሰ ። አይሁድ ፡ ግን ፡ ሰንበት ፡ ሻሪ ፡ አደረጉት ።

## አምስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ በሰንበት ፡ ወደ ፡ አልዓዛር ፡ መቃብር ፡ እያለቀሰ ፡ ሂደና ፡ ከመቃብሩ ፡ አፍ ፡ ያለውን ፡ ደንጊያውን ፡ አንሡ ፡ አላቸው ።

፪ ፤ የሞተውም ፡ ሰው ፡ እኅት ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ዛሬ ዐራተኛ ፡ ቀኑ ፡ ነውና ፡ ፈጽሞ ፡ ሸቷል ፡ አለችው ። ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ብታምኚስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ተአምራቱን ፡ (ጌትነቱን ፡) ታያለሽ ፡ አላልኩሽምን አላት ። ደንጊያውን ፡ ከመቃብሩ ፡ ላይ ፡ አንሡት ።

፫ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ዐይኖቹን ፡ ወደ፡ሰማይ አቅንቶ፡ አባቴ ፡ ልመናዬን ፡ ሰምተኸኛልና ፡ አመ ሰግንሃለሁ ። ዘወትርም ፡ እንደምትሰማኝ ፡ ዐውቃለሁ አለ ። እሊህ ፡ የቆሙት ፡ ሰዎች ፡ አንተ ፡ እንደ ፡ ላከኝ ፡ ያምኑ ፡ ዘንድ ፡ እንዲህ ፡ አልኩ ፡ እንጂ ። ይህን ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ አልዓዛር ፡ አልዓዛር ፡ ና፡ወደውጭ ውጣ ፡ ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ቃል ፡ አሰምቶ ፡ ተናገረ ።

፬ ፤ ይኸውም ፡ የሞተው ፡ ሰው ፡ እጁም ፡ እግሩም ታሥሮ ፡ እንደ ፡ ተገነዘ ፡ ፊቱም ፡ በልብስ ፡ እንደ ተጠቀለለ ፡ ከመቃብር ፡ ውስጥ ፡ ወጣ ።

፭ ፤ ጌታችንም ፡ መግነዙን ፡ ፈትታችሁ ፡ ተዉት ይሂድ፡ አላቸው ። ሄደም ። እንዲህ ፡ ሙታንን ፡ የሚ ያስነሣ ፡ የታመሙትንም ፡ የሚያድን ፡ አምላክ ፡ ከጲ ላጦስ ፡ ፊት ፡ አቁመው ፡ አጣሉት ፡ አካሰሱት ።

## ስድስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ እንዲህም ፡ ካጣሉት ፡ ካካሰሱት ፡ በኋላ ፡ ሕዝቡንና ፡ ሊቃነ ፡ ካህናቱን ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ ላይ ያገኘሁበት ፡ በደል ፡ የለም ፡ አላቸው ።

፲ ፤ ከገሊላ ፡ ጀምሮ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ በይሁዳ ፡ አውራጃ ፡ እያስተማረ ፡ ሕዝቡን ፡ ያውካል ፡ እያሉ ፡ ሁሉም ፡ ጮሁ ።

፲፩ ፤ ጲላጦስም ፡ ገሊላ ፡ ሲሉ ፡ ሰምቶ ፡ የገሊላ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ የገሊላን ፡ ሰዎች ፡ ከሄሮድስ ፡ ግዛት ፡ እንደሆነ ፡ ዐውቆ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ሄሮድስ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሳለ ፡ ወደ ፡ ሄሮድስ ፡ ላከው ፡

፲፪ ፤ በላከውም ፡ ጊዜ ፡ **ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡** ከመ ገዛት ፡ ነጻ ፡ ሲሆን ፤ በትሕትና ፡ ሄደ ። እሱ ፡ የም ድራውያንና ፡ የሰማያውያን ፡ ገዥዎች ፡ ገዥ ፡ ሲሆን ። የምድራውያንና ፡ የሰማያውያን ፡ ጌቶች ፡ ጌታ ፡ ሲሆን የሰማያዊ ፡ ንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ሲሆን ፤ እርሱ ፡ የምድ ርና ፡ የሰማይ ፡ ንጉሥ ፡ ሲሆን ። በደቀ ፡ መዝ ሙሩ ፡ በጴጥሮስ ፡ እጅ ፡ ከዓሣ ፡ ሆድ ፡ ወርቅ ፡ አውጥቶ ፡ ግብር ፡ ለሚቀበሉ ፡ ሰዎች ፡ ግብርን ፡ በትሕትና ፡ ሰጠ ።

፲፫ ፤ ሄሮድስም ፡ **ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡** ባየው ፡ ጊዜ ፡ የተወደደ ፡ ደም ፡ ግባቱን ፡ መልኩንና ፡ ብሩህ ፡ የሆነ ፡ ፊቱን ፡ ከማየቱ ፡ የተነሣ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አለው ። ብዙ ፡ ሥራውን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ከብዙ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ሊያየው ፡ ይወድ ፡ ነበርና ። የሚሠራ ውንም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ሊያይ ፡ ይወድ ፡ ነበርና ። ብዙ ፡ ነገርም ፡ መረመረው ፡ ጠየቀው ፡ **ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡** ግን ፡ ቃል ፡ አልመለሰለትም ።

፮ ፡ ጸሐፍትና ፡ የካህናት ፡ አለቆችም ፡ ዝም ፡
ስላለ ፡ ቁመው ፡ ያጣሉት ፡ ያካሰሱት ፡ ነበረ ። ሄሮ
ድስና ፡ ብላቴኖቹ ፡ ክፉ ፡ ነውሳ ፡ እያሉ ፡ ዘበቱበት ።
ጌታችን ፡ ኢየሱስንም ፡ ሄሮድስ ፡ እንዳዘዛቸው ፡
ብዙ ፡ ገረፉት ። ሥጋው ፡ እየተቆራረጠ ፡ ደሙ ፡
እንደ ፡ ውሃ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ፈሰሰ ።

፯ ፡ ሄሮድስም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ አቃለለው
በመገረፉም ፡ ያዘነ ፡ የተከዘ ፡ ሆነ ፡ ጌታችን ፡ ኢየ
ሱስንም ፡ ቀይ ፡ ልብስ ፡ አለበሱት ።

፰ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ሞት ፡ ይገባዋል ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡
ጲላጦስ ፡ ላከው ። ጠላቱ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከቀድሞ ፡
ጀምሮ ፡ ሊገድለው ፡ ይወድ ፡ ነበርና ። ፈሪሳውያን
እንደ ፡ ነገሩት ፡ ሄሮድስ ፡ ሊገልህ ፡ ይፈልግሃልና ፡
ከዚህ ፡ ሂድ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

፱ ፡ ጌታችን ፡ ግን ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ እንዳይገድ
ለው ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ በጊዜው ፡ እንዲሞት ፡ ዐውቆ ፡
ይህን ፡ ቀበሮ ፡ ሄሮድስ ፡ ሂዳችሁ ፡ እንዲህ ፡ በሉት
ብሎ ፡ ነገራቸው ። እነሆ ፡ ጋኔን ፡ አወጣለሁ ፡
ዛሬም ፡ ነገም ፡ሕይወትን ፡ እሰጣለሁ ፡ በ፫ኛው
ውም ፡ ቀን ፡ ሥራዬን ፡ ፈጽሜ ፡ እሄዳለሁ ፡ በሉት
አላቸው ። ለመምህር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እንጂ ፡ ከኢየ
ሩሳሌም ፡ ውጭ ፡ ሊሞት ፡ አይገባውምና ።

፲ ፡ በዚችም ፡ በመከራው ፡ ቀን ፡ የፍቅርና ፡ የአ
ርቅ ፡ ቀን ፡ የይቅርታ ፡ ቀን ፡ ኃጢአት ፡ የሚሠረ

ይበት ፡ ቀን ፡ የሕይወትና ፡ የደኅንነት ፡ ቀን ፡ ናትና ከቀድሞ ፡ ጀምሮ ፡ ጸብ ፡ ክርክር ፡ የነበራቸው ፡ ጲላጦስና ፡ ሄሮድስ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ተፋቀሩ ።

፲፭ ፤ ጲላጦስም ፡ ካደባባይ ፡ ገብቶ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ጠርቶ ፡ የአይሁድ ፡ ንጉሣቸው ፡ አንተ ፡ ነህን ፡ አለው ። ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ መልሰ ፡ ይህን ፡ የምትናገረው ፡ ከልብህ ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ነገሩህን ፡ አለው ።

፲፮ ፤ ጲላጦስም ፡ እኔ ፡ አይሁዳዊ ፡ ነኝን ፤ ወገኖችህ ፡ የካህናት ፡ አለቆችም ፡ ወደኔ ፡ ያመጡህ ፡ አይደለምን ፡ ምን ፡ ላድርግህ ፡ አለው ። ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ መንግሥቴስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ አይደለችም ብሎ ፡ መለሰ ። መንግሥቴስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ቢሆን አይሁድ ፡ ይዘው ፡ ወዳንተ ፡ እንዳያመጡኝ ፡ ብላቴናዎቼ ፡ በተዋጉልኝ ፡ ነበር ።

፲፯ ፤ ዛሬስ ፡ መንግሥቴ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ አይደለችም ። ጲላጦስም ፡ መሆኑን ፡ ንጉሥ ፡ ነሃ ፡ አለው ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ እኔ ፡ ንጉሥ ፡ እንደሆንኩ ፡ አንተ ፡ ትላለህ ፡ አለው ። ስለዚህ ፡ ነገር ፡ በዕውነት ምስክር ፡ እሆን ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ መጥቼ ፡ እመሰክር ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ ሁኜ ፡ ተወልጃለሁ ። ከዕውነት ፡ የተገኘ ፡ ሁሉ ፡ ቃሌን ፡ ይሰማኛል ። ጲላጦስም ፡ ዕውነቱ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ አለው ።

## ሰባተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ጌቶቼ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፤ አደራ
አላችኋለሁ ። እመቤቴ ፡ ማርያም ፡ አንቺንም ፡ እማ
ልድሻለሁ ። ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በነፍሱና ፡
በሥጋው ፡ በተቀበላቸው ፡ መከራዎች ፡ ሁሉ ። በመ
ቸንከሩም ፡ የሾህ ፡ አክሊል ፡ ተቀዳጅቶ ፡ በመሰቀሉ
፪ ፤ በሞቱም ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ በመውረዱ ። በጦር
በመወጋቱ ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በመ
ቀበሩ ። ኀጢአቴን ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ ትሉኝ ፡ ዘንድ ።
ከኀጢአትም ፡ ፍዳ ፡ ሁሉ ፡ ታድኑኝ ፡ ዘንድ ፡ አሜን ።

## የረቡዕ ፡ ተአምር ።

፩ ፤ በቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ እንደ ፡ ነገረ ፡ በሰንበት ፡
ቀን ፡ የተደረገ ፡ ተአምር ፡ ይህ ፡ ነው ።

፪ ፤ ከታመመ ፡ ሠላሳ ፡ ስምንት ፡ ዘመን ፡ የሆነው
አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ እሱን
ባልጋው ፡ ላይ ፡ ተኝቶ ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ ደዌው ፡ እንደ
ዘገየበት ፡ ዐውቆ ፡ ልትድን ፡ ትወዳለህን ፡ አለው ።
፫ ፤ ወደሚጠመቁበት ፡ የሚያወርደኝ ፡ ሰው ፡
የለኝም ። ዘመድም ፡ የለኝም ፡ እንጂ ፡ አዎን ፡ ጌታዬ
እኔስ ፡ ልድን ፡ እወዳለሁ ፡ አለው ። እኔም ፡ በመጣሁ
ጊዜ ፡ ሌላው ፡ ቀድሞኝ ፡ ይወርዳል ።

፩ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ በሰንበት ፡ ተነሥተህ አልጋህን ፡ ተሸክመህ ፡ ሂድ ፡ አለው ። ይህም ፡ ሰው ፡ ድኖ ፡ አልጋውን ፡ ተሸክሞ ፡ ሂደ ። አይሁድግን ፡ ጌታን ፡ ሰንበት ፡ ሻረ ፡ አሉት ።

## የረቡዕ ፡ አርኬ ።

፩ ፡ ሊገድሉህ ፡ ተባብረው ፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ የተማከሩብህ ። በሰው ፡ ፍቅር ፡ ገመድ የተያዝህ ፡ ክርስቶስ ። የቸርነትህ ፡ ነገር ፡ በመናገር አያልቅም ። የትሕትናህም ፡ ምሥጢሩ ፡ ቀዋሚ ፡ ነው

፪ ፡ በነግህ ፡ ከግዞት ፡ ቤት ፡ ያወጡህ ፡ ክርቶስ ፡ ከቀያፋ ፡ ቤት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፍርድ ፡ አደባባይ ፡ በተሳለ ፡ ደንጊያ ፡ ላይ ፡ አይሁድ ፡ የጐተቱህ። በየዕለቱና ፡ በየወሮቹ ፡ ጠብቀኝ ፡ ቸር ፡ እረኛ ፡ አንተ ፡ ነህ እንደ ፡ ምንደኛም ፡ አይደለህምና ።

፫ ፡ ጦሮች ፡ በአይሁድ ፡ ፊት ፡ የመንግሥትህን ገናንነት ፡ ይገልጡ ፡ ዘንድ ፡ በፊትህ ፡ የጦሮች ፡ እራሶች ፡ የሰገዱልህ ፡ ክርስቶስ ፡ ወደ ፡ ጲላጦስ ፡ ቦታ ፡ ባገቡህ ፡ ጊዜ ። አቤቱ ፡ አንድ ፡ ሳይቀር ፡ ዕዳዬን ፡ አጥፋ ። ቍጥሩ ፡ ፈጽሞ ፡ ብዙ ፡ ነውና ።

፬ ፡ ለማጣላት ፡ በጲላጦስ ፡ ፊት ፡ ያቆሙህ ፡ የናትህ ፡ ዘመዶች ፡ በመፈራረቅም ፡ የሰደቡህ ፡ ልጣድህ ፡ ኃጢአት ፡ ማስተሥረይ ፡ የሆን ፡ ክርስቶስ ፡

በገቢርና ፡ በኀልዮ ፡ ብበድል ፡ የኔ ፡ የባሪያህን ፡ ኃጢአት ፡ አታስብ ።

፭ ፤ ሊቃነ ፡ መላእክት ፡ በፍርሃት ፡ በፊትህ ፡ ሲቆሙ እንደ ፡ ባሪያ ፡ በጲላጦስ ፡ ፊት ፡ የቆምህ ። እኔ ፡ ባሪያህ ፡ የዚህ ፡ የግፍህን ፡ ልክ ፡ ባሰብሁት ፡ ጊዜ ። ክርስቶስ ፡ ትሕትናህ ፡ ዕፁብ ፡ ነው ፡ ዕፁብ ፡ ነው ። ትዕግሥትህም ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነው ፡ አልሁ ።

፮ ፤ እውነተኛ ፡ ሰው ፡ ስትሆን ፡ አይሁድ ፡ የገደሉህ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አባት ፡ ብታደርግ ፡ በንጉሥ ፡ ቄሣር ፡ በደል ፡ ያጣሉህ ። በደሌ ፡ ከሥጋዬ ፡ በአፍአ ፡ ነውና ፡ በደለኛ ፡ በሚሆን ፡ በሥጋዬ ፡ አቤቱ ፡ አንተ ፡ አስተሥርይልኝ ።

፯ ፤ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤ ሁለቱ ፡ የካህናት ፡ አለቆች ከመረመሩህ ፡ በኋላ ፡ አይሁድ ። የንጉሥ ፡ ወንጀለኛ ነው ፡ ባሉህ ፡ ጊዜ ፡ ሄሮድስና ፡ ጲላጦስ ፡ የመረመሩህ ። ከክርስቲያን ፡ ወንድሞቼ ፡ እኔ ፡ ትንሽ ፡ ነኝና እኔን ፡ ባሪያህን ፡ በሦስተኛ ፡ ሰማይ ፡ አንግሠኝ ።

፰ ፤ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤ በልባቸው ፡ ከራቁ ፡ ዘንድ አንተን ፡ ከማክበር ፡ ተለይተው ፡ የሄሮድስ ፡ ወታደሮች ፡ በትሕትናህ ፡ የዘበቱብህ ፡ ቍጥሩን ፡ ማወቅ እስኪሳናቸው ፡ ድረስ ፡ አይሁድ ፡ የገረፉህ ። አንተን ለመያዝ ፡ በተጉ ፡ ጊዜ ፡ የአይሁድ ፡ ወገኖች ፡ እንደ ወደቁ ፡ ጠላቶቼ ፡ እንደነሱ ፡ የኋሊት ፡ ይውደቁ ።

፱ ፤ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤ ፊትህን ፡ በማየት ፡ ልቡ ፡ ደስ ፡ ካለው ፡ በኋላ ፡ ሄሮድስ ፡ የመገረፍህን ፡ ፍርድ

ያለ ፡ አግባቡ ፡ የፈረደብህ ፡ ቀይ ፡ የሆነ ፡ የምልክት ልብስን ፡ ያለበሱህ ። አቤቱ ፡ ኃጢአቴ ፡ በዝቷልና ቀድሞ ፡ ልብህ ፡ በ ሰው ፡ እንደ ፡ ተጸጸተ ፡ አት ጸጸትብኝ ።

፲ ፤ ስቅለትን ፡ ከወደደ ፡ በኋላ ፡ ከሚያስፈራ ሥቃይ ፡ ሞት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ያዳንኸው ፡ አቤቱ ፡ የኃጥአን ፡ ምሕረት ፡ ሥራህ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ተገ ለጠ ። ማን ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ካዳንከው ፡ በኋላ ፡ ሰይ ጣን ፡ ይሁዳ ፡ በክፉ ፡ አሟሟት ፡ ሙቷልና ።

፲፩ ፤ የካህናት ፡ አለቆችና ፡ ወገኖችህ ፡ አሲዘው ሃልና ፡ መማለጃ ፡ በመውደድ ፡ ምን ፡ ልሥራልህ ። መሥፍን ፡ እሊህ ፡ ወደ ፡ መመስገኛህ ፡ ቦታ ፡ መር ተው ፡ ይወስዱኝ ፡ ዘንድ ፡ ቸርነትህንና ፡ ብርሃንህን ላክ ፡ አለህ ።

የኔን ፡ የባ ሪያህን ፡ ኃጢአቴን ፡ አስተሥርይልኝ ፡ አሜን ።

## የሐሙስ ፡ ድርሳን ፡ ማሕየዊ ።
## አንደኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ በማመን ፡ ዓለምን ፡ ሁሉ ፡ የሚያድን ፡ ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ የሚታደግ ፡ የክርስቶስ ፡ የመከራውንና ፡ የሞቱን ፡ ነገር ፡ የሚናገር ፡ በዕለተ ፡ ሐሙስ ፡ የሚነበብ ፡ የሚጸለይ ፡ ድርሳን ፡ ይህ ፡ ነው ።

፪ ፤ ሹሙ ፡ በየበዓሉ ፡ ከታሠሩት ፡ የወደዱትን አንዱን ፡ ያድንላቸው ፡ ዘንድ ፡ ለሕዝቡ ፡ ልማድ ፡

ነበራቸው ። በዚያን ፡ ወራት ፡ የወንበዶች ፡ አለቃ
የሚሆን ፡ በርባን ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ እሥረኛ ፡ ነበር
ወንበዴነቱንም ፡ ሁሉ ፡ ያውቀዋል ።

፫ ፡ ሁሉም ፡ ተሰብስበው ፡ ሳሉ ፡ ጲላጦስ ፡ ሕዝ
ቡን ፡ ማንን ፡ ላድንላችሁ ፡ ትወዳላችሁ ። በርባንን
ነው ፡ ወይንስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚሉት ፡ ኢየሱስን ፡ ነው
አላቸው ። ቀንተው ፡ እንዳሲያዙት ፡ ያውቃልና ።

፬ ፡ ጲላጦስም ፡ መኳንንቱንና ፡ የካህናቱን ፡ አለ
ቆች ፡ ዳግመኛ ፡ ጠርቶ ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ወን
ጀለኛ ፡ ይዛችሁ ፡ ወደኔ ፡ አመጣችሁት ። እነሆ ፡
በፊታችሁ ፡ መረመርኩት ፡ በከሰሳችሁበትም ፡ ነገር
በደል ፡ አላገኘሁበትም ፡ አላቸው ። ወደ ፡ ሄሮ
ድስም ፡ ላኩት ፡ እሱም ፡ መልሶ ፡ ወደኔ ፡ ላከው ።
እነሆ ፡ እሱም ፡ ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ የሠራው ፡
ወንጀል ፡ የለም ፡ ገርፌ ፡ ልተወው ፡ አላቸው ።

፭ ፡ የካህናቱ ፡ አለቆች ፡ ግን ፡ ኢየሱስን ፡ ስቀል
ልን ፡ በርባንን ፡ አድንልን ፡ ብላችሁ ፡ ለምኑ ፡ ብለው
ሕዝቡን ፡ አባበሏቸው ። መላውም ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ
ይህን ፡ ሰው ፡ በሞት ፡ አስወግደው ፡ በርባንን ፡ አድ
ነው ፡ ብለው ፡ ጮሁ ።

፮ ፡ ዳግመኛም ፡ ጲላጦስ ፡ ኢየሱስን ፡ ፈትቼ ፡
አድንላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ትወዳላችሁን ፡ አላቸው ።
እነሱ ፡ ግን ፡ ስቀለው ፡ ብለው ፡ ጮሁ ።

፳፪ ፤ ጲላጦስም ፡ ሦስተኛ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ክፉ ፡ ሥራ
ሠራ ፡ አላቸው ። እነሆ ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ የሚያስሞት ፡
በደል ፡ አላገኘሁበትም ፡ ገርፌ ፡ ልተወው ፡ አላቸው ።
፳፫ ፤ በታላቅ ፡ ቃል ፡ እየጮሁ ፡ ስቀለው ፡ ስቀ
ለው ፡ አሉ ። የካህናቱ ፡ አለቆች ፡ ቃልና ፡ የሕዝቡ
ቃል ፡ በረታ ።

፲፱ ፤ አይሁድና ፡ ጲላጦስ ፡ እንደዚህ ፡ ሲነጋገሩ ፡
ሚስቱ ፡ በዚህ ፡ በንጹሕ ፡ ሰው ፡ ደም ፡ ኀላፊ ፡
እንዳትሆንና ፡ እንዳትበድል ፡ ዕወቅ ፡ ብላ ፡ ላከች
በት ። ዛሬ ፡ በሕልሜ ፡ በእሳት ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀ
ምጦ ፡ አየሁት ፡ የእሳት ፡ ነበልባል ፡ ለብሶ ፡ የብዙ ፡
ብዙ ፡ የሚሆኑ ፡ መላእክትም ፡ ከበውት ፡ አንተ ፡ ግን
በእሳት ፡ ሰንሰለት ፡ ታሥረህ ፡ በእሳት ፡ አለንጋ ፡ እየገ
ረፉህ፡በአንገትህም፡ ታላቅ ፡ ዘንዶ፡ ተጠምጥሞ፡ከፊቱ
ቆመህ ፡ አየሁህ ። ስለዚህ ፡ ነገር ፡ በዚችም ፡ ሌሊት
ብዙ ፡ መከራ ፡ ስቀበል ፡ አደርኩ ፡ ብላ ፡ ላከችበት ።
፳፬ ፤ ጲላጦስም ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ጸብ ፡ ክር
ክር ፡ እየበዛ ፡ እንጂ ፡ የሚረባ ፡ የሚጠቅም ፡ ነገር
እንደሌለ ፡ አይቶ ፡ ውሃ ፡ በመቅረርት ፡ አስመጥቶ
በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ እጁን ፡ ታጠበና ። እኔ ፡ ከዚህ ፡
ከንጹሕ ፡ ሰው ፡ ደም ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፡ እናንተ ፡
ዕወቁ ፡ አለ ።

፳፭ ፤ ሕዝቡም ፡ የዚህ ፡ ሰው ፡ ደም ፡ በኛ ፡ ላይ
በልጆቻችንም ፡ ላይ ፡ ይሁንብን ፡ አሉ ። አይሁድ
ግን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ እየሰደቡ ፡ አንድ ፡ ጊዜ

ወደ ፡ ምስሶው ፡ ገፍተው ፡ ጣሉት ። ስድቡ ፡ ግን ፡
በዕለተ ፡ ዐርብ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡
ሙሉ ፡ ሰደቡት ፡ እንጂ ። የዮሴፍ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ የሳምራ
ዊም ፡ ሰው ፡ ነው ፡ እያሉ ። ጋኔንም ፡ ይዞ ፡ ያሳብ
ደዋል ፡ ልቡም ፡ እንደ ፡ ሰም ፡ ቀለጠ ፡ አጋንንትንም
ከአለቃቸው ፡ እየተነጋገረ ፡ ያወጣቸዋል ፡ እያሉ ።
፳፭ ፡ ጌታችን ፡ ግን ፡ በትሕትና ፡ መለሰ ፡ እኔስ ፡
ጋኔን ፡ የለብኝም ፡ አባቴን ፡ አከብራለሁ ፡ እንጂ ፡
አላቸው ። እናንተ ፡ ግን ፡ ትሰድቡኛላችሁ ፡ ታቃል
ሉኛላችሁ ፡ እኔስ ፡ ለራሴ ፡ ተድላ ፡ አልሻም ፡ የኔን ፡
ተድላ ፡ የሚሻ ፡ የሚፈርድልኝ ፡ አለ ፡ እንጂ ።
፳፮ ፡ ዳግመኛም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ሰይጣን ፡ ሰይጣንን ፡ ማውጣት ፡ እንዴት ፡ ይቻ
ለዋል ፡ አላቸው ። እርስ ፡ በርሷ ፡ የምትለያይ ፡ መን
ግሥት ፡ ትጠፋለች ፡ አትጸናምና ። የሀገር ፡ ሰዎችና
ቤተሰብ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ከተለያዩ ፡ ቤቱም ፡
አይጸና ፡ አገሩም ፡ አይቀና ። ሰይጣንም ፡ ሰይጣንን
የሚያወጣው ፡ ከሆነ ፡ ተለያየ ፡ መንግሥቱስ ፡ እን
ዴት ፡ ትፀናለች ።
፳፯ ፡ እኔ ፡ አጋንንትን ፡ ካለቃቸው ፡ እየተነጋገርኩ
የማወጣቸው ፡ ከሆነ ፡ ልጆቻችሁ ፡ በምንድር ፡ ነው
የሚያወጧቸው ። ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እነሱ ፡ መፈራ
ረጃ ፡ ይሆኑባችኋል ። እኔ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡
ሥልጣን ፡ አጋንንትን ፡ የማወጣቸው ፡ ከሆነ ፡ የእግዚ
አብሔር መንግሥት ፡ ልታጠፉችሁ ፡ ደርሳለች ። ኃይ

ለኛን ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ ካላሠሩት ፡ ከኃይለኛ ፡ ቤት ገብቶ ፡ ገንዘቡን ፡ መዝረፍ ፡ የሚቻለው ፡ የለም ።

፲፩ ፤ ከታሠረ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ገብቶ ፡ ገንዘቡን ፡ ይዘርፈዋል ። ከኔ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ያልሆነ ፡ ባላጋራዩ ፡ ነው ፡ ከኔም ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ያልሆነ ፡ ይለየኛል ። ሰውን ፡ የበደለ ፡ ኃጢአቱ ፡ ይሠረይለታል መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ የሰደበ ፡ ግን ፡ ኃጢአቱ ፡ አይሠረይለትም ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሚመጣውም ፡ ዓለም በገሃነም ፡ ለዘላለሙ ፡ ይፈረድበታል ፡ እንጂ ፡ አለ። ክፉ ፡ ጋኔን ፡ ይዞ ፡ ያሳብደዋል ፡ ብለውታልና ።

፲፪ ፤ አጋንንት ፡ ያደረባቸው ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ከአይሁድ ፡ ሺህ ፡ ጊዜ ፡ ተሽለው ፡ ምስክር ፡ ሆኑት ። ጋኔን ፡ እንደሌለበት ፡ ከብዔል ፡ ዜቡልም ፡ ጋራ ፡ መስማማት ፡ እንደሌለበት ። የልዑል ፡ እግዚአብሔር የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ እንደሆነ ፡ የልዑል ፡ እግዚአብሔር ልጅ ፡ ኢየሱስ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ አለን ፡ በማለታቸው ። ጊዜው ፡ ሳይደርስ ፡ መከራ ፡ ታጸናብን ፡ ዘንድ ከዚህም ፡ ታሳድደን ፡ ዘንድ ፡ መጣህን ፡ አጋንንትም ከዚህ ፡ የምታወጣን ፡ ከሆነ ፡ በፈቃድህ ፡ ወደ ፡ እሪያዎች ፡ አሰናብተን ፡ ብለው ፡ ለመኑት ፡ ሰገዱለትም ፤

፲፫ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ሂዱ ፡ ብሎ ፡ አሰናበታቸው ፡ እሊህም ፡ አጋንንት ፡ ከሰዎች ፡ ላይ ፡ ወጥተው ፡ ሄደው ፡ በእሪያዎቹ ፡ አደሩባቸው ። ሌላውም ጋኔን ፡ ያደረበት ፡ ሰው ፡ የናዝሬቱ ፡ ሰው ፡ ኢየሱስ ታጠፋን ፡ ዘንድ ፡ መጣህን ፡ እኛ ፡ ካንተ ፡ ምን ፡

አለን ፡ ብሎ ፡ ባዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ ጮኸ ። አንተ ፡ ማነህ
እግዚአብሔር ፡ ያከበረህ ፡ ማን ፡ እንደሆንክ ፡ ዐወቅንህ

፲፰ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ መለሰ ፡ ከሱም ፡
ተለተይህ ፡ ውጣ ፡ ብሎ ፡ ገሠፀው ። ጋኔኑም ፡ አማቶት
ጣለው ። በታላቅ ፡ ቃል ፡ እየጮኸ ፡ ወጣ ። እሱ
ንም ፡ አልጐዳውም ። አጋንንትም ፡ የያዛቸው ፡ ሁሉ
ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ይሰግዱለታል ። እየጮሁም ፡ የልዑል
እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ክርስቶስ ፡ በዕውነት ፡ አንተ
ነህ ፡ ይሉታል ።

፲፱ ፡ አይሁድ ፡ ግን ፡ ኃጥእ ፡ ነው ። በደለኛ ፡ ነው
ከፉ ፡ አድራጊ ፡ የሚያስት ፡ ነው ፡ አሉት ። የሚበላ
ወይንም ፡ የሚጠጣ ፡ የኃጥአንንም ፡ የመጸብሐንም ፡
ወዳጅ ፡ ነው ፡ አሉት ። የሚሳደብም ፡ ነው ፡ አሉት ።

፳ ፡ ጌታችን ፡ ግን ፡ በባሕርዩ ፡ ንጹሕ ፡ በአነዋወሩ
ክቡር ፡ ዕውነተኛ ፡ ነው ። ስለኃጢአት ፡ ከናንተ ፡
የሚከራከረኝ ፡ ማነው ፡ ብሎ ፡ አይሁድን ፡ እንዳላ
ቸው ፡ ኃጥእ ፡ አይደለም ።

፳፩ ፡ ዳግመኛም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ የላከውን
ደስ ፡ ሊያሰኝ ፡ የሚወድ ፡ ግን ፡ ዕውነተኛ ፡ ነው ፡
በሱም ፡ ዘንድ ፡ ሐሰት ፡ የለበትም ። ዳግመኛም ፡
ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ባባቴ ፡ ዘንድ ፡ የሰማሁትን ፡
ዕውነተኛ ፡ ነገር ፡ የምነግራችሁን ፡ ዕውነተኛ ፡ እኔን
ልትገድሉኝ ፡ ለምን ፡ ትፈልጉኛላችሁ ፡ አላቸው ።

፳፪ ፡ ጌታችን ፡ በዕውነት ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡
ነው ፡ በውነትም ፡ በኀ ፡ የሚሠራ ፡ ኃጢአትን ፡

ይቅር ፡ የሚል ፡ ነው ፡ ፍጹም ፡ ዕውቀት ፡ የሌላችሁ አይሁድ ፡ ሆይ ፡ ኃጥእ ፡ ሰው ፡ ኃጢአትን ፡ ይቅር ይላልን ። በተመረጠ ፡ በመጽብሐዊ ፡ ቤት ፡ በፍቅርና ፡ በትሕትና ፡ ሆኖ ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ ተቀምጠ ፡ ሳለ የቀራጮችን ፡ የብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ኃጢአት ፡ ይቅር ፡ ብሏልና ።

፳፫ ፡ ጸሐፍት ፡ ፈሪሳውያን ፡ በታወኩ ፡ ጊዜ ። ደቀ መዛሙርቱን ፡ መምህራችሁ ፡ ከኃጥአን ፡ ከቀራጮች ጋራ ፡ ለምን ፡ ይበላል ፡ ብለው ፡ ቢጠይቋቸው ።

፳፬ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ባለመድኃኒትን ፡ ደኅነኞች ፡ ያይደሉ ፡ የታመሙት ፡ ይፈልጉታል ። ከመሥዋዕት ፡ ምጽዋትን ፡ እወዳለሁ ፡ ያለውን ፡ ሂዱ ፡ ዕወቁ ። ኃጥአንን ፡ ወደ ፡ ንስሐ ፡ ልጠራ ፡ መጣሁ እንጂ ፡ ጻድቃንን ፡ ልጠራ ፡ አልመጣሁምና ።

፳፭ ፡ አይሁድ ፡ ግን ፡ ኃጢአት ፡ ይቅር ፡ የሚል እሱን ፡ ኃጥእ ፡ አሉት ። አንድ ፡ በሽተኛ ፡ ዘመዶቹ ፡ ባልጋ ፡ ተሸክመው ፡ አምጥተው ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ወዳለበት ፡ ቤት ፡ አገቡት ።

፳፮ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ የዚህን ፡ በሽተኛ ፡ የሃይማኖቱን ፡ ጽናት ፡ አይቶ ፡ አንተ ፡ ልጅ ፡ ሃይማኖትህ ፡ አዳነህ ፡ ኃጢአትህም ፡ ተሠረየልህ ፡ አለው ጸሐፍት ፡ ፈሪሳውያንም ፡ ከፉ ፡ አሰበው ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ ይህ ፡ የሚሳደብ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ያላንድ ፡ እግዚአብሔርስ ፡ ኃጢአትን ፡ ይቅር፡ማለት ፡ የሚቻለው ፡ ማነው ፡ ተባባሉ ።

፳፩ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ሐሳባቸውን ፡ ዐውቆ በልቡናችሁ ፡ ክፉን ፡ ለምን ፡ ታስባላችሁ ፡ አላቸው ይህንን ፡ በሽተኛ ፡ አልጋህን ፡ ተሸክመህ ፡ ሂድ ከማለትና ፡ ኃጢአትህ ፡ ተሠረየልህ ፡ ከማለት ፡ ማን ኛው ፡ ይቀላል ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ኃጢአት ፡ ማስተሥ ረይ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለው ፡ ታውቁ ዘንድ ፡ በተገባችሁ ፡ ነበር ፡ አላቸው ።

፳፰ ፤ ይህንንም ፡ በሽተኛ ፡ ተነሥተህ ፡ አልጋህን ተሸክመህ ፡ ወደ ፡ ቤትህ ፡ ሂድ ፡ አለው ። ተነሥ ቶም ፡ አልጋውን ፡ ተሸክሞ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያ መሰገነ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ ። ሕዝቡም ፡ ይህንን ፡ አይተው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ኃጢአት ፡ ያስተሠርይ ፡ ዘንድ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ እንዲህ ፡ ሥልጣን ፡ የሰጠ እግዚአብሔርን ፡ እያደነቁ ፡ አመሰገኑ ። አይሁድ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ኃጢአትን ፡ የሚያስተሠርይ ፡ እሱን ኃጥእ ፡ ነው ፡ አሉት ።

፳፱ ፤ ጸሐፍት ፡ ፈሪሳውያንም ፡ ስትሴስን ፡ የተገ ኘች ፡ ሴት ፡ አሥረው ፡ አመጡና ፡ በጌታችን ፡ ፊት አቁመው ፡ መምህር ፡ ይህች ፡ ሴት ፡ ስትሴስን ፡ አግ ኝተን ፡ አምጥተናታል ፡ በኛ ፡ ሕግ ፡ ሙሴ ፡ በደንጊያ ፡ ትወገር ፡ ብሎ ፡ ሥርዐት ፡ ሠርቷል ፡ አንተ ፡ ስለ ፡ እሷ ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡ አሉት ። ይህንንም ማለታቸው ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ምክንያት ፡ ያገኙበት ፡ ዘንድ ፡ ሊፈታተኑት ፡ ነው ።

፴ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ምድር ፡ ምድር ፡ እየ ተመለከተ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ከስ ማቸው ፡ ጋራ በጣቶቹ ፡ ጻፈ ። ነገር ፡ ግን ፡ ያንዱን ኃጢአት ፡ ላንዱ ፡ አልገለጠም ። ጌታችን ፡ ኢየሱ ስም ፡ ኃጢአትን ፡ የሚሠውር ፡ ነው ፡ እንጂ ። ከና ንተ ፡ ኃጢአት ፡ የሌለበት ፡ ሰው ፡ መዠመሪያ ፡ በደንጊያ ፡ ይውገራት ፡ አላቸው ።

፴፩ ፤ ዳግመኛም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ተመልክቶ ፡ የቀረ ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ጻፈባቸው ። ይህንንም ፡ ዘለፋቸውን ፡ ሰምተው ፡ ወጥተው ፡ ሄዱ ።

፴፪ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ይህችን ፡ የታሠረች ቷት ፡ የሚፈርዱብሽ ፡ ሰዎች ፡ ወዴት ፡ አሉ ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቃት ፡ ጌታዬ ፡ እኔ ፡ አላውቅም ፡ አለችው ።

፴፫ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም እኔም ፡ አልፈርድብሽም በደኅና ፡ ሂጂ ። ዳግመኛም ፡ አትበድዪ ፡ አላት ። አይ ሁድ ፡ ግን ፡ ኃጢአትን ፡ የሚያስተሠርይ ፡ እሱን ፡ ኃጥእ ፡ አሉት ።

፴፬ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ ከዛፍ ላይ ፡ የወጣ ፡ የቀራጮች ፡ አለቃ ፡ የሚሆን ፡ ዘኬዎ ስን ፡ ኃጢአቱን ፡ ይቅር ፡ አለው ፡ ከቤቱም ፡ ገብቶ ዋለ ። ሺቱ ፡ የቀባችውን ፡ እግሩንም ፡ በዕንባዋ ፡ ያጠበችው ፡ በራስዋ ፡ ጠጉር ፡ ያራሰችውንም ፡ ብዙ ፡ ኃጢአቷን ፡ ይቅር ፡ አላት ። ብዙውን ፡ ወዳዋለችና ።

፴፩ ፤ ኃጢአትን ፡ ይቅር ፡ የሚል ፡ በጎ ፡ የሚሠራ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ አምላክ ፡ ገፉት ፡ ሰደቡት ። ጌታችን ፡ ኢየሱስንም ፡ ይገርፉት ፡ ዘንድ ፡ እግሮቹ ንም ፡ እጆቹምን ፡ ከደንጊያ ፡ ጋራ ፡ የኋሊት ፡ አሠ ሩት ። ነቢዩ ፡ ጀርባዬን ፡ ለግርፋት ፡ ሰጠሁ ። ያለ ውን ፡ አላስተዋሉምና ። የኃይሉን ፡ ጽናት ፡ የእጆ ቹንና ፡ የእግሮቹን ፡ ልዕልና ፡ አላስተዋሉምና ።

፴፪ ፤ መጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፡ ከኔ ፡ በኋላ ፡ የሚመ ጣው ፡ ከኔ ፡ ይጸናል ፡ ብሎ ፡ ካስተማራቸው ፡ በኋላ የእግሮቹን ፡ ጫማ ፡ ማዘቢያ ፡ ለመፍታት ፡ የማይገ ባኝ ፡ ነኝ ፡ እኔም ፡ በውሃ ፡ አጠምቃችኋለሁ ። እሱ ፡ ግን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በእሳት ፡ ያጠምቃችኋል የውድማን ፡ እኽል ፡ የሚያጸራባቸው ፡ መንሾች ፡ በእ ጆቹ ፡ የተያዙ ፡ ስንዴውን ፡ በረቅ ፡ በጐተራ ፡ ያከማ ቻል ። ገለባውን ፡ ስይቶ ፡ ከማይጠፋ ፡ እሳት ፡ የሚ ያቃጥልበት ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስና ፡ በእሳት ፡ የሚያ ጠምቅ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ አምላክ ፡ አሠሩት ።

፴፫ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስንም ፡ ካሠሩት ፡ በኋላ ፡ አራት ፡ ቤት ፡ ጭፍሮችና ፡ ጲላጦስ ፡ በገመድና ፡ ባለንጋ ፡ ፷ሺ ፡ ከ፷፻፷፯ ፡ ጊዜ ፡ ገረፉት ። አምስት ፡ ሺህ ፡ ነው ፡ የሚሉም ፡ አሉ ። የግርፋቱን ፡ ቍጥር እያሳሳቱ ፡ ገርፈውታልና ።

፴፬ ፤ የሚሞት ፡ እንዳይገረፍ ፡ የማይሞትም ፡ እንዲገረፍ ፡ እያወቁ ። በግፍ ፡ ገርፈው ፡ በግፍ ፡ ገደ ሉት ። የተገረፈባቸውም ፡ አለንጋና ፡ ገመድ ፡ በደም

ታለሉ ። ከግርፋቱም ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ ሥጋው ፡ ሁሉ ፡ አለቀ ፡ ሺህ ፡ ፷፮፡ ከሚሆኑ ፡ ቊስሎቹም ፡ ወገን ፡ አጥንቶቹ ፡ ታዩ ። ጥቁርና ፡ ሰማይ ፡ የሚ መስሉ ፡ ቊስሎች ፡ ግን ፡ ሺሕ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ከዘጠና ፡ ናቸው ።

፴፱ ፤ የማይገረፍ ፡ አምላክ ፡ በዚህ ፡ ሥጋ ፡ ተገ ረፈ ፡ ጲላጦስ ፡ እጁን ፡ ከታጠበ ፡ በኋላ ፡ ጌታችንን የገረፈው ፡ በጆሮ ፡ ለሚሰማው ፡ በዐይን ፡ ለሚያ የው ፡ ሰው ፡ ዕፁብ ፡ ድንቅ ፡ ነው ። በመገረፉም ፡ አይሁድን ፡ ደስ ፡ አሰኛቸው ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ግን ፡ በመገረፉ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ከተገረፈባት ፡ ኃጢአት ፡ ፍዳ ፡ አዳነን ። ስለ ፡ ልጆቹና ፡ ስለ ፡ አዳም ፡ መገረፍን ፡ መታሰርን ፡ ከፍሎልናልና ።

## ሁለተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ጲላጦስም ፡ ፈቃዳቸውን ፡ ለመፈጸም ፡ ስቀሉት ብሎ ፡ ጌታችንን ፡ ለአይሁድ ፡ ሰጣቸው ። የጭፍራ ባለዋሶችም ፡ ጌታችንን ፡ ተቀብለው ፡ ወደ ፡ ፍርድ አደባባይ ፡ ወሰዱት ።

፪ ፤ የንጉሡ ፡ የቄሣር ፡ ሥዕል ፡ ወዳለበት ። በደሙ ፡ አንድ ፡ የሆኑትን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ሰበሰቡ ባሮቹ ፡ መንግሥታት ፡ መዘባበቻ ፡ ይዘብቱበት ፡ ዘንድ

፫ ፤ ልብሶቹንም ፡ ገፈፉ ፡ የመንግሥት ፡ ልብስ የሚሆን ፡ ነጭ ፡ ሐር ፡ የካህናት ፡ ልብስ ፡ የሚሆን

ቀይ ፡ ሐር ፡ ነበራቸው ፡ ቀይና ፡ ጥቍር ፡ ልብስ ፡ አለበሱት ፡፡ የአጣቢ ፡ ሳሙና ፡ የማይሆን የማይቻለው ፡ እንደ ፡ መብረቅ ፡ የሚያንጸባርቅ ፡ እንደ ፡ በረድ ፡ የሆነ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ የሚለብስ ፡ ሲሆን ፡፡ እንደዚህ ፡ በምድር ፡ በመዘባበት ፡ ቀይ ፡ ሐርና ፡ ነጭ ፡ ሐር ፡ አለበሱት ፡፡ ለኪሩቤል ፡ ልብስ ፡ ረቅ ፡ ልብስ ፡ ለሱራፌል ፡ ግርማ ፡ ያለው ፡ የመብ ፡ የሚያለብሳቸው ፡ እሱን ፡ በእሳት ፡ በተጋረደ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ የሚቀመጥ ፡ እሱን ፡ በመዘባበቻ ፡ መቀመጫ ፡ ላይ ፡ አስቀመጡት ፡፡

፬ ፡ ከዚህ ፡ ከዙፋኑ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ገለት ፡ ብልጭታ ፡ መብረቅም ፡ ነጐድጓድም ፡ ይወጣል ፡፡ ከዚህም ፡ ከዙፋኑ ፡ ሥር ፡ የንፉስ ፡ ባሕር ፡ የብርሃን ፡ ባሕር ፡ ይመነጫል ፡፡ ከዘንባባ ፡ እሾህ ፡ ጋራ ፡ የተጋጉ ፡ በመርፌ ፡ አምሳል ፡ የተሠሩ ፡ አምሳ እሾሆች ፡ ያሉበት ፡ የመገዳደሪያ ፡ አክሊል ፡ አቀዳጁት ፡፡ እሊህም ፡ እሾሆች ፡ እስከ ፡ ራሱ ፡ አጥንት ፡ ድረስ ፡ ገቡ ፡፡

፭ ፡ የሕይወት ፡ መገኛ ፡ እሱን ፡ የሾኽ ፡ አክሊል አቀዳጁት ፡፡ ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ የሚያድን ፡ እሱን ፡ የሾኽ ፡ አክሊል ፡ አቀዳጁት ፡፡ መላእክትን ፡ የብርሃን ፡ ራስ ፡ ቍር ፡ የሚያቀዳጃቸው ፡ የንጉሥታት ፡ ገዥ ፡ የሚሆን ፡ እሱን ፡ የሾኽ ፡ አክሊል ፡ አቀዳጁት ፡፡ በሾኽ ፡ አክሊልም ፡ ከራሱ ፡ ክፍል ፡ የበሱት ፡ ያቆ

ስሉት ፡ ሺህ ፡ ናቸው ። ከራሱም ፡ ቍስሎች ፡ ደም እንደ ፡ ውሃ ፡ በዝቶ ፡ ፈሰሰ ።

፫ ፤ ፊቱም ፡ ደምን ፡ ለበሰ ። ሰውነቱም ፡ ሁሉ ፡ በደም ፡ ተጠመቀ ። የጽዮንም ፡ ልጆች ፡ እናቱ ፡ ያቀዳ ጀችውን ፡ አክሊል ፡ ተቀዳጅቶ ፡ አዩት ። ተድላ ፡ ደስታ የሚያደርግበትና ፡ የሙሽርነቱ ፡ ቀን ፡ ነውና ።

፬ ፤ በቀኝ ፡ እጁ ፡ ዘንግ ፡ አስያዙት ። ሲያሽሟ ጥጡ ፡ ከፊቱ ፡ እየወደቁ ፡ እጅ ፡ ነሡለት ። የመላ እክት ፡ ሠራዊት ፡ እየደነገጹ ፡ የሚሰግዱለትን ። የአ ይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ቸር ፡ ውለሃል ፡ አሉት ። ሥል ጣናትና ፡ ሊቃናት ፡ እየፈሩ ፡ ለሚሰግዱለት ፡ እሱን በትዕቢት ፡ እጅ ፡ ነሡለት ።

፭ ፤ አምስት ፡ የሚሆኑ ፡ መዘባበቻቸውን ፡ ከጨረሱ በኋላ ፡ በምራቁ ፡ ሁለተኛ ፡ ዐይኖችን ፡ በሚፈጥር ፡ ፊት ፡ ምራቃቸውን ፡ ተፉበት ። ዳግመኛም ፡ ፊቱን በጥፊ ፡ መቱት ። ኪሩቤል ፡ ፊቱን ፡ ከማየት ፡ የተነሣ በእሳት ፡ አክናፍ ፡ የሚሠወሩት ፡ ያልበደላቸውን ፡ እሱን አይሁድ ፡ ፊቱን ፡ ጸፉት ፡ ፊቱ ፡ እንደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱ ስና ፡ እንደ ፡ አባቱ ፡ ሲሆን ፡ በሥጋው ፡ ፊቱን ፡ ጸፉት ከፊቱ ፡ ግርማ ፡ የተነሣ ፡ ፍጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ የሚርዱለት የሚንቀጠቀጡለት ፡ የፈጣሪያቸውን ፡ ፊቱን ፡ ጸፉት ። መዠመሪያ ፡ በመመታቱና ፡ የሾኽ ፡ አክሊል ፡ በመ ቀዳጀቱ ፡ ራሱ ፡ የቆሰለ ፡ ከመሆኑ ፡ በላይ ፡ የያዘውን ፡ በትር ፡ ከእጁ ፡ ተቀብለው ፡ ራሱን ፡ መቱት

፱ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የሾኽ ፡ አክሊልን ፡ በመቀ ዳጀቱ ፡ በምድራችን ፡ ላይ ፡ የበቀሉትን ፡ አሜከ ላና ፡ እሾኽ ፡ እርግማንን ፡ አጠፋልን ። ራሱንም ፡ በዘንግ ፡ በመመታቱ ፡ የታላቁን ፡ እባብ ፡ ሰባቱን እራሶቹን ፡ ዐሥሩ ፡ ቀንዶቹን ፡ አጠፋልን ።

## ሥስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ከግ ምብ ፡ ላይ ፡ አውጥተው ፡ ሲዘባበቱ ፡ በመስኮት ፡ ዘልቀህ ፡ ተመልከት፡አሉት ። እንደ ፡ ነገሥታትም ፡ ልማድ ፡ ለሕዝቡ ፡ ተገልጸህ ፡ ታያቸው ፡ ንጉሣ ችን ፡ ነህና ፡ አሉት ።

፪ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ለሕዝቡ ፡ በተገለጸ ላቸው ፡ ጊዜ ፡ እየሳቁ ፡ ተዘባበቱበት ፡ ጥርሶቻቸ ውንም ፡ አፏጩበት ። ስንኳን ፡ ስንኳን ፡ በዐይና ችን ፡ አየነው ፡ እያሉ ፡ ተናገሩ ።

፫ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ከግንቡ ፡ ላይ ፡ አውር ደው ፡ እስከ ፡ ደረቱ ፡ ድረስ ፡ ከጕድጓድ ፡ ቀበሩት ። በጕድጓድም ፡ ውስጥ ፡ እንዳይሞት ፡ እጆቹን ፡ ከተ ተከለ ፡ ግንድ ፡ ጋራ ፡ አሠሩት ። ለሞትም ፡ በደ ረሰ ፡ ጊዜ ፡ ከጕድጓድ ፡ አወጡት ።

## ዐራተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ጲላጦስም ፡ ወደ ፡ አይሁድ ፡ ወጥቶ ፡ አን
ዲት ፡ ስንኳ ፡ በደል ፡ እንዳላገኘሁበት ፡ ታውቁ ፡
ዘንድ ፡ እነሆ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አወጣላችኋለሁ ፡ አላቸው
፪ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ነጭ ፡ ሐር ፡ ለብሶ ፡
የሾኽ ፡ አክሊል ፡ ተቀዳጅቶ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወጣ ።
ይህ ፡ ሰው ፡ እነሆ ፡ አላቸው ፡ የካህናቱም ፡ አለ
ቆች ፡ ብላቴኖቻቸውም ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ስቀለው ፡
ስለቀው ፡ ብለው ፡ ጮሁ ።
፫ ፤ ጲላጦስም ፡ እኔስ ፡ ያገኘሁበት ፡ በደል ፡ የለ
ኝም ፡ እናንተ ፡ ወስዳችሁ ፡ ስቀሉት ፡ አላቸው ።
፬ ፤ አይሁድም ፡ መልሰው ፡ ለኛስ ፡ ሕግ ፡ አለን ፡
እንደ ፡ ሕጋችን ፡ ሊሞት ፡ ይገባዋል ፡ የእግዚ
አብሔር ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ ብሏልና ፡ አሉ ።
፭ ፤ ጌታችንስ ፡ በዕውነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ
ነው ። አባቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ በደብረ ፡ ታቦ
ርና ፡ በዮርዳኖስ ፡ የምወደው ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የሚ
ነግራችሁን ፡ ስሙት ፡ ብሏልና ። መንፈስ ፡ ቅዱስም
በደመና ፡ በርግብ ፡ አምሳል ፡ ወርዶ ፡ በላዩ ፡ ተቀ
ምጦ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መሰከ
ረለት ። ሙሴም ፡ ኤልያስም ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡
የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ አሉት ።

፮ ፤ ከዚህም ፡ አስቀድሞ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ በቂሣርያ ፡ እናንተስ ፡ ማን ትሉኛላችሁ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። ያን ፡ ጊዜ ፡ አባቱ እግዚአብሔር ፡ ለጴጥሮስ ፡ ገለጸለት ፡ ጴጥሮስም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ክርስቶስ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ አለው ።

፯ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ የዮና ፡ ልጅ ስምዖን ፡ አንተም ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነህ ፡ አለው ። ሰማያዊ ፡ አባቴ ፡ ገልጾልህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሥጋዊ ደማዊ ፡ መምህር ፡ አልገለጸልህምና ።

፰ ፤ ከዚህም ፡ አስቀድሞ ፡ የምሥጢር ፡ መል ክተኛ ፡ ገብርኤል ፡ ክቡር ፡ ልዑል ፡ ነው ፡ የል ዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ይባላል ፡ አለው ። መጥምቁ ፡ ዮሐንስም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈጽሞ ፡ ያየው ፡ የለም ፡ ባባቱ ፡ ቀኝ ፡ የተቀመጠ ፡ አንድ ልጅ ፡ አይቶ ፡ ነገረን ፡ እንጂ ፡ አለ ።

፱ ፤ ዳግመኛም ፡ እኔ ፡ አይቸዋለሁ ፡ የእግዚአ ብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እኔ ፡ ምስክሩ ፡ ነኝ ፡ አለ ። ዳግመኛ ፡ አብ ፡ ልጁን ፡ ይወዳልና ፡ ሁሉንም በእጁ ፡ ሰጠው ።

፲ ፤ በወልድ ፡ ያመነ ፡ የዘላለም ፡ ሕይወት ፡ አለው ። በወልድ ፡ ያላመነ ፡ ግን ፡ ለዘላለም ፡ ሕይ ወትን ፡ አያያትም ። መቅሠፍት ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ይኖ ራል ፡ እንጂ ። ናትናኤልም ፡ መምህር ፡ በዕውነት

የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ የእስራኤልም ፡ ንጉሣቸው
አንተ ፡ ነህ ፡ አለው ።

፲፩ ፤ ወደመርከቡም ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ባሕር ፡ ነፋ
ሳትም ፡ ታዘዙለት ። በመርከቡ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡
ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ መጥተው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡
ክርስቶስ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ እያሉ ፡ ሰገዱለት ። ጌታ
ችን ፡ ኢየሱስም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ እናንተም
ከነዚህ ፡ ጋራ ፡ ልትሄዱ ፡ ትወዳላችሁን ፡ አላቸው ።

፲፪ ፤ ጴጥሮስም ፡ መልሶ ፡ አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ የዘ
ለዓለም ፡ ትምህርት ፡ ሕይወት ፡ ካንተ ፡ ሳለ ፡ ወዴት
እንሄዳለን ፡ እኛስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ክርስ
ቶስ ፡ እንደሆንክ ፡ ዐውቀን ፡ አምነናል ፡ አለው ።
ማርታም ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ የመጣህ ፡ የእግዚአብ
ሔር ፡ ልጅ ፡ ክርስቶስ ፡ አንተ ፡ እንደሆንክ ፡ አም
ኜብሃለሁ ፡ አለች ።

፲፫ ፤ ነባቤ ፡ መለኮት ፡ የሚባል ፡ ዮሐንስም ፡
ይህ ፡ ሁሉ ፡ የተጻፈ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ታምኑ ፡
ዘንድ ፡ ነው ። በሱም ፡ ስም ፡ አምናችሁ ፡ የዘለ
ዓለም ፡ ሕይወትን ፡ ታገኙ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ አለ ።

## አምስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ወደ ፡ ጥንተ ፡ ነገራችን ፡ እንመለስና ፡ ጲላጦስ ፡
ግን ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ሰምቶ ፡ እጅግ ፡ ፈራ ። ወደ ፡

አደባባይም ፡ ወጥቶ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ አንተ ከወዴት ፡ ነህ ፡ አለው ፡፡

፱ ፤ ጌታችን ፡ ግን ፡ ምንም ፡ አልመለሰለትም ፡፡ ጲላጦስም ፡ መልስ ፡ አትመልስልኝምን ፡ ላድንህ ፡ እንዲቻለኝ ፡ አታውቅምን ፡ አለው ፡፡

፲ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ ከሰማይ ፡ ሥልጣን ፡ ካልተሰጠህ ፡ በምንም ፡ በምን ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ የለህም ፡ አለው ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ባሲያዘኝ ፡ በይሁዳ ፡ ጽኑ ፡ ፍዳ ፡ አለበት ፡፡ ስለዚህም ነገር ፡ ጲላጦስ ፡ ሊያድነው ፡ ወደደ ፡፡

፲፩ ፤ አይሁድም ፡ ይህን ፡ ካዳንከው ፡ የቄሣር ፡ ወዳጅ ፡ አይደለህም ፡፡ ንጉሥ ፡ ነኝ ፡ የሚል ፡ ሁሉ ፡ የቄሣር ፡ ወንጀለኛ ፡ ነውና ፡ አሉት ፡፡

## ስድስተኛ ፡ ምዕራፍ ፡፡

፩ ፤ ጌቶቼ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ! አደራ ፡ እላችኋለሁ ፡፡ እመቤቴ ፡ ማርያም ፡ አንቺንም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ትገቢልኝ ፡ ዘንድ ፡ እማልድሻለሁ ፡፡ በነፍሱና በሥጋው ፡ በተቀበላቸው ፡ መከራዎች ፡ ሁሉ ፡፡

፪ ፤ በመቸንከሩም ፡፡ የሾኽ ፡ አክሊል ፡ ተቀዳጅቶ በመስቀሉ ፡፡ ሞቱም ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ በመውረዱ ፡ ባጦር ፡ በመወጋቱ

፫ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በመቀበሩ ኃጢአቴን ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ ትሉ ፡ ዘንድ ፡ ከኃጢአ

ትም ፡ ፍዳ ፡ ሁሉ ፡ ታድኑኝ ፡ ዘንድ ፡ በዘላ
ለሙ ፡ አሚን ።

## የሐሙስ ፡ አርኬ ።

፩ ፤ አገባቡ ፡ ጥፋት ፡ ሲሆን ፤ በርባንን ፡ ያድ
ንላቸው ፡ ዘንድ ፡ ጲላጦስን ፡ ለመኑት ። አቤቱ ፡
የአይሁድ ፡ ወገኖች ፡ ባለመከፈል ፡ ጮሁብህ ፤
ሁሉንም ፡ አስጮሁብህ ። በቃላቸውም ፡ ስቀለው ፡
ስቀለው ፡ አሉ ።

፪ ፤ ተሰብስበው ፡ ከንቱ ፡ ነገርን ፡ የተናገሩ ፡
አይሁድ ፡ በማቃለል ፡ ኢየሱስን ፡ በሞት ፡ እናርቀው
በርባንን ፡ እናድነው ፡ ባሉህ ፡ ጊዜ ፡ የታገሥህ ። የኢየ
ሱስን ፡ ትዕግሥት ፡ ምድር ፡ መሸከም ፡ ተሳናት ፡ ብሎ
የኔ ፡ የባሪያህ ፡ ቃል ፡ ትዕግሥትህን ፡ አመሰገነው ።

፫ ፤ አይሁድ ፡ ይገርፉህ ፡ ዘንድ ፡ በኃይል ፡ ወደ ፡ ደን
ጊያ ፡ ምሰሶ ፡ ገፍተው ፡ በመረጡት ፡ ገመድ ፡ ከሱ ፡ ጋራ
ያሠሩህ ። ሄሮድስ ፡ የገረፈህ ፡ ቃል ፡ ኃጢአት ፡ ማስተ
ሥረይ ፡ በሚችል ፡ በሥልጣንህ ፡ በደሌን ፡ አስተሥር
ይልኝ ፡ በደሌ ፡ እንደ ፡ ሣርና ፡ እንደ ፡ ቅጠል ፡ በዝቷልና

፬ ፤ ከልብስ ፡ የተራቆትህ ። መጽሐፍም ፡ እንደተ
ናገረ ፡ በጅራፎች ፡ አጥንትህ ፡ እስኪታይ ፡ የተገ
ረፍህ ። ዘአምስት ፡ እልፍ ፡ ልክ ፡ በመገረፍህ ፡
ክርስቶስ ፡ ግዙፍ ፡ የሚሆን ፡ ባለአንገት ፡ እኔን ፡
ከአፍህ ፡ በወጣ ፡ ሥልጣን ፡ ከመቆረጥ ፡ አድነኝ ።

፭ ፤ አምስት ፡ በሆኑ ፡ በመንግሥት ፡ ሥራዎች ፡ ይሜወቱብህ ፡ ዘንድ ፡ በንጉሥ ፡ ሥዕል ፡ ቤት ፡ ያገቡህ ፡ አይሁድ ፡ በዝብብት ፡ ወምበር ፡ ያስቀመጡህ ክርስቶስ ፡ ሆይ ችግረኛ ፡ ልጅን ፡ አባት ፡ እንደ ፡ አዳነው ፡ ከምስቱ ፡ ጥል ፡ በቸርነትህ ፡ አድነኝ ፡፡

፮ ፤ በሰማይ ፡ አምሳል ፡ ጥቍር ፡ ሐርና ፡ ቀይ ፡ ግምጃ ፡ ያለበሱህ ፡ በበትር ፡ በመደብደብና ፡ በጥፊ ፡ በመመታት ፡ ጊዜ ፡ ያልተናገርህ ፡ ነቢይ ፡ እሳትና ፡ ውሃ ፡ በውስጧ ፡ ከተቀላቀሉባት ፡ ከታላቅ ፡ ባሕር ፡ መስጠም ፡ በመስቀልህ ፡ አድነኝ ፡፡

፯ ፤ የሰብዓ ፡ እሾኾች ፡ ዓይነት ፡ ያለበት ፡ የተማዳሮት ፡ ዘውድን ፡ አቀዳጅተው ፡ ያገዳደሩህ ፡፡ በእሾኾች ፡ ቍጥርም ፡ የከበረ ፡ የራስህ ፡ ደም ፡ የፈሰሰ ፡፡ መልአከ ፡ ሞት ፡ በእሳት ፡ ጕጠት ፡ ነፍሴን እንዳያወጣ ፡ እንደ ፡ ቸር ፡ ወዳጅ ፡ በሞቴ ፡ ጊዜ ፡ በረድኤት ፡ ጐብኘኝ ፡፡

፰ ፤ ዓለምን ፡ በያዘ ፡ እጅህ ፡ በትርን ፡ ያስያዙህ በሽንገላም ፡ እራስህን ፡ የመቱህ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ መልአክን ፡ ከሆንኩ ፡ በኋላ ፡ በሥራዬ ፡ እንስሳ ፡ ሆኛለሁና ፡ ከረቂቅ ፡ ሥልጣንህ ፡ የተነሣ ፡ ወደሌት እሄዳለሁ ፡ ከፊትህስ ፡ ወዴት ፡ እሸሻለሁ ፡፡

፱ ፤ ከረጅም ፡ የጨዋታ ፡ ሕንፃ ፡ ያወረዱህ ፡ ወገኖች ፡ በመለኮቱ ፡ ረቂቅ ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ እስከ ፡ ሆነ ፡ ደረትህ ፡ ድረስ ፡ በጥልቅ ፡ ጕድጓድ

ውስጥ ፡ የቀበሩህ ፡ ጽድቅ ፡ የሌለኝ ፡ እኔ ፡ ባሪያህን ፡ ጳውሎስ ፡ እንደ ፡ ነገረኝ ፡ በቸርነትህ ፡ አጽድቀኝ ።

፲ ፤ በመስገድና ፡ በመንበርከክ ፡ ያሸሚጠጡህ ፡ ወገኖች ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ አይደለም ፡ ያሉህ ፡ ከመታወክ ፡ ዕብራዊ ፡ ሕይወትህን ፡ ከጠሉ ዘንድ ፡ ጲላጦስን ፡ ይኸንን ፡ ሰው ፡ ብታድነው ፡ ፈጽመህ ፡ የንጉሥ ፡ ወዳጅ ፡ አይደለህም ፡ አሉት ።

፲፩ ፤ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤ እኔን ፡ ባሪያህን ፡ ጠብቀኝ ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

## የዐርብ ፡ ድርሳነ ፡ ማሕየዊ ።
## አንደኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ በማመን ፡ ሁሉን ፡ የሚታደግ ፡ ሁሉን ፡ የሚያድን ፡ የጌታችን ፡ የመድኃኔ ፡ ዓለምን ፡ የሞቱንና ፡ የመከራውን ፡ ነገር ፡ የሚናገር ፡ በዕለተ ፡ ዓርብ ፡ የሚነበብ ፡ (የሚጸለይ ፡) ድርሳን ፡ ይህ ፡ ነው ።

፪ ፤ ጲላጦስም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ሰምቶ ፡ ጌታችን ኢየሱስን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አወጣው ። በዕብራይስጥ ፡ ንጥፍ ፡ ደንጊያ ፡ በሚሉት ፡ ሊቶስጥራ ፡ በሚባል ቦታ ፡ በወንበር ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ። ስድስት ፡ ሰዓት ፡ ሆኖ ፡ ነበረና ፡ ፋሲካቸው ፡ አለፈባቸው ።

፫ ፤ ጲላጦስም ፡ አይሁድን ፡ ንጉሣችሁ ፡ እነሆ ፡ አላቸው ። ስቅለህ ፡ በሞት ፡ አርቅልን ፡ ብለው ፡

ሙሁ ። ጲላጦስም ፡ ንጉሣችሁን ፡ ልስቀለውን ፡
አላቸው ። የካህናት ፡ አለቆችም ፡ መልሰው ፡
እኛስ ፡ ያለ ፡ ቄሣር ፡ ንጉሥ ፡ የለንም ፡ አሉት ።
ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ስቀሉት ፡ ብሎ ፡ ሰጣቸውና ፡
ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ተቀብለው ፡ ይዘውት ፡ ሄዱ ።
፲፯ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያለበሱትን ፡ ነጩን ፡ ሐርና
ቀዩን ፡ ሐር ፡ ገፈው ፡ ልብሱን ፡ አለበሱት ። ቁመቱ
፲፯ ፡ ክንድ ፡ የሚሆን ፡ የሚሰቀልበትን ፡ ዕንጨት ፡
አሸከመው ፡ ሊሰቅሉት ፡ ወሰዱት ። ሲወስዱትም ፡
የቀራንዮ ፡ ሰው ፡ ስምዖን ፡ ከዱር ፡ ሲገባ ፡ አገኙት ።
ጌታችን ፡ ኢየሱስንም ፡ ይከተለው ፡ ዘንድ ፡ መስ
ቀሉን ፡ አሸከሙት ። የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ይዘው ፡
የተከተሉትም ፡ ጭፍሮች ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ሰማኒያ
ናቸው ። ከነሱም ፡ ጋራ ፡ የተባበሩ ፡ ሌሎችም
ሰዎች ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ናቸው ። ሴቶችም ፡
ተከትለው ፡ ያለቅሱለት ፡ ነበር ።
ሸ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ተመልሶ ፡ አይቶ ፡
የእሥራኤል ፡ ልጆች ፡ ለኔ ፡ አታልቅሱ ፡ ለራሳችሁ
ለልጆቻችሁም ፡ አልቅሱ ፡ እንጂ ፡ አላቸው ።
መካን ፡ የሆኑ ፡ ሴቶች ፡ ያልወለዱችም ፡ ማኅፀን ፡
ያላጠቡም ፡ ጡቶች ፡ ንዑዳት ፡ ክቡራት ፡ ናቸው ፡
የሚሉበት ፡ ወራት ፡ ይመጣልና ። የዚያን ፡ ጊዜ ፡
ተራራው ፡ ተንዶ ፡ በተጫነን ፡ ምድሩ ፡ ተከፍቶ ፡
በዋጠን ፡ ትላላችሁ ። በዚህ ፡ በርጥብ ፡ ዕንጨት ፡
እንዲህ ፡ ያደረጉ ፡ ደረቅ ፡ ቢያገኙ ፡ እንዴት ፡ በሆኑ ።

፬ ፤ ከሱም ፡ ጋራ ፡ ይሰቅሏቸው ፡ ዘንድ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ይሠሩ ፡ የነበሩ ፡ ሁለት ፡ ወንበዴዎች ፡ ወሰዱ ። ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ የመስቀሉን ፡ ዕንጨት ፡ በመ ሸከም ፡ ደክሞ ፡ ወዛ ፡ ትከሻውም ፡ ሊሰበር ፡ ደረሰ የሚፍገመገሙትን ፡ የሚደግፍ ፡ የወደቁትን ፡ የሚ ያነሣ ፡ እሱ ፡ ሲሆን ፤ መስቀሉን ፡ እንደ ፡ ተሸ ከመ ፡ በጐዳና ፡ ላይ ፡ አምስት ፡ ጊዜ ፡ ወደቀ ።

፭ ፤ በወደቀም ጊዜ ፡ የዘንባባ ፡ ገመድ ፡ በአንገቱ አግብተው ፡ ሦስት ፡ ኃይለኞች ፡ ጐተቱት ። ወደ ፡ ሠርጉ ፡ የተጠሩትን ፡ ሰዎች ፡ በመታረዱ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ የላህም ፡ ፍሪዳ ፡ ነውና ። ለመሰቀልም ፈጥኖ ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ እስከሚሰቀልበት ፡ ቦታ ፡ ድረስ ፡ በበትር ፡ እየመቱ ፡ እየገፉ ፡ ወሰዱት ። በጐ ዳና ፡ የዘገየ ፡ እንደሆን ፡ ልጆቹን ፡ ስላዳነለት ፡ ጲላ ጦስ ፡ መጥቶ ፡ ከመስቀል ፡ ያድነዋል ፡ ብለው ፡ እያ ዳፉ ፡ ወሰዱት ።

፮ ፤ ቀራንዮም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ደረት ፡ የሚሰነ ጥቅ ፡ ጉሮሮ ፡ የሚያነቃ ፡ የዝሙን ፡ ሐሞትና ፡ ከርቤ የተቀላቀለበት ፡ ጠጅ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ አጠ ጡት ። እሱም ፡ ጥቂት ፡ ቀምሶ ፡ ተወው ። እንደ ወንበዶች ፡ ጥሩ ፡ ጠጅ ፡ አላጠጡትም ፡ ጠጅ ፡ ያጠ ጣነው ፡ እንደሆነ ፡ ከስካሩ ፡ የተነሣ ፡ የችንካሩ ፡ መከራ ፡ አይሰማውም ። ተሰቅሎም ፡ ፃዕር ፡ ሳያ ገኘው ፡ ይሞታልና ፡ አሉ ፡ እንጂ ።

፱ ፤ አይሁድም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ከመስ
ቀሉ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ክንድ ፡ ያህል ፡ በተረፈ ፡ ችን
ክር ፡ ላይ ፡ በጀርባው ፡ አስተኙት ፡፡ ይኸውም ፡ ችን
ክር ፡ በደረቱ ፡ ዘልቆ ፡ ወጣ ፡፡ ደረቱንም ፡ ከመስ
ቀሉ ፡ ጋራ ፡ ባንድ ፡ ችንካር ፡ በጀርባው ፡ እስኪ
ወጣ ፡ ቸንከሩት ፡፡ መላእክት ፡ ግን ፡ በደረቱና ፡
በጀርባው ፡ የፈሰሰውን ፡ ደም ፡ በእሳት ፡ ጽዋ ፡ ተቀ
በሉት ፡፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ እጆቹ ፡ ከመስቀሉ
ዳርቻ ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ እጆቹን ፡ በገመድ ፡
እየጐተቱ ፡ በሁለት ፡ ችንካር ፡ ቸንከሩት ፡፡

፲ ፤ መላእክት ፡ ግን ፡ የእጆቹን ፡ ደም ፡ በእሳት ፡
ጽዋ ፡ ተቀበሉት ፡፡ የታመሙትን ፡ በእጆቹ ፡ ስለ ፡
አዳናቸው ፡ ፈንታ ፡ በእጆቹም ፡ ለምጻሞችን ፡ ስለ
አዳናቸው ፡ ፈንታ ፡፡ የዕውሮችን ፡ ዐይን ፡ በእጆቹ
ስለአዳናቸው ፡ ፈንታ ፤ በእጆቹም ፡ የሞቱትን ፡ ስለ
አስነሣቸው ፡ ፈንታ ፡ ቸንከሩት ፡፡

## ሁለተኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ ወደሱ ፡ እየማለደ ፡ መጥቶ ፡
እጅ ፡ ነሣው ፡ ለመነውም ፡፡ ልጄን ፡ ድዳ ፡ ደን
ቆሮ ፡ የሆነ ፡ ጋኔን ፡ ይዞታልና ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡
እዘንልኝ ፡ ብሎ ፡ ማለደው ፡፡ ዘወትር ፡ እየጣለው ፡
ፈጽሞ ፡ ያመዋል ፡፡ ይልቁንም ፡ ከገደል ፡ ከእሳትና ፡
ከውሃ ፡ ይጥለዋል ፡፡ ወደ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርትህም ፡
ወሰድኩት ፡ ማዳን ፡ ተሳናቸው ፡ አለው ፡፡

፩ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም መልሶ ፡ ሃይማኖት ፡ የሌ
ላት ፡ ክፉ ፡ ትውልድ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ከናንተ
ጋራ ፡ እኖራለሁ ። እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ እታገሣችኋለሁ
ብሎ ፡ ወደኔ ፡ አምጡት ፡ አላቸውና ፡ ወደሱ ፡ አመጡለት
፪ ፤ ይህም ፡ ጋኔን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ባየው
ጊዜ ፡ ከምድር ፡ ጣለው ፡ አማታው ፡ አራገጠው ፡
አሸናው ።
፫ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሲራራቅ
ባየ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ጋኔን ፡ ተቆጣው ። ከሱ ፡ ትወጣ
ዘንድ ፡ ዳግመኛም ፡ ወደሱ ፡ እንዳትመለስ ፡ አዝ
ሃለሁ ፡ አለው ። ብዙ ፡ ጊዜም ፡ አስጨንቆ ፡ ሦስት ፡
ጊዜም ፡ አማቶ ፡ ለቆት ፡ ሄደ ።
፬ ፤ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ሞተ ፡ እስኪሉ ፡ ድረስ ፡ እንደ
በድንም ፡ ሆነ ። ጌታችን ፡ ኢየሱስም በእጁ ፡ ይዞ ፡ አን
ሥቶ ፡ አቆመው ። አይሁድ ፡ ግን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱ
ስን ፡ እጆቹን ፡ በሁለት ፡ ችንካሮች ፡ ቸነከሩት ።
፭ ፤ ዕውር ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ አምጥተው ፡ በእጁ ፡
ይዳስሰው ፡ ዘንድ ፡ ለመኑት ። ጌታችን ፡ ኢየሱስም
ይህን ፡ ዕውር ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ ከሰው ፡ ለይቶ ፡
ዐይኖቹን ፡ በምራቁ ፡ ቀብቶ ፡ ምን ፡ ታያለህ ፡ አለው
እሱም ፡ ሰው ፡ ዕንጨት ፡ መስሎ ፡ ሲመላለስ ፡ አያለሁ
አለው ። ዳግመኛም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ዐይና
ቹን ፡ ዳሰሰውና ፡ ብሩህ ፡ ሁኖ ፡ አየ ።
የዳዊት ፡ ልጅ ፡
፮ ፤ እቤቱ ፡ እስኪገባ ፡ ድረስ ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡
ኢየሱስ ፡ ይቅር ፡ በለን ፡ እያሉ ፡ በጉዳና ፡ የተከተ

ሎትን ፡ ሁለቱንም ፡ ዕውሮች ፡ አዳናቸው ። በጐዳና ተቀምጠው ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ኢየሱስ ፡ ይቅር ፡ በለን ፡ እያሉ ፡ የጮሁትን ፡ ሁለቱንም ፡ ዕውሮች ፡ አዳናቸው ። ሌሎችንም ፡ ዕውሮች ፡ በእጁ ፡ ዳስ ሳቸውና ፡ አዳናቸው ።

፳ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ እንደ ፡ ሃይማኖታችሁ ፡ ይደረግላችሁ ፡ አላቸው ። ያን ፡ ጊዜውን ፡ ዐይኖቻቸው ድነው ፡ አዩ ። ልምሾ ፡ የሆኑትን ፡ አንካሶችንም ፡ ሠርቀ ፡ ወርኅ ፡ እያየ ፡ የሚጥላቸውን ፡ በሽተኞች ፡ ደዌ ፡ የጸናባቸውንም ፡ ጋኔን ፡ የሚጥላቸውንም ፡ አጋን ንት ፡ ያደሩባቸውንም ፡ በእጁ ፡ እየዳሰሰ ፡ አዳናቸው ። አይሁድ ፡ ግን ፡ ዕውር ፡ ያበራውን ፡ ድዉይ ፡ የፈወሰ ውን ፡ ጌታ ፡ እጆቹን ፡ በ፪ት ፡ ችንካር ፡ ቸንከሩት ።

## ሦስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ናይን ፡ በምትባለውም ፡ አገር ፡ ያንድ ፡ የድኃ ልጅ ፡ (ቃሬዛ) በድን ፡ አገኘ ፡ ከሷም ፡ ጋራ ፡ ብዙ የሀገር ፡ ሰዎች ፡ (ለቀስተኞች ) ነበሩ ።

፪ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ባያት ፡ ጊዜ ፡ አዘነላት ። አታልቅሺም ፡ አላት ። ቀርቦ ፡ በድኑን ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ አንተ ፡ ብላቴና ፡ ተነሥ ፡ አለው ። ይኸውም ፡ የሞተው ብላቴና ፡ ተነሥቶ ፡ ተቀምጦ ፡ ተናገረ ። ለእናቱም ፡ ሰጣት አይሁድ ፡ ግን ፡ ሙት ፡ ያስነሣውን ፡ ርኅሩኅን ፡ እሱን ጌታን ፡ እጆቹን ፡ በሁለት ፡ ችንካር ፡ ቸንከሩት ።

## ዐራተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ ይህን ፡ ሲነጋገር ፡ ኢያኢሮስ ፡ የሚባል ፡ አንድ አገረ ፡ ገዥ ፡ መጣ ። ጌታችን ፡ ኢየሱስንም ባገኘው ጊዜ ፡ ሰገደለት ። አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ ልጄ ፡ ሞተችብኝ ነገር ፡ ግን ፡ መጥተህ ፡ እጅህን ፡ በላይዋ ፡ ጫነው ፡ ልጄም ፡ ትድንልኛለች ፡ ብሎ ፡ ማለደው ።

፪ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ተነሥቶ ፡ ሄደ ። ከደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተከተሉት ። ከሹሙም ፡ ቤት ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ለቀስተኞች ሲያለቅሱ ፡ ሲታወኩ ፡ አገኛቸው ።

፫ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ከዚህ ፡ ወግዱ ፡ አላ ቻውና ። ብላቴናዪቱ ፡ ተኝታለች ፡ እንጂ ፡ አልሞ ተችም ፡ አላቸው ፡ ሕዝቡም ፡ ሳቁበት ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ። ገብቶ ፡ እጅዋን ፡ ይዞ ፡ ጣቢታ ፡ ተነሺ ፡ አላት ። ተነሥታም ፡ ተመላለሰች

፬ ፤ እናት ፡ አባቷንም ፡ የምትበላውን ፡ ስጧት ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ። ከእስራኤልም ፡ ወገን ፡ የሚሆን አንድ ፡ ምዉት ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ አስነሣው ። ሌሎ ችንም ፡ የሞቱትን ፡ ሰዎች ፡ አስነሣቸው ። በእጆቹ የተደረጉት ፡ ተአምራቶች ፡ ብዙ ፡ ናቸው ።

፭ ፤ አይሁድ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ተአምራት አድራጊውን ፡ እጆቹን ፡ በሁለት ፡ ችንካር ፡ ቸነከ ሩት ። እግሮቹንም ፡ ባንድ ፡ ችንካር ፡ አንዱን ፡ ካንዱ

ጋራ ፡ አንድ ፡ አድርገው ፡ ቸነከሩት ። መላእክትም የእግሮቹን ፡ ደም ፡ በእሳት ፡ ጽዋዕ ፡ ተቀበሉት ። በቤተ ፡ መቅደስና ፡ በየአዳራሾች ፡ ስለ ፡ ተመላለሱ ፈንታ ። ከዳን ፡ እስከ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ በአይሁድ ፡ አገሮች ፡ ስለ ፡ ተመላለሱ ፈንታ ።

፰ ፤ ማዕበሉ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ድረስ ፡ የሚወጣ የሚጮኽ ፡ ጥልቁንም ፡ ባሕር ፡ በመርከብና ፡ ያለ መርከብ ፡ ስለ ፡ ሄዱ ፡ ፈንታ ። በየብስ ፡ እንደ ሚሄድ ፡ ሰው ፡ በአዟሪ ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ ዕውነት ፡ ስለ ፡ ሄዱ ፡ ፈንታ ። በአይሁድ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሞ ፡ የጠፉትን ፡ በጎች ፡ ለመፈለግ ፡ በየወሩ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ስለ ፡ ዞረ ፡ ፈንታ ፡ ቸነከሩት ።

፱ ፤ መከራም ፡ ቢያጸኑበት ፡ አልተቀየማቸውም ። ዕውነትን ፡ ለሚፈርድ ፡ ቸርነትን ፡ መለስ ፡ እንጂ በመቸንከሩም ፡ የሞት ፡ ችንካርን ፡ አጠፋልን ። ሔዋን ፡ በእግሮቿ ፡ ወደ ፡ ዕፀ ፡ በለስ ፡ ስለ ፡ ተመላለሰች ፡ እጆቹንና ፡ እግሮቹን ፡ በመቸንከር ፡ ከፍ ኗልና ። በእጆቿም ፡ የበለስን ፡ ፍሬ ፡ ስለ ፡ ቆረጠች ፈንታ ፡ በእውነት ፡ **የእግዚአብሔር ፡ ቃል** ፡ በሥ ጋው ፡ ከመስቀል ፡ ዕንጨት ፡ ጋራ ፡ ተቸነከረ ።

## አምስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

**፩ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስንም ፡ በዕንጨት ፡ መስቀል** ላይ ፡ ሰቀሉት ። ፊቱን ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ቀኝ ፡

እጁን ፡ ወዲ ፡ ደቡብ ፡ ግራ ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ አድርገው ፡ በዚያ ፡ ሰቀሉት ።

፪ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥጋ በሰቀሉ ፡ ጊዜ ፡ ሥጋን የተዋሐደ ፡ ቃልንም ፡ ሰቀሉት ። በሥጋና ፡ በቃል ፡ መካከል ፡ ምንም ፡ ምን ፡ መለያየት ፡ የለም ። ከሱም ጋራ፡ሁለቱን ፡ ወንበዴዎች ፡ አንዱን ፡ በቀኙ ፡ አንዱን በግራው ። በመካከላቸው ፡ጌታችን ፡ ኢየሱስን አድርገው ፡ ሰቀሉ ። ሕዝቡም ፡ እሱም ፡ እንደነሱ ፡ ወንበዴ ፡ ነው ፡ ይሉት ፡ ዘንድ ፡ ሰቀሉት ።

፫ ፡ እሱ ፡ ግን ፡ ወዶ ፡ ከወንበዴዎች ፡ ጋራ ፡ በዕንጨት ፡ መስቀል ፡ ላይ ፡ ተሰቀለ ። ልዑላን ፡ መላእክት ፈርተው ፡ በፊቱ ፡ ራሳቸውን ፡ የሚያዋርዱለት ። እሱ ፡ በሚሰቅሉት ፡ ፊት ፡ መከራ ፡ ለመቀበል ፡ ራሱን ፡ አዋረደ ። በከሃሊነቱ ፡ ሰማይና ፡ ምድርን ፡ ያጸና ፡ ከግርማውም ፡ የተነሣ ፡ ሰማያትና ፡ ምድር ፡ የሚንቀጠቀጡለትን ፡ እሱን ፡ ደካማ ፡ ዕንጨት ፡ ተሸከመው ።

፬ ፡ እሱ ፡ ግን ፡ ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያስታርቀን ፡ ዘንድ ፡ ከሰማይ ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ ከምድር ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ በዕንጨት ፡ ላይ ፡ ተሰቀለ ። ኃጢአትን ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ በዕንጨት ፡ ላይ ፡ ተሰቀለ ። እሱም ፡ ስለኛ ፡ በሥጋው ፡ በዕንጨት ፡ መስቀል ፡ ተሰቀለ ። ከኃጢአታችንም ፡ ይለየን ፡ ዘንድ ። በቸርነቱ ፡ ያድነን ፡ ዘንድ ፡ ተሰቀለ ።

፭ ፤ እሱ ፡ ግን ፡ ሰማይን ፡ ይቀድስ ፡ ዘንድ ፡
በዕንጨት ፡ መስቀል ፡ ላይ ፡ ተሰቀለ ። በአየር ፡
ያሉ ፡ አጋንንትንም ፡ ያወርዳቸው ፡ ዘንድ ፤ ሙሴ
አርዌ ፡ ብርትን ፡ በገዳም ፡ እንደ ፡ ሰቀለው ፡ እሱም
በዕንጨት ፡ ላይ ፡ ተሰቀለ ። በሱ ፡ ያመነ ፡ ሁሉ ፡
ይድናል ፡ እንጂ ፡ እንዳይጐዳ ። የክብር ፡ ባለቤት ፡
እሱ ፡ ግን ፡ ስለኛ ፡ በዕንጨት ፡ ላይ ፡ ተሰቀለ ።
፮ ፤ አውቀውስ ፡ ቢሆን ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡
ጌታን ፡ ባልሰቀሉትም ፡ ነበር ። ሰማይ ፡ ዙፋኑ ፡
ምድር ፡ በእግሮቹ ፡ የተረገጠች ፡ ስትሆን ፡ ስለኛ ፡
በዕንጨት ፡ ተሰቀለ ።

፯ ፤ እሱ ፡ ግን ፡ ተጠብቆለት ፡ ስላለ ፡ ስለ ፡
ደስታው ፡ ምዕመናን ፡ ደኅንነት ፡ የመስቀልን ፡
መከራ ፡ ንቆ ፡ አቃሎ ፡ ተቀበለ ፡ ኀፍረትንም ፡ ናቃት ።
ለተሰቀለ ፡ ለሱ ፡ የማይሰግድ ፡ ቢኖር ፡ የተለየ ፡
የተወገዘ ፡ ይሁን ። እሱ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ዓለሙ ፡ ደኅን
ነት ፡ በማዕዘነ ፡ ምድር ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወደታች ፡ ወደ
ግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ሆኖ ፡ እንደመጋረጃ ፡ በዕንጨት
ላይ ፡ ተሰቀለ ። እኛን ፡ ከጻድቃን ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡
ያደርገን ፡ ዘንድ ፡ እሱ ፡ ከበደለኞች ፡ ጋራ ፡ ተቆጠረ ።
፰ ፤ ጲላጦስና ፡ አይሁድም ፡ በደሉን ፡ የሚና
ገር ፡ መጽሐፍ ፡ ከራሱ ፡ በላይ ፡ ጽፈው ፡ አኖሩ ፡
ጽሕፈቱም ፡ ይህ ፡ የናዝሬቱ ፡ ሰው ፡ ኢየሱስ ፡ የአይ
ሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ነው ።

፱ ፤ ይህችንም ፡ መጽሐፍ ፡ ከአይሁድ ፡ ወገን ፡ የነበቧት ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ የሰቀሉበት ፡ ቦታ ፡ ላገር ፡ አቅራቢያ ፡ ነው ። ጽሕፈቱም ፡ በጽርዕና ፡ በሮማይስጥ ፡ በዕብራይስጥ ፡ ነው ። የካህናቱም ፡ አለቆች ፡ ጲላጦስን ፡ እኔ ፡ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ነኝ ፡ ይላል ፡ ብለህ ፡ ጻፍ ፡ እንጂ ፡ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ አትጻፍ ፡ አሉት ።

፲ ፤ ጲላጦስም ፡ መልሶ ፡ እኔ ፡ የጻፍኩትን ፡ ጽፌያለሁ ፡ ይኸውም ፡ ጲላጦስ ፡ ጽፎ ፡ ከራሱ ፡ በላይ ፡ ያኖረው ፡ በደሉን ፡ የሚናገር ፡ መጽሐፍ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ አጋንንት ፡ የጻፉትን ፡ የዕዳችንን ፡ መጽሐፍ ፡ ያጠፋልን ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

፲፩ ፤ በጐዳና ፡ የሚሄዱ ፡ ሁሉ ፡ ራሳቸውን ፡ እየነቀነቁ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ሰደቡት ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ አፍርሼ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ እሠራዋለሁ ፡ የምትል ፡ ሆይ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ከሆንክ ፡ ራስህን ፡ አድን ፡ እስኪ ። ከመስቀልምህም ፡ ውረድ ፡ እያሉ ፡ እንደዚህም ፡ ጸሐፍትና ፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡ ሌላውን ፡ ያድናል ፡ ራሱን ፡ ለማዳን ፡ ግን ፡ አይችልም ፡ እያሉ ፡ ይዘብቱበት ፡ ነበር ።

፲፪ ፤ የእሥራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሆነ ፡ እነሆ ፡ አሁን ፡ ከመስቀሉ ፡ ይውረድ ፡ አይተን ፡ እንመንበት ፡ አሉ ። እሱ ፡ ግን ፡ በከሃሊነቱና ፡ በሥልጣኑም ፡ እነሱ ፡ እንደ ፡ ተገዳደሩት ፡ ከመስቀሉ ፡ ይወርድ ፡ ዘንድ ፡ በቻለ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ አዳ

ምን ፡ በሞቴ ፡ አድንሃለሁ ፡ ብሎ ፡ የነገረው ፡ ቃል፡ አይታበልምና ፡ ስለዚህ ፡ ከመስቀሉ ፡ አልወረደም ።

፲፫ ፤ ዳግመኛም ፡ በእግዚአብሔር ከታመነ ፡ እነሆ ፡ ይወደው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አሁን ፡ ያድነው ። የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ ይላልና ። ከሱም ፡ ጋራ የተሰቀሉት ፡ ያሽሟጥጡት ፡ ነበር ፡ አይሁድም ፡ በመነጸጸር ፡ ይህ ፡ በመካከል ፡ የተሰቀለው ፡ ንጉሥ ነው ፡ እያሉ ፡ ተጠቃቀሱበት ።

፲፬ ፤ እነዚህም ፡ በግራው ፡ በቀኙ ፡ የተሰቀሉት ፡ ሹማምንቶቹ ፡ ናቸው ። እነሱ ፡ እንደዚህ ፡ ሲሰድቡት እሱ ፡ ግን ፡ በኃጢአት ፡ ሳሉ ፡ እንዳይሞቱ ፡ ስለነሱ ለመነላቸው ።

፲፭ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ አባቴ ፡ ያለዕውቀት ይሠሩታልና ፡ ይቅር ፡ በላቸው ፡ አለ ። በዚህም ፡ ልመ ናው ፡ ንስሐ ፡ የሚገቡበት ፡ ዐርባ ፡ ዘመን ፡ ተሰጣቸው ። እነሱ ፡ ግን ፡ ንስሐ ፡ አልገቡም ፡ የገቡም ፡ አሉ ።

፲፮ ፤ ከሱም ጋራ የተሰቀለው ፡ አንዱ ፡ ወንበዴ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሆንክስ ፡ እኛንም ፡ ራስህንም ፡ አድን ፡ ብሎ ፡ ሰደበው ። ሁለተኛውም ፡ ወንበዴ ፡ እየገሠ ፀው ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ፍርድ ፡ ተፈርዶብን ፡ ሳለን እግዚአብሔርን ፡ አትፈራውምን ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ለኛስ ፡ በሚገባ ፡ ተፈርዶብናል ፡ እንደ ፡ ሥራችንም ተቀብለናል ። ይህ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ የሠራው ፡ የለም ።

፲፮ ፤ ይህን ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ ዓይኖቹ ፡ ተገልጸውለት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ በጌትነቱ ፡ ዙፋን ፡ ተቀምጦ ፡ አየ ። መላእክትም ፡ ዙሪያውን ፡ ቁመው ፡ አየ ፡ አቤቱ ፡ በጌትነትህ ፡ በመጣህ ፡ ጊዜ ፡ አስበኝ አለው ። ዛሬ ፡ አስበኝ ፡ አላለውም ። ኃጥአንን ፡ የሚቀበል ፡ ንስሐ ፡ የገቡትን ፡ የሚወድ ፡ ጌታችን ፡ ግን በቸርነቱ ፡ ብዛት ፡ ዛሬ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ በገነት ፡ እንድትኖር ፡ በእውነት ፡ እነግርሃለሁ ፡ አለው ።

፲፯ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስንም ፡ ከሰቀሉት ፡ በኋላ ፡ ልብሱን ፡ ወስደው ፡ እያንዳንዱ ፡ ጭፍራ ፡ ላራት ፡ ከፈሉት ። ስፌት ፡ የሌለባት ፡ ሥረ ፡ ወጽ ፡ የምትሆን ፡ ቀሚሱን ፡ ግን ፡ ዕጣ ፡ ተጣጥለን ፡ ለደረሰው ይድረሰው ፡ እንጂ ፡ አንቁረጠው ፡ አንቅደደው ፡ ተባባሉ ። ልብሴን ፡ ለራሳቸው ፡ ተካፈሉት ፡ በቀሚሴም ፡ ላይ ፡ ዕጣ ፡ ተጣጣሉ ፡ ብሎ ፡ መጽሐፍ ፡ የተናገረው ፡ ይደርስ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ። ጭፍሮቹም ፡ እንደዚሁ ፡ አደረጉ ።

## ስድስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ እናቱ ፡ እመቤታችንም ከእኅቷ ፡ ከቀለዮጳ ፡ ልጅ ፡ ከማርያምና ከመግደላዊት ማርያም ፡ ከመስቀሉ ፡ አጠገብ ፡ ቆማ ፡ ሆድ ፡ በሚያቃጥል ፡ አንጀት ፡ በሚቈራርጥ ፡ በጽኑዕ ፡ ኀዘን ፡

እየጮኸች ፡ ታለቅስ ፡ ነበር ። ከመስቀሉ ፡ ሥር ፡ ወደቀች ፡ ለመሞትም ፡ ደረሰች ።

፮ ፤ ፈቱም ፡ የመላእክት ፡ አለቆች ፡ መጥተው ፡ አረጋጓት ፡ አጽናኗት ፡ እሷ ፡ ግን ፡ ልቅሶ ፡ መተ ውና ፡ መጽናናትንም ፡ አልቻለችም ። አባቷ ፡ ዳዊ ትም ፡ እሳት ፡ በሆነ ፡ ፈረስ ፡ ተቀምጦ ፡ መጥቶ ፡ አጽናናት ። እሷ ፡ ግን ፡ ልቅሶ ፡ መተውን ፡ መጽናና ትን ፡ እምቢ ፡ አለች ።

፯ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ እናቱንና ፡ የሚወደ ውን ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩን ፡ (ዮሐንስን ፡) ቁመው ፡ ባያቸው ፡ ጊዜ ። እናቱን ፡ እነሆ ፡ ልጅሽ ፡ አላት ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩንም ፡ እነሆ ፡ እናትህ ፡ አለው ፡ ይህም ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ የደሙን ፡ መፍሰስ ፡ የጎ ኑን ፡ መወጋት ፡ የልጅዋን ፡ ሞት ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ከኀዘን ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ እንዳትሞት ፡ ከዚ ያን ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ወስዶ ፡ ከቤቱ ፡ አኖራት ።

፰ ፤ እቤትም ፡ ከገባች ፡ በኋላ ፡ መጽናናትን ፡ ልቅሶ መተውንም ፡ እምቢ ፡ አለች ። እስከ ፡ ሦስት ፡ ቀንም ድረስ ፡ እህል ፡ ውሃ ፡ አልቀመሰችም ።

## ሰባተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ጌቶቼ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፤ አደራ እላችኋለሁ ። እመቤቴ ፡ ማርያም ፡ ሐንችንም ፡ እማልድሻለሁ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ግቢልኝ ፡ እልሻለሁ ። በነፍሱና ፡ በሥጋው ፡ በተቀበላቸው ፡ መከራዎች ፡

ሁሉ ። በመቸንከሩም ። የእሾህ ፡ አክሊል ፡ ተቀ
ዳጅቶ ፡ በመሰቀሉ።

፪ ፤ በሞቱም ፡ ወደ ፡ ሲኦልም ፡ በመውረዱ ።
በጦር ፡ በመወጋቱ ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ
በመቀበሩ ። ኃጢአቴን ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ ትሉኝ ፡
ዘንድ ። ከኃጢአትም ፡ ፍዳ ፡ ታድኑኝ ፡ ዘንድ ።
ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

## አንደኛ ፡ የዐርብ ፡ ተአምር ።

፩ ፤ በወንጌል ፡ እንደተነገረ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ
ክርስቶስ በእጆቹ ፡ ያደረገው ፡ ተአምር ፡ ይህ ፡ ነው ።

፪ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ከተራራው ፡ ሲወርድ ፡
ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተከተሉት ። አንድ ፡ ለምጻም ፡ ሰው ፡
መጥቶ ፡ እየሰገደ ፡ ማለደው ፡ አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ ከወ
ደድክስ ፡ እኔን ፡ ማዳን ፡ ይቻልሃል ፡ አለው ።

፫ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ ዳስ
ሰው ፡ ልትድንም ፡ እወዳለሁ ፡ አለውና ፡ ከለምጹ
ዳነ ፡ ለምጻሞችንም ፡ ሁሉ ፡ አዳናቸው ።

፬ ፤ አይሁድ ፡ ግን ፡ እሱን ፡ እጆቹን ፡ በሁለት ፡
ችንካር ፡ ቸነከሩት ። የጴጥሮስንም ፡ አማት ፡ ጌታ
ችን ፡ ኢየሱስ ፡ በእጆቹ ፡ ዳሰሳት ። ከገለማ ፡ ሆድ
ዋም ፡ አዳናት ፡ ተነሥታም ፡ ተከተለቻቸው ።

፭ ፤ ድዳ ፡ ደንቆሮም ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ አምጥተው ፡
ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ በእጁ ፡ ይዳስሰው ፡ ዘንድ ፡

ማለዱት ። ከሰው ፡ ዘንድ ፡ ለይቶ ፡ በእጁ ፡ ዠሮውን ዳሰሰው ። ምራቁንም ፡ በላዩ ፡ ትፍ ፡ ብሎ ፡ አንደበቱን ፡ ዳሰሰው ። ወደ ፡ ሰማይም ፡ ተመልክቶ ፡ አባቱን ፡ ኤፍፍታሔ ፡ እያለ ፡ ማለደ ።

፮ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ አንደበቱ ፡ ቀንቶ ፡ ተናገረ ፡ ዠሮውንም ፡ በእጁ ፡ ዳሰሰውና ፡ ተከፍቶለት ፡ ሰማ ። ብዙዎቹን ፡ ድዳ ፡ ደንቆሮ ፡ የሆኑትን ፡ በእጁ ፡ ዳሰ በቃሉ ፡ ተናግሮ ፡ በምራቁ ፡ ቀብቶ ፡ አዳናቸው ። ሁሉ ንተናው ፡ ሕይወት ፡ ነውና ። አይሁድ ፡ ግን ፡ እሱን እጆቹን ፡ በሁለት ፡ ችንካሮች ፡ ቸነከሩት ።

## ሁለተኛ ፡ ተአምር ።

፩ ፤ በልብሱ ፡ የተደረገው ፡ ተአምር ፡ ይህ ፡ ነው ጌንሴሬጥ ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ በማለዱት ፡ ጊዜ ፡ ልብሱን ፡ ዳሰው ፡ ብዙ ፡ የሚሆኑ ፡ ሕሙማን ፡ ድውያንን ፡ በልብሶቹ ፡ አዳናቸው ።

፪ ፤ ከ፲፪ ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ ደም ፡ የሚፈሳት ፡ ሴት ከወደ ፡ ኋላው ፡ መጥታ ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስን ፡ የልብሱን ፡ ጫፍ ፡ ዳሰሰችው ። በልቡናዋ ፡ የልብሱን ፡ ጫፍ ፡ የዳሰስኩ ፡ እንደሆን ፡ ከደዌ ፡ እድናለሁ ፡ ብላ አስባለችና ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ አይቶ ፡ ልጄ ፡ እመኝ ፡ ሃይማኖትሽ ፡ አዳነሽ ፡ አላት ። እሷም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ፈጥና ፡ ዳነች ። አይሁድ ፡ ግን ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስን ፡ አጥንቶች ፡ በዘንግ ፡ ቈጠሯቸው ።

## ምስተኛ ፡ ተአምር ።

፩ ፤ በዕለተ ፡ ዐርብ ፡ የተደረገው ፡ ተአምር ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ፀሐይ ፡ ታጣ ፡ ጨረቃም ፡ ጨለመ ፡ በከበረ ፡ ስቅለቱም ፡ ጊዜ ፡ ለአይሁድ ፡ እንዳያበሩ ከዋክብት ፡ ብርሃናቸውን ፡ ሠወሩ ።

፪ ፤ ጨረቃም ፡ ምሉ ፡ ሳለ ፡ ብርሃኑን ፡ አላበራም ። ፀሐይም ፡ ጨለመ ፡ ከወንበዴዎች ፡ ጋራ ፡ በዕንጨት ላይ ፡ ተሰቅሎ ፡ እየተጨነቀ ፡ መከራ ፡ የሚቀበል ፡ የፈጣሪያቸውን ፡ ዕርቃን ፡ እንዳያዩ ፡ ሁሉም ጨለማ ፡ ሆኑ ። ከ፮ ፡ ሰዓት ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ጨለማ ፡ ሆነ ።

፫ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ ተአምራት ፡ በፊታቸው ፡ ሲያደርግ ፡ አይሁድ ፡ አላመኑበትም ።

## አርኬ ፡ ዘዐርብ ።

፩ ፤ በትርጓሜው ፡ የራስ ፡ ቅል ፡ ከሚባል ፡ እስከ ቀራንዮ ፡ ድረስ ፡ ያለፍርድ ፡ መስቀልን ፡ ያሸከሙህ ፡ ቅን ፡ የሆነ ፡ የሞት ፡ ፍርድን ፡ የተሸ

ከመ ፡ አርአዩ ፡ አምሳል ፡ የሆንህ ፡ ክርስቶስ ፡ ብዙ ፡ ኃጢአቴን ፡ ለማስተሥረይ ፡ አቤቱ ፡ ነፍሴ ፡ እንደ ፡ አይሁድ ፡ ነፍስ ፡ በልቅሶ ፡ እንዳትኖር ፡ ጸጋህ ፡ ትድረስ ።

፪ ፤ በበትርና ፡ በከዘራ ፡ አጅንም ፡ በማጠፍ ፡ በድካምህ ፡ ጊዜ ፡ አይሁድ ፡ የመቱህ ፡ ከባድ ፡ መስቀል ፡ በመሸከም ፡ የደከምህ ። አቤቱ ፡ እንደ ፡ ዕዳዬ ፡ አትፍረድብኝ ፡ ወንድምም ፡ ዘመድም ፡ አንተ ፡ ነህና ።

፫ ፤ ከወይንና ፡ ከሐሞት ፡ ጋራ ፡ የተቀላቀለ ፡ መራራንና ፡ ክርቤን ፡ ያጠጡህ ። የወንበዴዎች ፡ መጠጥ የወይን ፡ ጠጅን ፡ ያላጠጡህ ፡ እንደ ፡ ዲያብሎስና እንደ ፡ አለቆቹ ፡ የታሠርሁ ፡ እንዳልሆን ፡ የጴጥሮስ ፈጣሪ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ከኃጢአት ፡ ዘወትር ፡ ፍታኝ ።

፬ ፤ ክንድ ፡ ያኽል ፡ ከመስቀል ፡ በተረፈ ፡ በብረት ፡ ላይ ፡ በተገረፈ ፡ ዠርባህ ፡ የሳቡህ ። እጆችህን የተቸነከርህ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤ ዘወትር ፡ እታመን ብሃለሁና ፡ ዮሐንስ ፡ እንድንታችንን ፡ እንደ ፡ ጳፈ ከአንተና ፡ ከአብ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ አድርገኝ ።

፭ ፤ እግሮችህን ፡ አንዱን ፡ ከሁለተኛው ፡ ጋራ አጠጋግተው ፡ የቸነከሩህ ። የልጆቹና ፡ የአዳም ፡ መድኃኒት ፡ እግሮችህን ፡ የተቸነከርህ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤ ወደኔ ፡ መጥተው ፡ ከመውደቅ ፡ በእጃቸው ፡ ያነሱኝ ፡ ዘንድ ፡ መላእክትን ፡ እዘዛቸው ።

፮ ፤ ቀማኞች ፡ ከሆኑ ፡ ከንጥጦስ ፡ ጋራ ፡ የተሰቀልህ ። አይሁድ ፡ በማይገባ ፡ ስድብ ፡ የሰደቡህ ። መን

ገዶቹ ፡ ልጆችም ፡ የሰደቡህ ፡ ከሞት ፡ ጦር ፡ በመ ስቀልህ ፡ ሰውረኝ ። በዚህ ፡ ጦር ፡ ገኘ ፡ አንተ ፡ ተወግተሃልና ። ስቅለትህን ፡ የሚወድ ፡ አብ ፡ ኃጢ አታቸውን ፡ ያቀል ፡ ዘንድ ።

፷ ፤ ለሰቀሉህ ፡ ወገኖች ፡ የለመንህ ፡ በዕለተ ፡ ዐርብ ፡ የተሠዋህ ፡ የወንጌላዊ ፡ ላህም ፡ ክርስቶስ

ሆይ ፤ ኮከብ ፡ ስጦታህ ፡ እንደ ፡ ኮከብ ፡ ወጥቶ ፡ በተደነቀ ፡ ብርሃኑ ፡ ብዛት ፡ እኔን ፡ ባሪያህን ፡ ደስ ፡ ያሰኘኝ ።

፷፩ ፤ ወታደሮች ፡ ልብስህን ፡ የገፈፉህ ፡ የራ ስህንም ፡ ኩፌት ፡ ከበትርና ፡ ከጫማዎች ፡ ጋራ ፡ ስፌት ፡ ከሌላት ፡ ከምትገናጸፋት ፡ ልብስህም ፡ ጋራ ፡ የወሰዱብህ ። በእሳታዊ ፡ ደንጊያ ፡ ላይ ፡ ከመ ስቀል ፡ አድነኝ ። በደለኛ ፡ በመስቀል ፡ ይሞታልና ።

፷፪ ፤ ባስታራቂ ፡ ሕግ ፡ ልጅሽ ፡ በመካከል ፡ ቁሞ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ከምድር ፡ በላይ ፡ የተሰቀለ ፡ ሁኖ ፡ በአየሺው ፡ ጊዜ ፡ ያለቀስሽ ። እመቤቴ ፡

ማርያም ፡ ሆይ ፤ ከዘማ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ሁኛለሁና ፡ ይቅርታን ፡ አብዝተሽ ፡ ይቅር ፡ በይኝ ።

፷፫ ፤ በመስቀልና ፡ በችንካር ፡ መከራ ፡ የተቀበልህ ሁነህ ፡ በአዩ ፡ ጊዜ ፡ የሰማይ ፡ መላእክት ፡ ከቆመ ፡ መስቀል ፡ እግር ፡ በታች ፡ ተነጸፉ ። የሥጋህ ፡ መራቆትንም ፡ ፈጽመው ፡ ይሠውሩ ፡ ዘንድ ፡ የፀሐይ ሠሌዳ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ጨለመ ፡ የጨረቃ ፡ ሠሌዳም ፡ ደም ፡ እስኪሆን ፡ ድረስ ፡ ቀላ ።

፲፩ ፤ ሁለቱ ፡ ቀማኞች ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ያሽሟጠጡህ ። በቀኝህ ፡ የተሰቀለ ፡ ቀማኛ ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ ፈጣሪ ፡ ኃይልህን ፡ በመንግሥትህ ፡ አስበኝ ፡ ብሎ በጸጸት ፡ ቃል ፡ ወዳንተ ፡ ጮኸ ።

፲፪ ፡ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ ኃጢአቴን አስተሥርይልኝ ፡ በደሎቼንም ፡ አጥፋልኝ ። የኔ ፡ የባሪያህ ፡ ጠላቶቼንና ፡ የጥንት ፡ ጠላቶቼን ፡ አስወግድልኝ

## የቀዳሚት ፡ ድርሳነ ፡ ማሕየዊ ።

## አንደኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ በማመን ፡ ሁሉን የሚታደግ ፡ ሁሉን ፡ የሚያድን ፡ የጌታችን ፡ የመድኃኔ ፡ ዓለምን ፡ ሞቱንና ፡ መከራውን ፡ የሚናገር ፡ በዕለተ ፡ ቀዳሚት ፡ የሚነበብ ፡ ድርሳን ፡ ይህ ፡ ነው ።

፪ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ኤሎሄ ፡ ኤሎሄ ፡ ኤልማስ ፡ ሰበቅታኒ ፡ እያለ ፡ አሰምቶ ፡ ተናገረ ። ይህንንም ፡ ማለት ፡ ፈጣሪዬ ፡ ስለ ፡ ምዕመናን ፡ ለምን ፡ ተውከኝ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፫ ፤ እዚያ ፡ የቆሙ ፡ አይሁድ ፡ ግን ፡ ይህስ ፡ ኤልያስን ፡ ይጠራል ፡ አሉ ። ከነዚያም ፡ በትዕቢት ቃል ፡ ኤልያስ ፡ መጥቶ ፡ ያድነው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተዉት ፡ እንየው ፡ አሉ ።

፬ ፤ ጌታችን ፡ ግን ፡ ፈጣሪዬ ፡ ለምን ፡ ትተወኛለህ ፡ ያለው ፡ ከሰማይ ፡ ረዳት ፡ ሽቶ ፡ አይደለም ።

የብዙ ፡ ብዙ ፡ የሚሆን ፡ የመላእክት ፡ ፈጣሪያቸው ፡ ነውና ።

፮ ፤ ጌታችን ፡ ፈጣሪዬ ፡ ለምን ፡ ትተወኛለህ ፡ ማለቱ ፡ ግን ፡ በበቀል ፡ ያገኘንን ፡ እርግማን ፡ ያር ቅልን ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ከአዳም ፡ ዠምሮ ፡ ያገኘን መከራ ፡ ከኛ ፡ ያርቅ ፡ ዘንድ ፡ አባቱን ፡ ለመነ ፡ እሱን ፡ በመበደላችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከተወን ፡ ከኛ ፡ እንዳንዱ ፡ ራሱን ፡ አንድ ፡ እንደሚያደርግ ፡ ሆኖ ፡ ስለኛ ፡ ይለምን ፡ ዘንድ ፡ እሱ ፡ እኛን ፡ መስሏ ልና ፡ (ሥጋ ፡ መልበሱን ፡ ነው ። )

፯ ፤ ነፍሱን ፡ ከሥጋው ፡ እለያለሁ ፡ ብሎ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በድፍረት ፡ መልአከ ፡ ሞት ፡ ወደርሱ ፡ መጣ ኤሎሂ ፡ ኤሎሄ ፡ ኤልማስ ፡ ሰበቅታኒ ፡ እያለ ፡ ሲና ገር ፡ በሰማው ፡ ጊዜ ፡ የፈራ ፡ መስሎት ፡ በሌላው እንዳሰለመደ ። ኤሎሄ ፡ ኤሎሄ ፡ ኤልማስ ፡ ሰበቅ ታኒ ፡ ማለቱ ፡ መከራን ፡ ያርቅ ፡ ዘንድ ፡ ሙስና ፡ መቃብርን ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ መርገምንም ፡ ከኛ ፡ ይለይ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አላወቀም ፡ ነበርና ። ሰውም ፡ በመሆኑ ፡ በመለኮትነቱም ፡ ክቡር ፡ ንጹሕ ነውና ፡ በኃጢአት ፡ ምክንያት ፡ እሱን ፡ የሚከራከ ርበት ፡ መልአከ ፡ ሞት ፡ ምንም ፡ አላገኘም ። በሰ ውነቱም ፡ በመለኮትነቱም ፡ ንጹሕ ፡ ክቡር ፡ ነውና

፰ ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ መልአከ ፡ ሞትን ፡ ስለ ፡ መደፋፈሩ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እንዳይል ፡ በነፋስ አውታር ፡ አጽንቶ ፡ አሠረው ። ልብሱን ፡ ገለጠ

ለት ፡ እንዲያየውም ፡ አደረገው ፡፡ መላእክትንም ፡ በከበረ ፡ በመስቀሉ ፡ ዙሪያ ፡ አዘንብለው ፡ ወድቀው ፡ ስለአያቸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ እንደሆነ ፡ ተረዳ ፡፡ በክፉ ፡ መከራ ፡ በጽኑ ፡ ፍርሃት ፡ ተይዞ ፡ ከመከራው ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ ላብ ፡ አላበው ፡፡

፰ ፤ ከእሥራቱ ፡ በፈታው ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ላቡን ፡ አጠፋለት ፡፡ መቆምም ፡ በካሣ ፡ ይሆንለት ፡ ዘንድ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ፊት ፡ ቁሞ ፡ እየሰገደ ፡ ማለደ በራሱ ፡ ፈርዶ ፡ አዳምን ፡ ከነልጆቹ ፡ እለቃለሁ ፡ አለ ፡ ሌላ ፡ የሚሰጠው ፡ ካሣ ፡ አጥቷልና ፡፡

፱ ፤ ዳግመኛም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ አሰምቶ ተናገረ ፡፡ ነፍሱንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መንፈ ስ ፡ ቅዱስ ፡አደራ ፡ አለ ፡ በሥልጣን ፡ አንድ ፡ ስለሆኑ ፡፡ ) አባቴ ፡ ነፍሴን ፡ በእጅህ ፡ አደራ ፡ እላለሁ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ አባቱ ነውና ፡፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ያባቱ እጅ ፡ ነውና ፡፡

፲ ፤ ይህም ፡ አደራ ፡ ማለቱ ፡ ስለ ፡ ነፍሱ ፡ አይደለም ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ እኔ ፡ ነፍሴን ፡ ከሥጋዬ ፡ እለያታለሁ ፡ ዳግመኛም ፡ አስነሣታለሁ ፡፡ ያለኔ ፡ ፈቃድ ነፍሴን ፡ ከሥጋዬ ፡ የሚለያት ፡ የለም ፡ ብሏልና ፡ እኔ ፡ በፈቃዴ ፡ ሥጋዬን ፡ ከነፍሴ ፡ ለይቼ ፡ በመቃብር ፡ አኖራታለሁ ፡ እንጂ ፡፡

፲፩ ፤ ዳግመኛም ፡ አስነሣት ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን አለኝ ፡ በመስቀልም ፡ በመቃብርም ፡ አኖራት ፡ ዘንድ ፡ ይቻለኛል ። እኔ ፡ በፈቃዴ ፡ ነፍሴን ፡ ከሥጋዬ ፡ እለያታለሁና ። ነገር ፡ ግን ፡ ነፍሱን ፡ አደራ ፡ በማለቱ ፡ የኛን ፡ ነፍስ ፡ ወዳባቱና ፡ ወደ ፡ መንፈስ ቅዱስ ፡ አደራ ፡ ብሎ ፡ መልኩ ፡ ፈጽሞ ፡ ክፉ ፡ ከሚሆን ፡ ከሞት ፡ እጅ ፡ አዳነን ።

## ሁለተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ትንቢቱ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ተፈጸመ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ መጽሐፍ ፡ የተናገረው ፡ ይደርስ ፡ ዘንድ ። በሙታን፡ልማድ ፡ ውሃ ፡ ጠማኝ ፡ አለ በጽምዕ ፡ አንደበቱ ፡ ደርቋልና ፡ ጉሮሮውም ፡ ተጣግቷልና ። ቀድሞም ፡ በጐዳና ፡ ሲሄድ ፡ በጽምዕ ፡ ደክሟል ። ሰውነቶቹም ፡ በጽምዕ ፡ ታስረዋልና ።
፪ ፤ ምንጭ ፡ ካለበት ፡ ሥፍራ ፡ ተቀምጦ ፡ ከሳምር ፡ ሴት ፡ ውሃ ፡ ለመነ ። ይህቺም ፡ የሳምር ፡ ሴት ፡ አላጠጣችውም ። እኔ ፡ የሳምር ፡ ሀገር ፡ ሴት ስሆን ፡ አንተ ፡ የአይሁድ ፡ ወገን ፡ ስትሆን ፡ እንዴት ፡ እኔን ፡ ውሃ ፡ አጠጪኝ ፡ ትለኛለህ ፡ አለችው እንጂ ። አይሁድ ፡ ከሳምር ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ በሥርዐትና ፡ በባህል ፡ አይተባበሩምና ።

፫ ፤ እሱ ፡ ግን ፡ ለዘለዓለሙ ፡ የማይደርቅ ፡ የሕይወት ፡ ውሃ ፡ ያለው ፡ ባለጸጋ ፡ ፈጣሪ ፡ ነው ። እሱ

ግን ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ሦስት ፡ ሦስት ፡ እንስራ ፡ በሚይዝ ፡ የስድስቱን ፡ ጋኖች ፡ ውሃ ፡ በባሕርዩ ፡ ጠጅ ፡ ያደረገ ፡ ከሃሊ ፡ ፈጣሪ ፡ ነው ። ለሠርግ ፡ የተጠሩ ትንም ፡ ሰዎች ፡ አጠጣቸው ። በጠጡም ፡ ጊዜ ፡ ከጠጁ ፡ ጣዕም ፡ የተነሣ ፡ አደነቁ ።

፱ ፤ ሙሽራውንም ፡ ጠርተው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የማረውን ፡ ጠጅ ፡ ያጠጣል ። ከጠገቡ በኋላ ፡ ግን ፡ ተራውን ፡ ጠጅ ፡ ያጠጣል ። አንተ ግን ፡ ማለፊያውን ፡ ጠጅ ፡ እስካሁን ፡ አቆየኸው አሉት ። እንደዚህ ፡ የሕይወት ፡ ውሃ ፡ ያለውን ፡ ባለጸጋ ፡ ፈጣሪን ፡ እንደዚህ ፡ የስድስቱን ፡ ጋኖች ፡ ውሃ ፡ ጠጅ ፡ ያደረገ ፡ ከሃሊ ፡ የሆነን ፡ አምላክ ፡ በተጸማ ፡ ጊዜ ፡ ከርቤና ፡ የበለስ ፡ ደም ፡ የተቀላቀ ለበት ፡ መጣጣና ፡ የበግ ፡ ሐሞት ፡ አጠጡት ።

፲ ፤ ማቴዎስም ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ፡ ከነሱ ፡ አንዱ ፈጥኖ ፡ ሄዶ ፡ በዐይኑ ፡ በጎ ፡ መጣጣውን ፡ አምጥቶ በዘንግ ፡ አስሮ ፡ አጠጣው ፡ ብሏል ። ዮሐንስም ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ። በዚያም ፡ መጻጻ ፡ የተመላ ፡ ዕቃ ( ማሰሮ ) ተቀምጦ ፡ ነበር ። እነርሳቸውም ፡ መጻጻ ውን ፡ በሰፍነግ ፡ መልተው ፡ በስምዛ ፡ (ሰንሰል ፡) ዘንግ ፡ አሥረው ፡ ወደ ፡ አፉ ፡ አገናኙት ፡ ጠመቁበትም

፲፩ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ መጻጻውን ፡ ቀምሶ ፡ በመ ጽሐፍ ፡ የተጻፈው ፡ ሁሉ ፡ ደረሰ ፡ ተፈጸመ ፡ አለ ፤ በጉሮሮው ፡ መጠማትና ፡ ባንደበቱ ፡ መድረቅ ፡ ከሥ ጋዊና ፡ ከነፍሳዊ ፡ መጠማት ፡ አዳነን ። በቀትርም

ጊዜ ፡ የዝኆን ፡ ሐሞትና ፡ ከርቤ ፡ የተቀላቀለበት መጻጻን ፡ በመጠጣቱ ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓትም ፡ መጻጻ ንና ፡ የበግ ፡ ሐሞትን ፡ በመጠጣቱ ። የጣፈጠ ፡ የበ ለስ ፡ ፍሬን ፡ ስለ ፡ በሉ ፡ ስለ ፡ አዳምና ፡ ስለ ፡ ሔዋን ከፈለ ። ለኛም ፡ መራር ፡ የሆነ ፡ ሞትንና ፡ እርግማ ንን ፡ አጠፋልን ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ጌታችን ፡ ኢየ ሱስ ፡ ሳይሞት ፡ ራሱን ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ዘንበል ፡ አደ ረገ ፡ አሸናፊ ፡ ነውና ።

፯ ፤ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ራሱን ፡ አላዘንበለም ፡ ሞት ፡ እንደሚበረታባቸው ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ ሰዎች አይደለምና ። ከሞቱም ፡ በኋላ ፡ ራሳቸውን ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ እንደሚያዘነብሉ ፡ አይደለምና ። ጌታችን ፡ ግን ፡ ራሱን ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ በማዘንበሉ ፡ እኛን ፡ ከግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ አሳለፈን ። ጌታችንም ፡ ራሱን ፡ በማዋረዱ ፡ ራሳችንን ፡ ከመዋረድ ፡ ወደ ፡ ልዕልና ፡ አወጣን ። አክሊለ ፡ ሦክም ፡ በመቀዳጀቱ እኛን ፡ ጌታችን ፡ የደኅንነት ፡ ራስ ፡ ወርቅ ፡ የማያ ልፍ ፡ የክብር ፡ አክሊል ፡ አቀዳጀን ።

## ሦስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ንጉሥንና ፡ እግዚአ ብሔርን ፡ እንደ ፡ በደለ ፡ እንደ ፡ ነፍስ ፡ ገዳይም

በዕንጨት ፡ ሰቅለው ፡ ገደሉት ። በምሳሌ ፡ የነገራቸውን ፡ አላሰቡምና ።

፪ ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ የወይን ፡ ተክል ፡ ተከለ ፡ የሚጠብቅበትን ፡ ግንብ ፡ ሠራ ፡ ውድማም ፡ አበጀለት ፡ ወይኑንም ፡ የሚጠብቅለት ፡ ሾሞ ፡ ሾሞ ፡ ሄደ ። የሚያፈራበትም ፡ ሰዓት ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ከወይኑ ፡ ፍሬ ፡ አምጡ ፡ ብሎ ፡ ብላቴኖቹን ፡ ሰደደ ። ተክል ፡ ጠባቂዎችም ፡ ብላቴኖችን ፡ ይዘው ፡ ከነሱ ፡ የገረፉዋቸው ፡ የመቷቸውም ፡ የደበደቡዋቸውም ፡ የገደሏቸውም ፡ አሉ ። ከቀድሞዎችም ፡ የሚበዙ ፡ ብላቴኖችን ፡ ሰደደ ። እነሱንም ፡ ገደሏቸው ።

፫ ፤ የሚወደውም ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ነበረው ፡ ልጄንስ ፡ ያፍሩታል ፡ ብሎ ፡ ሰደደው ፡ ወይን ፡ ጠባቂዎቹም ፡ ልጁን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ እንዲህ ፡ ተባባሉ ። ወራሹ ፡ ይህ ፡ ነውና ፡ እንግደለው ፡ ርስቱንም ፡ እኛ ፡ እናድርግ ፡ ብለው ፡ ያዙት ፡ ከተክልም ፡ ቦታ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አውጥተው ፡ ገደሉት ። የተክሉ ፡ ባለቤት ፡ እነዚህን ፡ ምን ፡ ያደርጋቸዋል ። መጥቶ ፡ ይገድላቸው ፡ የለምን ፡ ወይኑንስ ፡ ፍሬውን ፡ በየጊዜው ፡ ለሚሰጡት ፡ ለሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ይሰጣቸው ፡ የለምን ፡ ብሎ ፡ የነገራቸውን ፡ አላስተዋሉምና ።

፬ ፤ ይህ ፡ ምሳሌ ፡ በአይሁድ ፡ ደረሰባቸው ፡ ነቢያትን ፡ እንደ ፡ ገደሉ ፡ የፍርድና ፡ የሕግ ፡ ባለቤት ልጁን ፡ የገደሉት ፡ አይሁድ ፡ አባቱ ፡ በሮማውያን

እጅ ፡ ገድለዋቸዋልና ። ከነሱም ፡ ክህነታቸውን ፡ ሕጋቸውን ፡ መንግሥታቸውንም ፡ አሳለፈባቸው ። የሃይማኖታቸውን ፡ ፍሬ ፡ ለሚሰጡ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ሰጠባቸው ። በሞት ፡ ጊዜ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ ሳያውቅ ፡ ድንገት ፡ ገደሉት ፡ እንዳይሉ ፡ አስቀድሞ ፡ በምሳሌ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ነገራቸው ።

፳ ፤ እነሆ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንወጣለን ፡ የሰው ፡ ልጅንም ፡ ይዘው ፡ ለክፉ ፡ ሰዎች ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጡታል ። ብዙ ፡ መከራ ፡ ያጸኑበታል ፡ ሰቅለውም ፡ ይገድሉታል ። በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ይነሣል ፡ አላቸው ። ዳግመኛም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ይመሰገን ፡ ዘንድ ፡ ጊዜው ፡ ደረሰ ፡ አላቸው ።

፳፩ ፤ የስንዴ ፡ ቅንጣት ፡ ከምድር ፡ ካልወደቀች ፡ ካልፈረሰች ፡ ብቻዋን ፡ ትኖራለች ። ከሞተች ፡ ከፈረሰች ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ፍሬ ፡ ታፈራለች ፡ ብዬ ፡ በውነት ፡ እነግራችኋለሁ ፡ ዳግመኛም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ የሚፈረድበት ፡ ጊዜ ፡ ደረሰ ። እንግዲህስ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ አበጋዝ ፡ (ዲያብሎስ ፡) ይፈረድበታል ። ከሰው ፡ ለይተው ፡ ይሰዱታል ። እኔም ፡ ከተሰቀልኩ ፡ በኋላ ፡ ሁሉንም ፡ ወደኔ ፡ እስባለሁ ። (ወገኔ ፡ አደርጋቸዋለሁ ።) ይህንንም ፡ ማለቱ ፡ በማናቸውም ፡ ሞት ፡ ይሞት ፡ ዘንድ ፡ ስላለው ፡ሲነግራቸው ፡ ነው ።

፳፪ ፤ ሕዝቡም ፡ ክርስቶስ ፡ ዘለዓለም ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖር ፡ በኦሪት ፡ ሰምተናል ። እንዴት ፡

አንተ ፡ ይሞታል ፡ ትለናለህ ። የሰው ፡ ልጅ ፡ ማነው ፡ አሉት ።

፴፭ ፤ ዳግመኛም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ከናንተ ፡ ጋራ ፡ እኖራለሁ ። ጨለማ ፡ (ሞት) ሳይ ደርስባችሁ ፡ ተመላለሱ ፡ እመኑ ፡ አላቸው ። በጨለማ ፡ የሚሄድ ፡ የሚሄድበትን ፡ አያውቅምና። ብርሃን ፡ ሳለ ፡ በሱ ፡ እመኑ ፡ የብርሃን ፡ ልጆች ፡ ትሆኑ ዘንድ ፤ ይህንንም ፡ ካላቸው ፡ በኋላ ፡ ተሠወራቸው ።

፴፱ ፤ ዳግመኛም ፡ ቸር ፡ ጠባቂ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ቸር ፡ ጠባቂ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ስለ ፡ በጎቹ ፡ ተላልፎ ፡ ይሞ ትላቸዋል ። ዳግመኛም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሊያገለ ግሉት ፡ አልመጣም ። እሱ ፡ ሊያገለግል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ክፉ ፡ ሰዎች ፡ ራሱን ፡ አሳልፎ ፡ ሊሰጥ ፡ ነው ፡ አላቸው ።

፲ ፤ ዳግመኛም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ትመራመራላችሁን ፡ አላቸው ። ዳግመኛ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ አታዩኝም ። ዳግመኛም ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ታዩኛላችሁ ፡ ስላልኳችሁ ፡ እኔም ፡ ወዳባቴ ፡ እሄዳለሁና ።

፲፩ ፤ እናንተም ፡ እንድታለቅሱ ፡ እንድታዝኑ ፡ በዕውነት ፡ እነግራችኋለሁ ። ዓለሙ ፡ ግን ፡ ደስ ይለዋል ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ ታዝናላችሁ ። ነገር ፡ ግን ኀዘናችሁ ፡ ደስታ ፡ ይሆንላችኋል ፡ ( ወደ ፡ ደስታ ይለወጥላችኋል ። ) ሴት ፡ ቀኗ ፡ ደርሶ ፡ በምትወል ድበት ፡ ጊዜ ፡ እንድታዝን ። ልጅ ፡ ከወለደች ፡ በኋላ

ግን ፡ ስለ ፡ ደስታዋ ፡ መከራዋን ፡ አታስበውም ወንድ ፡ ልጅ ፡ በዓለም ፡ ወልዳለችና ።

፲፪ ፤ እናንተም ፡ እንደዚሁ ፡ ታዝናላችሁ ፡ ነገር ግን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አያችኋለሁ ፡ ልባችሁም ፡ ደስ ይለዋል ። ደስታችሁንም ፡ ከናንተ ፡ የሚወስድባችሁ ፡ የለም ። ዳግመኛም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ፋሲካ ፡ እንዲሆን ፡ ዕወቁ ፡ የሰው ፡ ልጅንም ፡ ይይዙታል ፡ ሰቅለውም ይገድሉታል ፡ አላቸው ።

## አራተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ይህም ፡ የጌታችን ፡ ስቅለት ፡ በፈቃዱ ፡ ነው በፈቃዱስ ፡ ባይሆን ፡ ባልገደሉትም ፡ ነበር ። ይጥሉት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ራስ ፡ ባደረሱት ፡ ጊዜ ፡ ከመካከላቸው ፡ ተሠውሮ ፡ ሳያዩት ፡ ሄደልና ።

፪ ፤ ዳግመኛም ፡ አይሁድ ፡ ይመቱት ፡ ዘንድ ፡ ድንጋይ ፡ ባነሡ ፡ ጊዜ ፡ ከምኵራብ ፡ (ካዳራሽ ፡) ወጥቶ ፡ ከመካከላቸው ፡ ተሠውሮ ፡ ሄደልና ። ሊይዙትም ፡ በወደዱ ፡ ጊዜ ፡ ከእጃቸው ፡ አምልጦ ፡ ወደ ዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ሄደ ። ፈቃዱ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ገደሉት እንጂ ፡ ስለኛ ፡ ይሞት ፡ ዘንድ ፡ ፈቃዱ ፡ ነውና ።

፫ ፤ ጴጥሮስም ፡ እንዳይሞት ፡ በከለከለው ፡ ጊዜ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ጴጥሮስን ፡ ባላጋራዬ ፡ ከኋላዬ

ወግድ ፡ ብሎ ፡ ተቈጣው ፡፡ የሰውን ፡ እንጂ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ አታስብምና ፡ አለው ፡፡
፬ ፤ ጴጥሮስም ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ ቤት ፡ ሊሠራ በመከረ ፡ ጊዜ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ በዚያ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ በግብፅ ፡ ተአምራት ፡ ካደረገ ፡ ከሙሴ ፡ ጋራ ፡ በሹማምቱም ፡ ላይ ፡ እሳት ፡ ካወረደ ፡ ቀናዒ ፡ ከሚሆን ፡ ከኤልያስ ፡ ጋራ ፡ አይሁድ ፡ እንዳይገድሉት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ምክሩን ፡ አልተቀበለውም ፡፡
፭ ፤ ከደብረ ፡ ታቦር ፡ ወርዶ ፡ ስለእኛ ፡ ሞተ ፡ እንጂ ፡፡ ከመላእክት ፡ ጥቂት ፡ አነሰ ፡፡ የማይሞት ፡ ፈጣሪ ፡ ሲሆን ፡ ስለኛ ፡ መከራ ፡ ተቀብሎ ፡ ሙቷልና ፡፡ የሚያገለግሉት ፡ መላእክትን ፡ ከእሳት ፡ ከነፋስ ፡ የፈጠራቸው እሱ ፡ ሲሆን ፤ ሥጋም ፡ ከመላእክት ፡ ጥቂት ፡ አነሰ ፡ መባሉ ፡ ሞት ፡ ስለሚባል ፡ መከራው ፡ ነው ፡፡ አነሰ ፡ መባሉ ፡ በክብር ፡ በጌትነት ፡ አይደለም ፡ በተዋህዶ ከመለኮት ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ነውና ፡፡
፮ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በመከራውና ፡ በሞቱ ፡ ስለ ፡ አዳም ኃጢአት ፡ የበደሉትንም ፡ ያልበደሉትንም ፡ ከአዳም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሙሴ ፡ ድረስ ፡ የገዛቸው ፡ ሞትን ፡ አጠፋው ፡፡ ሁሉም ፡ በአዳም ፡ አምሳል ፡ ተፈጥሯልና ለጌታችን ፡ ግን ፡ ሞት ፡ አይገባውም ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ በዘር ፡ አልተወለደምና ፡ እሱም ፡ አልበደለምና ፡፡
፯ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ ሙት ፡ ተሰቀል ፡ ያለውን ፡ ትእዛዝ ፡ ተቀብሎ ፡ ለሞት ፡ ደረሰ ፡፡ የሞተውም ፡ በመስቀል ፡ ተሰቅሎ ፡ ነው ፡ ስለ ፡

ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ሞትን ፡ ተቀበሏልና ። ለእሱ ፡ ግን ፡ የበደሉን ፡ ሰዎች ፡ ሞትን ፡ ተቀበለ ፡ ያድናቸው ፡ ዘንድ ፡ በሐዲስ ፡ ሕግ ፡ የተመረጠ ፡ መምህር ፡ ሆነ ፡ መድኃኒታችን ፡ ፈጣሪያችን ፡ እሱ ፡ ግን ፡ ስለኛ ፡ ሞተ ። ሰውነቱን ፡ ለሞት ፡ ስለኛ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ ።

፰ ፡ በጳንጦስ ፡ ሰው ፡ በጲላጦስ ፡ ዘመን ፡ ምስክር ሆነ ፡ ከኀጢአታችን ፡ ያድነን ፡ ዘንድ ፡ ለርሱም ፡ ሐዲስ ፡ (የበቁ ፡) ወገኖች ፡ ያደርገን ፡ ዘንድ ። እሱ ግን ፡ በደሙ ፡ ወገኖቹን ፡ ያከበራቸው ፡ ዘንድ ፡ ከከተማው ፡ በአፍአ ፡ ሞተ ። እሱም ፡ የሰውን ፡ ኃጢአት ፡ ለማስተሥረይ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ። እኛን ከአባቱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ያስታርቀን ፡ ዘንድ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ እሱ ፡ ስለኛ ፡ ሞተ ፡ በመለኮትነቱ ሕያው ፡ ሲሆን ፡ በሥጋ ፡ ሞተ ።

## አምስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፡ አይሁድ ፡ ግን ፡ ቀኑ ፡ ዐርብ ፡ ነበርና ፡ ሰንበት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እሊህ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ተሰቀሉ እንዳይድሩ ፡ አሉ ። ሰንበትን ፡ ያከብራሉና ።

፪ ፡ ጭፍሮችም ፡ ተሠውረው ፡ መጥተው ፡ ጲላጦስን ፡ እሊህን ፡ ሰዎች ፡ ጭን ፡ ጭናቸውን ፡ ሰብረን ፡ እናውርዳቸው ፡ ብለው ፡ ለመኑት ። ከጌታ ፡ ጋራ ፡ የተሰቀሉ ፡ ሁለቱንም ፡ ሰዎች ፡ ጭን ፡ ጭናቸውን ፡ ሰብረው ፡ አወረዷቸው ።

፫ ፤ ጭፍሮችም ፡ ወደ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ በደረሱ ጊዜ ፡ ፈጽሞ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ አይተው ፡ ጭኑን ፡ አልሰበሩትም ፡፡ ከጭፍሮች ፡ አንዱ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ባሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ጭኑን ፡ ስላልሰበሩት ፡ ተቆጥቶ ፡ መሞቱንና ፡ አለመሞቱን ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ በሠሩሊት ፡ በታላቅ ፡ ጦር ፡ ጎኑን ወጋው ፡ እንጂ ፡፡

፬ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስንም ፡ ጎኑን ፡ በወጋው ፡ ጊዜ ጥሩ ፡ ውሃ ፡ ትኩስ ፡ ደም ፡ ፈሰሰ ፡፡ ደሙም ፡ ከውሃው ፡ ጋራ ፡ አዳምን ፡ ለማዳን ፡ መቃብሩን ፡ ዘልቆ ፡ በአዳም ፡ ዓፅም ፡ ላይ ፡ ፈሰሰ ፡፡ እንደ ፡ ሩቅ ፡ ብእሲ ደሙ ፡ ደርቆ ፡ የሞተ ፡ አይደለምና ፡፡ መላእክትም ደሙን ፡ በእሳት ፡ ጽዋዕ ፡ ተቀበሉት ፡፡ ያየውም ፡ ሐራዊ ፡ ምስክር ፡ ሆነ ፡ ምስክርነቱም ፡ ዕውነት ፡ ነው ፡፡ እሱም ፡ እናንት ፡ ታምኑ ፡ ዘንድ ፡ ዕውነትን እንዲያስተምር ፡ ዐወቀ ፡፡ ይኸውም ፡ የተደረገ ፡ መጽሐፍ ፡ አጥንቱን ፡ አትስበሩ ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ይደርስ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡፡

፭ ፤ ዳግመኛም ፡ ሁለተኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ጎኑን ፡ የወጉት ፡ ሰዎች ፡ በተአምራት ፡ ያዩት ፡ ዘንድ ፡ አላቸው ፡ ብሏል ፡፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ነጠብጣብ ሁሉ ፡ የፈሰሰው ፡ በጥፈና ፡ በበትር ፡ በመመታቱ ነው ፡፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ በመጐተቱና ፡ በመረገጡ ፡ ነው ፡፡

በመገረፉና ፡ በመደብደቡም ፡ ነው ። የሾኽ ። አክሊልም ፡ በመቀዳጀቱ ፡ ነው ፡ በጦርና ፡ በችንካር ፡ በመወጋቱ ፡ ነው ። እልፍ ፡ ዘጠኝ ፡ ሺሕ ፡ ካንድ ፡ መቶ ፡ ሃያ ፡ አምስት ፡ በሚሆን ፡ በተቀበለው ፡ መከራ ፡ ሁሉ ፡ ነው ።

፮ ፤ በዚህም ፡ በመወጋቱ ፡ በፈሰሰው ፡ ደም ፡ የእሳት በትርና ፡ የእሳት ፡ ጦርና ፡ የእሳት ፡ ሰይፍም ፡ በያዙ በሱራፌልና ፡ በኪሩቤል ፡ እጅ ፡ አምስት ፡ ሺሕ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ የተዘጉ ፡ ሦስቱን ፡ የገነት በሮች ፡ ከፈተልን ። እነሱን ፡ ከሦስት ፡ በሮች ፡ አስወግዶ ። በቀኙ ፡ የተሰቀለውን ፡ ወንበዴ ፡ በሠርክ ፡ ጊዜ በደሙ ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ አገባው ። ይኸውም ፡ ደም ፤ አዳምን ፡ ከነልጆቹ ፡ እጁን ፡ ይዞ ፡ ከሲኦል ፡ አወጣው ።

፯ ፤ ከሲኦልም ፡ ባወጣቸው ፡ ጊዜ ፡ በነቢዩ ፡ በሙሴ ምስጋና ፡ አመሰገኑት ። በደሙም ፡ ወደ ፡ ተከፈተ ገነት ፡ ገቡ ። በመጀመሪያይቱ ፡ ሰንበትና ፡ እሑድ በተባለች ፡ በታላቂቱ ፡ ሰንበት ፡ ሕዝቡን ፡ በደስታ ከሲኦል ፡ አወጣቸው ። በገነትም ፡ አኖራቸው ።

## ስድስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ጌቶቼ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ! አደራ ፡ እላችኋለሁ ። እመቤቴ ፡ ማርያም ፡ አንችንም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ግቢልኝ ፡ እልሻለሁ ፡ (እማልድሻለሁ ።) በነፍሱና ፡ በሥጋው ፡ በተቀበላቸው ፡ መከራዎች ፡ ሁሉ ። በመቸንከሩም ።

፱ ፤ የእሾኽ ፡ አክሊል ፡ ተቀዳጅቶ ፡ በመስቀሉ ። በሞቱም ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ በመውረዱ ። በጦር ፡ በመጋቱ ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በመቀበሩ ። ኀጢአቱን ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ ትሉ ፡ ዘንድ ። ከኃጢአትም ፍዳ ፡ ሁሉ ፡ ታድኑኝ ፡ ዘንድ ፡ ለዘለዓለሙ ፡ አሜን ።

## የቀዳሚት ፡ ተአምር ።

፩ ፤ በአካለ ፡ ነፍስ ፡ ያደረገው ፡ ተአምር ፡ ይህ ፡ ነው ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በአካለ ፡ ነፍስ ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ወርዶ ። ገሃነምን ፡ የሚጠብቁ ፡ (በረኞች) ፡ አጋንንት ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ሸሹ ። ሰባት ፡ መቶ ፡ የሚሆኑ ፡ የብረት ፡ መዝጊያዎችና ፡ በሮችን ፡ ሰበራቸው ።

፪ ፤ መልአከ ፡ ሞትን ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ አውርዶ ከዚያ ፡ አሠረው ። ወደ ፡ ሲኦልም ፡ በመውረዱ ፡ ነፍሳችንን ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ከመውረድ ፡ አዳነን ። ለነቢያትም ፡ ለደጋጎቹም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በአካለ ፡ ነፍስ ፡ ወርዶ ፡ የደኅንነትን ፡ ምሥራች ፡ ነገራቸው ።

፫ ፤ አስቀድሞ ፡ ለካዱ ፡ ሰዎች ፡ በአካለ ፡ ነፍስ ወርዶ ። በንስሐ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትዕግሥት ፡ ደጅ ፡ እየጠኑ ፡ ለሚኖሩ ፡ ነጻነትን ፡ አበሠራቸው ፡ በመከራውና ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ የተደረገ ፡ ተአምር ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ቀኝ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ አጠመቃቸው ፡

በሞት ፡ ጥላ ፡ በጨለማ ፡ ታስረው ፡ የነበሩትን ፡ ፈታ
ቸው ፡ የታሰሩበትን ፡ እግር ፡ ብረት ፡ ሰባበረ ፡፡

፬ ፤ በቀራንዮ ፡ ያደረገው ፡ ተአምራት ፡ ይህ ፡ ነው
አይሁድን ፡ ለማጥፋት ፡ ሰይፋቸውን ፡ በመዘዙ ፡ ጊዜ
ሰባቱን ፡ የመላእክት ፡ አለቆች ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡
በመታገሥ ፡ ከለከላቸው ፡፡ በመጋረጃውም ፡ መቀደድ
በቸርነቱ ፡ ቍጣቸውን ፡ እንዲመልሱ ፡ አደረጋቸው ፡፡

፭ ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የቤተ ፡ መቅደሱ ፡ መጋ
ረጃ ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ ድረስ ፡ ከሁለት ፡ ተከ
ፈለ ፡፡ ጠላቱ ፡ በጠፋለት ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ እንደሚለው
ሰው ፡ ምድርም ፡ ደስ ፡ ብሏት ፡ ተንቀጠቀጠች ፡፡ በሞ
ቱም ፡ ሰማይ ፡ ታወከች ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ፀሐይና ፡
ጨረቃ ፡ ከዋክብትም ፡ ብርሃናቸውን ፡ ሰጡ ፡፡ ጨለ
ማም ፡ ተወገደ ፡፡ ድንጊያዎችም ፡ ተፈተቱ ፡፡ መቃ
ብሮችም ፡ ተከፈቱ ፡፡ ከሞቱት ፡ ከደጋጎቹም ፡ ወገን
አምስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ተነሡ ፡፡

፮ ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ኢየሩ
ሳሌም ፡ ገቡ ፡፡ ብዙዎችም ፡ ሰዎች ፡ ተገልጸው ፡
አዩዋቸው ፡፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ያስነሣቸው ፡
በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡፡ በሕይወቱም ፡
አብርሃምና ፡ ይስሐቅን ፡ ያዕቆብንና ፡ ዐሥራ ፡ ሁለ
ቱን ፡ ልጆች ፡ ነቢይ ፡ ሙሴንም ፡ ከመቃብር ፡
አስነሣቸው ፡ እንጂ ፡፡

፯ ፤ በሱ ፡ ስም ፡ እንዲያስተምሩ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ አስ
ናበታቸው ፡፡ የከበሩ ፡ ሴቶች ፡ ሣራንና ፡ ርብቃን

ራሔልንም ፡ አስነሣቻቸው ። የሕይወት ፡ ትንሣኤ ፡ ነውና ። ትንሣኤም ፡ ሕይወትም ፡ ነውና ።

፰ ፤ የመቶው ፡ አለቃና ፡ አብረውት ፡ ያሉ ፡ ጭፍሮቹም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ። እንዲህ ፡ ተጨንቆ ፡ እንደሞተና ፡ የዓለሙንም ፡ መናዋወጥ ፡ ባዩ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ፈሩ ። እግዚአብሔርንም ፡ አመሰገኑ ።

፱ ፤ ሁሉም ፡ አንድ ፡ ሁነው ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ ይህ ሰው ፡ በዕውነት ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ በዕውነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ ፡ ኑሯል አሉ ። የተሰበሰቡት ፡ ሁሉ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ። ያደረገውንም ፡ ይህን ፡ ድንቅ ፡ ተአምራት ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ደረታቸውን ፡ ደቁ ።

፲ ፤ እያደነቁም ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ወደ ፡ ሀገራቸው ፡ ተመልሰው ፡ ገቡ ። ቀድሞም ፡ የሚያውቁት ሰዎች ፡ ርቀው ፡ ቁመው ፡ ያዩት ፡ ነበር ። ከገሊላም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ የተከተሉት ፡ በገንዘባቸውም ፡ የሚያገለግሉት ፡ ብዙዎች ፡ ሴቶች ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ቁመው ፡ አዩት ። የሆነውንም ነገር ፡ ተመለከቱ ።

## የቀዳሚት ፡ ዓርኬ ።

፩ ፤ ሰውን ፡ ከሚገዛ ፡ ከሞት ፡ ዕዳ ፡ አሳቻውን ፡ ታድን ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ አዳምና ፡ ስለ ፡ ልጆቹ ፡ ኤሎሄ ፡ ኤሎሄ ፡ ኤልማስ ፡ ሰበቅታኒ ፡ ብለህ ፡ የጸለ

ይህ ፡ መምህር ፡ ሆይ ፤ አቤቱ ፡ ላንተ ፡ እገዛለሁ
ለመስቀልህም ፡ እገዛለሁና ፡ እንዳይን ፡ ብሌን ፡
ጠብቀኝ ። በክንፈ ፡ ረድኤትህም ፡ ሠውረኝ ።

፱ ፤ ፈጣሪዬ ፡ ፈጣሪዬ ፡ በምሕረት ፡ ተመልከ
ተኝ ፡ ብለህ ፡ ወደ ፡ ግሩም ፡ አባትህ ፡ ጮኸክ ፡
በፍጹም ፡ አስታራቂ ፡ ቃል ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤
ሰውነቴን ፡ ስለ ፡ አዳም ፡ ከፍያለሁና ፡ እንዳልህ ።
ጥፋት ፡ ይገሠፅ ። መርገምም ፡ ይጥፋ ።

፲ ፤ እንደ ፡ በሽተኞች ፡ የተጠማህ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤
በሚቾች ፡ ሰዎች ፡ ልማድም ፡ ውሃን ፡ የለመንህ ፡ ክር
ስቶስ ፡ መከራዎችን ፡ የታገሥህ ፡ የማትናገር ፡ በግ ፡ ክር
ስቶስ ፡ ሆይ በሱቱኤል ፡ ጽዋዕ ፡ የሆድህን ፡ ውሃ ፡ አጠጣኝ
የመቅሠፍትህን ፡ ወይን ፡ ግን ፡ በጾና ፡ ጽዋዕ ፡ አታጠጣኝ

፩ ፤ አንደበትህ ፡ በደረቀ ፡ ጕሮሮህም ፡ በተጠማ ፡
ጊዜ ፡ ዐዞከልና ፡ ሐሞትን ፡ ያጠጡህ ፡ ከሐሰት ፡
መምህራን ፡ እጅ ፡ ግፍ ፡ የተቀበልህ ፡ ክርስቶስ ፡
ሆይ ፤ ኃጥእ ፡ እኔን ፡ ከኵነኔ ፡ ካላዳንህ ፡ ከሀገር
በአፍአ ፡ ለምን ፡ ተሰቀልህ ።

፪ ፤ ረቂቅ ፡ ወዝን ፡ ባወዛኸው ፡ ጊዜ ፡ መልአከ ፡
ሞት ፡ ዲያብሎስ ፡ ቀድሞ ፡ የነሣሁህን ፡ ዕረፍትስ ፡
ተወውና ፡ ክርስቶስ ፡ በጲላጦስ ፡ ፊት ፡ ጥቂት ፡ ለመ
ቆምህ ። ሰማይና ፡ ምድር ፡ ለኔ ፡ ቢሆኑ ፡ የምከፍልህን
እሰጥህ ፡ ዘንድ ፡ አይበቃኝም ፡ አለ ።

፫ ፤ በላይ ፡ ወዳለ ፡ አባትህ ፡ ነፍስህን ፡ አደራ ፡
በማለት ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ከተሰቀሉ ፡ ሽፍቶች ፡ ጋራ

የተቆጠርህ ፡ ሆይ ፤ መልአከ ፡ ሞት ፡ በኃይሉ ፡ ነፍስ ፡ መለየትን ፡ ተወ ። ነገር ፡ ግን ፡ በፍጹም ፡ ልብህና ፡ በፍ ጹም ፡ አሳብህ ፡ ውደደኝ ፡ ውደደኝ ፡ ከኔም ፡ ጋራ ፡ ኑር ።

፯ ፤ ያለመድኸው ፡ ልማድ ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ በደረሰብህ ፡ ጊዜ ፡ ከእሳትና ፡ ከትል ፡ መከራ ፡ የሰዎችን ፡ ነፍሳት ፡ ታድን ፡ ዘንድ ፡ እራስንና ፡ አንገትን ፡ ዝቅ ፡ በማድረግ ፡ ሰውነትህን ፡ የሰጠህ ። የእሳት ፡ ሞገድ ፡ እንደሮቤል ፡ እንዳያስጥመኝ ። ሆይ ፡ መስቀልህ ፡ የሕይወት ፡ መርከብ ፡ ይሁንኝ ።

፰ ፤ በመቸንከርና ፡ ዳግመኛ ፡ በመሰቀል ፡ ሥጋህ ከታመመ ፡ በኋላ ፡ የሞትህ ። የሞትህ ፡ ሥልጣን ፡ የሞትን ፡ ሥልጣን ፡ ያደከመ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤ ዛሬ ፡ ሦስተኛ ፡ ማኅተምን ፡ አትፍታብኝ ፡ ጥቍር ፈረስንም ፡ አታሳየኝ ።

፱ ፤ ከሲኦል ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ የምትወርደው ፡ ገነት ነፍሳትን ፡ ለማውጣት ፡ ባድንነት ፡ ከነፍስህ ፡ ጋራ ፡ የወረድህ ። በመገለጥ ፡ ያለ ፤ የመውረድህን ፡ ምሥ ጢር ፡ ሳመሰግን ። ወደ ፡ ሲኦል ፡ ወርዶ ፡ ኃይሉን ፡ አጥፍቶ ፡ የሰይጣንን ፡ ምርኮ ፡ ቀማው ።

፲ ፤ በተቀዳጀኸው ፡ አክሊለ ፡ ሦክ ፡ እራስህ ፡ የተበሳ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤ በተሰቀለ ፡ ሰውነትህ ፡ የተ ጫወቱ ፡ ወገኖች ፡ በተሣለ ፡ ጦር ፡ የወጉህ ። በልቤ ባሰብሁት ፡ በቃሌም ። በተናገርኩት ፡ ብበድል ፡ የይ ቅርታ ፡ አባት ፡ ፈጣሪዬ ፡ ሆይ ፤ አንጻኝ ።

፲፩ ፤ መድረቅ ፡ እንደሚያገኘው ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ደም ፡ አይደለምና ፡ ገንትን ፡ በደምህ ፡ የከፈትኸው ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤ በነፋስ ፡ አውታር ፡ ሞትን ፡ ካሠርኸው ፡ በኋላ ፡ ንጉሥ ፡ ዳዊት ፡ ከመረጠው ፡ ከዚህ መቅሠፍት ፡ በጦር ፡ በመወጋትህ ፡ አድነኝ ።

፲፪ ፤ የእግርህንና ፡ የእጆችህን ፡ ችንካሮች ፡ የደረትህንም ፡ ችንካር ፤ የፊትህን ፡ መጸፋትና ፡ የራስህንም ፡ መመታት ። ዳግመኛ ፡ የዥርባህን ፡ ግርፋትና ፡ የጎንህን ፡ መወጋት ፡ አስበህ ፡ አቤቱ ፡ እኔን ፡ ይቅር ፡ በለኝ ። ይቅር ፡ ባይ ፡ ቸር ፡ አንተ ፡ ነህና ። ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤ እኔን ፡ ባሪያህን ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ጠብቀኝ ፤ ለዘለዓለሙ ፡ አሜን

## የእሑድ ፡ ድርሳን ፡ ማሕየዊ ።
## አንደኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ በማመን ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ የሚነበብ ፡ የሚጸለይ ሰውን ሁሉ ፡ የሚወድ ፡ ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ የሚያድን ፡ የጌታችን ፡ የሞቱና ፡ የመከራውን ፡ ነገር ፡ የሚናገር ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ።

፪ ፤ በሠርክም ፡ ጊዜ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ በሞቱና በሕይወቱ ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ ተሰቅሎ ፡ አምስቱን ፡ ሰዓት ፡ ፈጸመ ። በሕይወቱ ፡ ከቀትር ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ሰዓት ፡ ቆየ ። በሞቱ ፡ ከዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ እስከ ፡ ዐሥራ

አንድ ፡ ሰዓት ፡ ተሰቅሏልና ። ከዘመዶቹም ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ካመኑበትም ፡ ሕዝብ ፡ ወገን ፡ አንድ ስንኳ ፡ ከመስቀል ፡ የሚያወርደው ፡ አላገኘም ።

፫ ፤ አይሁድም ፡ ከመስቀል ፡ የሚያወርደው ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሌለው ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ። በእሳት ፡ ያቃጥሉት ፡ ዘንድ ፡ ሥጋውን ፡ ስጠን ፡ ብለው ፡ ለመኑት ። የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ጠላቶቹ ፡ በዝተዋልና ። ስለ ፡ ክፉ ፡ ሥራቸው ፡ ስለ ፡ ነቀፍኋቸውና ምስክር ፡ ስለ ፡ ሆንኩባቸው ፡ እኔን ፡ ዓለም ፡ (ሰው) ይጠላኛል ፡ ብሎ ፡ እሱ ፡ በሕይወቱ ፡ እንደ ፡ ተናገረ።

፬ ፤ዳግመኛም ፡ እኔን ፡ የጠላ ፡ አባቴን ፡ መጥላቱ፡ ነው ፡ ብሏልና ። ሌላ ፡ ሰው ፡ ያልሠራውን ፡ ሥራ ያልሠራሁላቸውስ ፡ ቢሆን ፡ በዳኑ ፡ ነበር ፡ ዕዳም ፡ ባልሆናቸውም ፡ ነበር ።

፭ ፤ ዛሬ ፡ ግን ፡ አዩኝ ፡ እኔንም ፡ አባቴንም ፡ ጠሉ ፡ በከንቱ ፡ ጠሉኝ ፡ ብሎ ፡ በኦሪታቸው ፡ የተጻፈው ፡ ይደርስ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ።

፮ ፤ ጲላጦስም ፡ አይሁድን ፡ እኔስ ፡ በሕይወቱም በስቅለቱም ፡ በሞቱም ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ተአምራት ፡ ያሳየ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅን ፡ ሥጋውን በእሳት ፡ አላቃጥልም ፡ አላቸው ።

## ሁለተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፡ በዕለተ ፡ ዐርብ ፡ ምሽትም ፡ በተቃረበ ፡ ጊዜ ፡ ዮሴፍና ፡ ኒቆዲሞስ ፡ መጡ ። ወደ ፡ ጲላጦስም ፡ ገብተው ፡ ረዳት ፡ የሌለው ፡ መጻተኛ ፡ እንግዳ ፡ የሚሆን የኢየሱስን ፡ ሥጋ ፡ ስጠን ፡ ብለው ፡ ለመኑት ፡ በውርጭና ፡ በቍር ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ የተሰቀለ ፡ የኢየሱስን ፡ ሥጋ ፡ ስጠን ። የመጣበትና ፡ የሚሄድበት የማይታወቅ ፡ ብቸኛ ፡ የሚሆን ፡ የኢየሱስን ፡ ሥጋ ፡ ስጠን ። ከመስቀልም ፡ ላይ ፡ አውርደን ፡ ገንዘን ፡ እንቅበረው ፡ ብለው ፡ ለመኑት ።

፪ ፡ ጲላጦስም ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እንዴት ፡ ሞተ ፡ ብሎ ፡ አደነቀ ። እንደ ፡ ሞተም ፡ ዐውቆ ፡ ብላቴናውን ፡ ጭፍራውን ፡ ጠርቶ ፡ የኢየሱስን ፡ ሥጋ ፡ ስጣቸው ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

፫ ፡ እሊህም ፡ ጌታችን ፡ ወደተሰቀለበት ፡ ቦታ ፡ ሄደው ፡ ሰገዱለት ። የተቸነከረባቸውንም ፡ የብረት ፡ ችንካር ፡ ከእጆቹና ፡ ከእግሮቹ ፡ ከደረቱም ፡ ነቅለው ፡ አወጡት ። ከመስቀሉም ፡ ጋራ ፡ የታሠረበት የወገቡን ፡ ገመድ ፡ ፈቱ ።

፬ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ከመስቀል ፡ ላይ ፡ አወረዱት ። ከመስቀልም ፡ ባወረዱት ጊዜ ። በደሙና ፡ ባጥንቶቹ ፡ በቍስሉ ፡ ፈጽሞ ፡ ሳይነዋወጥ ፡ ተኛ ።

፳ ፤ ስለኛ ፡ በሞት ፡ ዐይኖቹ ፡ እንደ ፡ ተሸፈኑ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ። ስለኛ ፡ ጆሮቹም ፡ በሞት ፡ እንደ ፡ ተዘጉ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ። ስለኛም ፡ በሞት ፡ እንደበቱ ፡ ዝም ፡ እንዳለ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ። ስለኛም ፡ እጆቹና ፡ እግሮቹን ፡ እንደ ፡ ታሠሩ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ። ሞትን ፡ ድል ፡ የምትነሣ ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፤ ተኛህን ፡ ሞትስ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ሠለጠነ ፡ እያሉ ፡ አለቀሱ ።

፳፩ ፤ ከሞተም ፡ በኋላ ፡ በሦስተኛው ፡ ሰዓት ፡ ሕያው ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ዐይኖቹ ፡ ያን ጊዜ ፡ ግልጽልጽ ፡ አሉ ። ዐይኖቹም በተገለጡ ፡ ጊዜ ፡ ዮሴፍና ፡ ኒቆዲሞስ ፡ ደነገጡ ። ከክቡር ፡ ሥጋው ፡ በድን ፡ በሰሙት ፡ በሦስቱ ፡ ምስጋናዎች ፡ አመሰገኑት ።

፳፪ ፤ እሱም ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ነገራቸው ። ዳግመኛም ፡ እስከ ፡ ትንሣኤ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በሞት ፡ ዐይኖቹ ፡ ተሸፈኑ ።

## ሦስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ዮሴፍና ፡ ኒቆዲሞስ ፡ ሰው ፡ ባልለበሰው ፡ አዲስ ፡ ግምጃ ፡ ሻሽ ፡ ገነዙት ። በሚገንዙት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ አይሁድ ፡ ሥርዐት ፡ ከሽቱና ፡ ከከርቤ ፡ ጋራ ፡ በሰበን ፡ ጠቀለሉት ።

፪ ፤ ይህም ፡ ኒቆዲሞስ ፡ አስቀድሞ ፡ ሌሊት ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ ሄዶ ፡ መምህር ፡ ሆይ ፤ ታስተምር ፡

ዘንድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተልከህ ፡ እንደ ፡ መጣህ እናምናለን ፡ ያለው ፡ ነው ፡፡ እግዚአብሔር ፡ በሀል ሎናህ ፡ ሳለህ ፡ ካንተ ፡ በቀር ፡ አንተ ፡ የምትሠ ራውን ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ የሚሠራ ፡ የለም ፡፡

፲፬ ፤ ጌታችንም ፡ የሞቱና ፡ የስቅለቱን ፡ ነገር ፡ ገለጠ ለት ፡፡ ሙሴ ፡ የምድር ፡ አርዌን ፡ በበረሃ ፡ እንደ ፡ ሰቀ ለው ፡፡ የሰው ፡ ልጅም ፡ እንዲሁ ፡ ይሰቀል ፡ ዘንድ ፡ አለው ፡ ብሎ ፡ ገለጠለት ፡፡ በሱ ፡ ያመነ ፡ ሁሉ ፡ እን ዳይጐዳ ፡ ለዘላለሙ ፡ ይድናል ፡ እንጂ ፡፡ እግዚአብሔር አንድ ፡ ልጁን ፡ ለሰው ፡ ቤዛ ፡ አድርጎ ፡ አሳልፎ ፡ እስከ መስጠት ፡ ደረሰ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ወዶታልና ፡፡

፲፮ ፤ በሱ ፡ ያመነ ፡ ሁሉ ፡ የዘላለም ፡ ሕይወት ፡ ያገኛል ፡ እንጂ ፡ እንዳይጐዳ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዓ ለም ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ ልጁን ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ አላከውምና ፡፡ ዓለሙን ፡ ያድነው ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሱም ፡ ያመነ ፡ እንዳይፈረድበት ፡፡

፳፩ ፤ ባዲስ ፡ ግምጃ ፡ ሻሽ ፡ እንደ ፡ ገነዙት ፡ ሰው ፡ ባልተቀበረበት ፡ ባዲስ ፡ መቃብር ፡ ጌታችን ኢየሱስን ፡ ቀበሩት ፡፡ ዮሐንስም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱ ስን ፡ ከሰቀሉበት ፡ አቅራቢያ ፡ የተክል ፡ ቦታ ፡ አለ በዚህም ፡ በተክል ፡ ቦታ ፡ ሰው ፡ ያልተቀበረበት ፡ አዲስ ፡ መቃብር ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ጽፏል ፡፡

፳፪ ፤ በዚያም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ቀበሩት ፡ የአይሁድ ፡ ዐርብ ፡ ጊዜው ፡ መሽቶ ፡ ነበርና ፡፡ መቃብ ሩም ፡ በተሰቀለበት ፡ ቦታ ፡ ቅርብ ፡ ነበረ ፡፡ መቃብሩንም

በታላቅ ፡ ደንጊያ ፡ ገጥመውት ፡ ሄዱ ። ያም ፡ ቀን ፡ ለቀዳሚት ፡ አጥቢያ ፡ ዐርብ ፡ ማታ ፡ ነበር ።

፺ ፤ ከገሊላ ፡ የተከተሉት ፡ ሴቶችም ፡ ሥጋው ፡ እንደምን ፡ እንደ ፡ ተቀበረ ፡ መቃብሩን ፡ አዩ ። ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ መጠን ፡ ያለው ፡ መቃብር ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ እንደ ፡ ወሰነውና ፡ እሱ ፡ በሰማይ በምድር ፡ የመላ ፡ ሲሆን ፡ እንደ ፡ ሙታን ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ተወሰነ ፡ ተመለከቱ ።

፺፩ ፤ ዮናስ ፡ በአንበሪ ፡ (በጕማሬ ፡) ሆድ ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ እንዳደረ ፡ የሰው ፡ ልጅም በመቃብር ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ ያድራል ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ቃሉ ፡ ዕውነተኛ ፡ ነውና ። ድንቅ በሚሆን ፡ በመቀበሩም ፡ ሙስና ፡ መቃብርን ፡ አጠፋልን ።

፺፪ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የካህናት ፡ አለቆችና ፡ ፈሪሳውያን ፡ ተሰብስበው ፡ ወደ ፡ ጲላጦስ ፡ ሂደው ፡ መማለጃ ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ ሰጡትና ፡ ይህ ፡ የሚያስት ፡ ሰው ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ እነሣለሁ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ አሰብን ። አሁንም ፡ መቃብሩን ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ጠብቁ ፡ ብለህ ፡ እዘዝ ፡ አሉት ። ደቀ መዛሙርቱም ፡ ሌሊት ፡ መጥተው ፡ በድኑን ፡ ሰርቀው ፡ እንዳይወስዱ ፡ ለሕዝቡም ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ ተነሣ ፡ እንዳይሉ ። ከቀደመች ፡ በደሉ ፡ የኋለኛዪቱ ፡ በደሉ ፡ የከፋች ፡ ትሆናለችና ፡ አሉት ።

፷፭ ፤ ጲላጦስም ፡ መማለጃ ፡ ስለ ፡ ተቀበለ ፡ የወታደር ፡ ጭፍሮች ፡ ተቀብላችሁ ፡ እናንተ ፡ እንዳወቃችሁ ፡ ሂዱ ፡ መቃብሩን ፡ አስጠብቁ ፡ አላቸው ።

፷፮ ፤ የካህናት ፡ አለቆችና ፡ ፈሪሳውያንም ፡ ወታደሮችን ፡ ይዘው ፡ ዘጠና ፡ ዘጠኝ ፡ በሚሆን ፡ መቆለፊያቸው ፡ መቃብሩን ፡ ቆለፉ ። ዐራቱም ፡ ሹማምቶች ፡ ካራት ፡ መቶ ፡ ጭፍራ ፡ ጋራ ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስን ፡ መቃብር ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ድረስ እየጠበቁ ፡ ተቀመጡ ።

## ዐራተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ሞትን ፡ ያጠፋ ፡ ሞትን ፡ ድል ፡ የነሣ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ አይሁድን ፡ ይህን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አፍርሱት ፡ እኔ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ አነሣዋለሁ ፡ እንዳላቸው ። በእውነት ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ ተነሣ ።

፪ ፤ አንበሳ ፡ ከተኛበት ፡ ፈጥኖ ፡ እንዲነሣ ። ወይን ፡ ጠጥቶ ፡ የሰከረ ፡ ኀይለኛ ፡ ፈጥኖ ፡ እንዲነሣ ። በመንፈስ ፡ ቅዱስና ፡ ባባቱ ፡ ኀይል ፡ በራሱም ፡ ሥልጣን ፡ ፈጥኖ ፡ ተነሣ ፡ የሞት ፡ ቍራኝነትንም ፡ አጠፋ ። ሞት ፡ ሊይዘው ፡ አይችልምና ።

፫ ፤ የተገነዘበትንም ፡ ልብስ ፡ ትቶ ፡ ልብሰ ፡ መንግሥቱን ፡ ለብሶ ፡ ተነሣ ። በተወለደም ፡ ጊዜ ፡ የናቱን ፡ ማኅተመ ፡ ድንግልና ፡ እንዳለወጠ ።

በትንሣኤውም ፡ የመቃብሩን ፡ ቍልፍ ፡ አልከፈ
ተም ። በተገነዘበትም ፡ ልብስ ፡ የመቶ ፡ አለቃውን
ዐይን ፡ አዳነ ። የሞተውንም ፡ ሰው ፡ አስነሣ ።
በመቃብሩም ፡ ጲላጦስ ፡ በውስጡ ፡ በቀበረው ፡ ጊዜ ፡
ፈያታዊ ፡ ዘየማንን ፡ አስነሣው ።

፲፱ ፡ እሑድ ፡ ማታም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ደቀ
መዛሙርቱ ፡ አይሁድን ፡ ስለፈሩ ፡ ተሰብስበው ፡
ወዳሉበት ፡ ከዝግ ፡ ቤት ፡ ገባ ። ያረጋጋቸውና ፡
ደስም ፡ ያሰኛቸው ፡ ዘንድ ።

፳ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡
አትፍሩ ፡ አትደንግጡ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አላቸው ።
እነሱ ፡ ግን ፡ ምትሐት ፡ የታያቸው ፡ መስሏቸው ፡
ፈጽመው ፡ ፈሩ ።

፳፩ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡
ምን ፡ ያስደነግጣችኋል ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሐሳብ ፡
በልቡናችሁ ፡ ለምን ፡ ያድራል ፡ አላቸው ። እጄንም
እግሬንም ፡ ዳሳችሁ ፡ እዩ ። ለምትሐት ፡ በኔ ፡
እንደምታዩት ፡ ሥጋ ፡ ዐጥንት ፡ የለውምና ። ይህን
ብሎ ፡ የተወጋ ፡ ጎኑን ፡ የተቸነከሩ ፡ እጆቹንና ፡
እግሮቹን ፡ አሳያቸው ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ጌታ
ችንን ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

፳፪ ፡ ዳግመኛም ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ አባቴ ፡
እንደ ፡ ላከኝ ፡ እኔም ፡ እልካችኋለሁ ፡ አላቸው ።
ይህንን ፡ ብሎ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አሳደረባቸው ።

መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀብላችሁ ፡ ኃጢአትን ፡ ይቅር ፡ ያላችሁላቸው ፡ ይቀርላቸዋል ፡ ይቅር ፡ ያላላችሁላቸውን ፡ አይቀርላቸውም ፡ አላቸው ።

## አምሰተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ሁለተኛ ፡ ጌታችን
ኢየሱስ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ከገዘግ ፡ ቤት ፡ ገብቶ
ተገለጸላቸውና ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ አላቸው ።
፪ ፤ ቶማስንም ፡ እጅህን ፡ አምጣ ፡ እጄንም ፡
ጎኔንም ፡ ዳስህ ፡ እይ ፡ አለው ። እመን ፡ እንጂ ፡
አትጠራጠር ፡ አለው ። ያንንም ፡ የጌታን ፡ ሥጋ ፡
ቶማስ ፡ ዳሰሰው ። አካላዊ ፡ ቃል ፡ በሥጋው ፡
ተሰቅሎ ፡ ሳለ ፡ ታግሦ ፡ የተቀበላቸውን ፡ የቅንዋ
ቱን ፡ ቦታ ፡ አየ ።
፫ ፤ ቶማስም ፡ በዳሰሰው ፡ ጊዜ ፡ ከመለኮትነቱ ፡
እሳትነት ፡ የተነሣ ፡ እጁ ፡ ተቃጠለ ። ቶማስም ፡
ደንግጦ ፡ አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ጌታዬ ፡ አለ ።
፬ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስንም ፡ አየኸኝና ፡ አመንኸ
ኝን ፡ ደጋጎቹስ ፡ ሳያዩኝ ፡ የሚያምኑብኝ ፡ ናቸው
ብሎ ፡ መለሰለት ። ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ በደቀ ፡
መዛሙርቱ ፡ ፊት ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ያልተጻፈ ፡
ሌላ ፡ ብዙ ፡ ተአምራትን ፡ አደረገ ።
፭ ፤ ይህም ፡ የተጻፈው ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የእግ
ዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ ፡ እንደሆነ ፡ ታምኑ ፡
ዘንድ ፡ ነው ። በስሙም ፡ ስም ፡ አምናችሁ ፡ የዘለዓለም

ሕይወትን ፡ ታገኙ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ እየበላ ፡ እየጠጣ እስከ ፡ ዐርባ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ተቀመጠ ።

## ስድስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ በአርባኛውም ፡ ቀን ፡ በብሩህ ፡ ደመና ፡ በሠረገላ ብርሃን ፡ በመላእክት ፡ ምስጋና ፡ በነጋሪት ፡ ድምፅ ፡ በኪሩቤል ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ዐረገ ። በነፋስም ፡ ክንፍ ተቀምጦ ፡ ወጣ ። በመላእክትም ፡ ከተማ ፡ ዘጠኝ ፡ ቀን ፡ አስተማረ ።

፪ ፤ በመዠመሪያይቱ ፡ ቀንም ፡ መላእክት ፡ ተገዙለት ፡ ሰገዱለትም ። በሁለተኛውም ፡ ቀን ፡ መላእክት ፡ ሰገዱለትም ፡ አመሰገኑትም ። በሦስተኛውም ቀን ፡ አጋዕዝዕት ፡ አመሰገኑት ፡ ሰገዱለትም ።

፫ ፤ ባራተኛውም ፡ ቀን ፡ መኳንንት ፡ አመሰገኑት ፡ ሰገዱለትም ። ባምስተኛውም ፡ ቀን ፡ መናብርት ፡ አመሰገኑት ፡ ሰገዱለትም ። በስድስተኛውም ፡ ቀን ፡ ኃይላት ፡ አመሰገኑት ፡ ሰገዱለትም ። በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ሊቃናት ፡ አመሰኑት ፡ ሰገዱለትም ።

፬ ፤ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ሱራፌል ፡ አመሰገኑት ፡ ሰገዱለትም ። በዘጠነኛውም ፡ ቀን ፡ ኪሩቤል አመሰገኑት ፡ ሰገዱለትም ። በማረጉም ፡ የሰማይን ፡ ጐዳና ፡ ጠረገልን ፡ የሰማይንም ፡ በር ፡ ከፈተልን ።

፭ ፤ ባሥረኛውም ፡ ቀን ፡ በባቱ ፡ ቀኝ ፡ በልዑል ዙፋኑ ፡ ተቀመጠ ። አባቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ልጁ ፡ በቀኝ ፡ ተቀመጥ ፡ ብሎታልና ። መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በቀኙ ፡ ያለ ፡ ነው ።

፮ ፤ በጌትነቱም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ እንደዐረገ ፡ ዳግመኛም ፡ በጌትነቱ ፡ ባባቱም ፡ ጌትነት ፡ ይመጣል ። በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ጌትነት ፡ ይመጣል ። ብዙ ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ በሚሆኑ ፡ በመላእክት ፡ የተመሰገነ ፡ በሰማይ ፡ ደመና ፡ ይመጣል ። መብረቅ ከምሥራቅ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንደሚታይ ፡ ይመጣል ። ከመስቀሉም ፡ ከችንካሩም ፡ ከእሾኽም ፡ አክሊሉ ፡ ጋራ ። በተወጋበትም ፡ ጦርም ፡ ጋራ ፡ ሐሞትም ፡ ከጠጣበትም ፡ ጋራ ። የተቸነከሩ ፡ የጆቹም ፡ የግሮቹም ፡ ደም ፡ እየፈሰሰ ። የተወጋ ፡ ጎኑም ፡ ደም ፡ እየፈሰሰ ፡ ለዘለዓለም ፡ የ ሚሆን ፡ ቸርነቱን ፡ ለመፈጸም ፡ ይመጣል ።

## ሰባተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ጌቶቼ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፤ አደራ እላችኋለሁ ። እመቤቴ ፡ ማርያም ፡ አንችንም ፡ እማልድሻለሁ ፡ ቃል ፡ ኪዳንም ፡ ግቢልኝ ፡ እልሻለሁ ። በነፍሱና ፡ በሥጋው ፡ በተቀበላቸው ፡ መከራዎች ፡ ሁሉ ።

፪ ፤ በመቸንከሩም ። የእሾኽ ፡ አክሊል ፡ ተቀዳጅቶ ፡ በመስቀሉ ። በሞቱም ፡ ወደ ፡ ሲኦልም ፡

በመውረዱ ። በጦር ፡ በመወጋቱ ። ጌታችን ፡ ኢየ
ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በመቀበሩ ። ኃጢአቴን ፡ ሁሉ ፡
ይቅር ፡ ትለኝ ፡ ዘንድ ። ከኃጢአትም ፡ ሁሉ ፡
ፍዳ ፡ ታድነኝ ፡ ዘንድ ፡ ለዘለዓለሙ ፡ አሜን ።

## የአሐዱ ፡ አርኬ ።

፩ ፤ መስቀልን ፡ ታግሠህ ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡
አምስት ፡ ሰዓት ፡ የቆየህ ፡ ክርስቶስ ፡ በሕያው ፡
ሥጋህና ፡ በሞተ ፡ ሥጋህ ፡ ለአይሁድ ፡ አርባ ፡
ዘመን ፡ እንደ ፡ ሰጠህ ፡ የንስሐ ፡ ዕድሜ ፡ ስጠኝ ፡
በድንገትም ፡ አትግደለኝ ።

፪ ፤ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤ በፍቅርህ ፡ ከአይሁድ ፡ ፍቅር
የተለዩ ፡ ወገኖች ፡ ወልድ ፡ ከመስቀል ፡ ጋራ ፡ የተ
ቸነከረና ፡ የተሰቀለ ፡ ሁኖ ፡ እንዳያድር ፡ ከጲላ
ጦስ ፡ ዘንድ ፡ ሥጋህን ፡ ለማውረድ ፡ ለመኑ ፡ ባወረ
ዱህም ፡ ጊዜ ፡ በምስጋና ፡ ቃል ፡ ከመስቀሉ ፡ ወርዶ ፡
ለሁሉ ፡ ሕይወትን ፡ አደረገ ፡ አሉ ።

፫ ፤ በዋግራ ፡ ሽቱና ፡ በከርቤ ፡ ገርዜን ፡ በሚባል ፡
ልብስም ፡ ሙታን ፡ እንደሆኑ ፡ እንደ ፡ አይሁድ ፡
ሕግ ፡ የገነዙህ ፡ የታመኑ ፡ ሟች ፡ ስትሆን ፡ ዐይና
ችን ፡ የገለጥህ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤ በምዕ
ራብ ፡ ቦታ ፡ አታስቀምጠኝ ፡ ኵነኔና ፡ ደይን ፡
በዚያ ፡ የተዘጋጀ ፡ ነውና ።

፬ ፤ ሁለት ፡ የሆኑ ፡ የአራት ፡ ጻድቃን ፡ በታች ፡ ወዳለ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ አውርደው ፡ የቀበሩህ ። በዮሴፍ ፡ ተክል ፡ ቦታ ፡ የታነፀ ፡ መቃብር ፡ ሦስት ክንድ ፡ ሲሆን ፡ እንዴት ፡ ቻለህ ፡ እስከ ፡ ትንሣኤስ ፡ ድረስ ፡ በውስጡ ፡ እንዴት ፡ ተኛህ ።

፭ ፤ የሚያስፈራ ፡ የአንበሳ ፡ ልጅ ፡ በኃይሉ ፡ እንዲነሣ ። ከጣፈጠ ፡ ከወይኑ ፡ መጠጥም ፡ የተነሣ ፡ ኖኅ ፡ እንደነቃ ፡ በሰላም ፡ ከሞትህ ፡ በኋላ ፡ የተነሣህ ፡ ደም ፡ በደም ፡ ይነጻልና ፡ አቤቱ ፡ በሽተኛ ፡ የምሆን ፡ የኔ ፡ የባሪያህን ፡ ደም ፡ በደምህ ፡ አንጻ ።

፮ ፤ በታላቅ ፡ ምስጋና ፡ ያረግህ ፡ የሚያቃጥል ፡ የእየር ፡ እሳትም ፡ ዕርገትህን ፡ ያልከለከለህ ። ባራተኛ ፡ሰማይ ፡ ውስጥ ፡ የምትኖር ፡ ክርስቶስ ፡ ባለቀስኸው ፡ ልቅሶ ፡ ሀዘን ፡ ባየሃት ፡ ጊዜ ፡ በደለኛ ፡ ሰው ፡ የምሆን ፡ እኔን ፡ በማየ ፡ ንስሐ ፡ እጠበኝ ፡ ከኃጢአትም ፡ አንጻኝ ።

፯ ፤ ፍጹም ፡ በሆነ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቀኝ ሳለህ ፡ በግራ ፡ የይሁዳ ፡ በተለየ ፡ አብ ፡ ቀኝ ፡ የተቀመጥህ ። አቤቱ ፡ ዓለም ፡ እንደሚሰጥ ፡ አትሰጥምና የሥጋና ፡ የነፍስ ፡ መድኃኒትን ፡ ዛሬ ፡ ስጠኝ ።

፰ ፤ ባንተ ፡ ምስጋና ፡ በአብ ፡ ምስጋና ፡ ፍሬ ፡ በሆነ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ምስጋና ፡ በብዙዎች መላእክት ፡ ምስጋና ፡ የምትመጣ ፡ መስቀልህ ፡ ትከሻ ፡ የማይችለው ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤ አቤቱ ፡ ነፍሴን ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ ቦታ ፡ አሳርፋት ። ግዙፍ ፡

የሆነ ፡ በሥጋዊ ፡ ሕይወቴም ፡ ላይ ፡ ጥፋትን ፡ አታሳየኝ ።

፱ ፤ ፈጣሪዬ ፡ ሆይ ፤ በብዙ ፡ መመታትህ ፡ ቍጥር ላንተ ፡ ምስጋና ፡ ይገባሃል ። ፈጣሪዬ ፡ ሆይ ፤ በብዙ ፡ መጸፋትህ ፡ ቍጥር ፡ ላንተ ፡ ምስጋና ፡ ይገባሃል ። ፈጣሪዬ ፡ ሆይ ፤ በብዙ ፡ መገረፍህ ፡ ቍጥር ፡ ላንተ ፡ ምስጋና ፡ ይገባሃል ። ፈጣሪዬ ፡ ሆይ ፤ በብዙ ፡ መከራህ ፡ ቍጥር ፡ ላንተ ፡ ምስጋና ፡ ይገባሃል ። ሞትን ፡ የተቀበልህ ፡ ንጉሤ ፡ ሆይ ፤ ላንተ ፡ ምስጋና ፡ ይገባሃል ።

፲ ፤ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤ ኃጢአቴን አስተሥርይልኝ ፡ በደሎቼንም ፡ አጥፋ ። የኔ ፡ የባሪያህን ፡ የዕለት ፡ ጠላቶቼንና ፡ ጥንተ ፡ ጠላቶቼን ፡ አስታግሥልኝ ። ለዘለዓለሙ ፡ በውነት ፡ ይሁን ፡ ይሁን ። በዕውነት ፡ ይደረግልኝ ።



ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር ለያይቶን የነበረውን የጸብ ግድግዳ አፈራርሶ በሰማይም በምድርም ያሉትን ነገሮች ሁሉ ከራሱ ጋር አስታረቀ በመስቀል ላይ በፈሰሰው ደሙም ሰላምን መሠረተ።

ኤፌ፡ ፪ ፡ ፲፬-፲፯ ። ቆላስ ፡ ፩ ፡ ፳ ።